www.chilot.me



ይችላል ፡፡ በዚህ አኳኋን የተተካውም ምክትል አባል ለዚያው ለተተካበት ስብሰባ እንደ አባል ሆኖ ይቆጠራል ፡፡

አንቀጽ ስምንት ፡፡

ስለ ስብሰባ መሟላት ፡፡

በማናቸውም ስብሰባ ከአባሎች ወይም የቦርዱ አባሎች ሆነው እንዲሠሩ ከተተኩት ምክትል አባሎች መካከል ሦስቱ ከተገኙ ስብሰባው እንደተሟላ ይቆጠራል ፡፡

አንቀጽ ዘጠኝ ፡፡

ስለ ድምፅ አሰጣጥ ፡፡

የቦርዱ ውሳኔ የሚጸናው በስብሰባው በተገኙ አባሎች ወይም የቦርዱ አባሎች ሆነው እንዲሠሩ በተተኩት ምክትል አባሎች የድምፅ ብልጫ ነው ፡፡ ድምፁ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሊቀ መንበሩ ሁለተኛ ወይም ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል ፡፡

አንቀጽ አሥር ፡፡

ስለ ውሳኔዎች መፈረም ፡፡

በያንዳንዱ የቦርድ ውሳኔ በስብሰባው ላይ የተገኙት አባሎች ሁሉ እንዲፈርሙበት ያስፈልጋል ፡፡

አንቀጽ አሥራ አንድ ፡፡

ቃለ ጉባኤዎችን ስለ ማረጋገጥ ፡፡

የማናቸውም ስብሰባ ቃለ ጉባኤ በቦርዱ ከጸደቀ በኋላ የቦርዱ ጸሐፊ ፈርምበት የዚያው ስብሰባ ሕጋዊ ሰነድ ይሆናል ፡፡

ክፍል ፫

ስለ ቦርዱ ሥልጣን ፡፡

አንቀጽ አሥራ ሁለት ፡፡

ሀ/ ቦርዱ ፡—

፩/ የሥራ ክርክሮችን ለማየት ፣ ተከራካሪዎችን ለማስታረቅ ፣ ለመገላገል ፣ ቢያስፈልግም የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱም በፊት ለጊዜው የሚያገለግል ዘዴ ለማድረግና የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት ፤

፪/ ተገቢ ስላልሆነ የሥራ አፈጻጸም የሚቀርበውን ማናቸውንም አቤቱታ ለማየት ፤ እንደዚህ ያለውን አፈጻጸም ለመከልከልና ይኸንኑ ተግባር እንዲተው ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሰዎች ወይም ድርጅቶች ለማዘዝ ፤

፫/ ውሳኔዎችንና ብይኖችን ተገቢ በሆነው መንገድ ለማስፈጸም ፤

፬/ ድርጅቶች እንዲፈርሱ ለሚኒስትሩ አሳብ ለማቅረብ ፤
ሥልጣን አለው ፡፡

www.chilot.me



በማናቸውም የሥራ ሰዓት ውስጥ ከማናቸውም የሥራ ድርጅት ውስጥ ለመግባት ፤ ስለ ሆነ ግን ድንገተኛ አስቸኳይ ነገር ካላጋጠመ በቀር ቦርዱ እንደዚህ ካለው የሥራ ድር ጅት ውስጥ ከመግባቱ በፊት በቂ በሆነ ጊዜ ቀደም ብሎ ለድርጅቱ ባለቤት ማስታወቅ አለበት ፤

ሰ/ ስለ ሥራው ዝርዝር አፈጻጸምና አስተዳደር የሚሰጥ ደንብ ለማውጣት ።

ክፍል ፱

ስለክርክሩ መስማት ።

አንቀጽ አሥራ አራት ።

ስለ ክርክሩ መስማት የሚሰጥ ማስታወቂያ ።

ሀ/ ስለማናቸውም ጉዳይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ቦርዱ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ወገኖች ማስታወቅና ቀርበው አሳባቸውን እንዲገልጹ መፍቀድ አለበት ። ስለዚህ ጉዳዩ ስለሚሰማ በት ቀን ፣ ሰዓትና ስፍራ ከሦስት (፫) ቀን ከማያንስ ጊዜ አስቀድሞ ለተባሉት ወገኖች በጽሑፍ የሆነ ማስታወቂያ መስጠት አለበት ።

ለ/ ቦርዱ ጉዳዩ የሚሰማበትን ቀንና ስፍራ ሲወስን ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ክርክራ ቸውን ለቦርዱ ለማሰማት በቂ ዕድል ሊኖራቸው አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ አለበት ።

ሐ/ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ከቦርዱ ዘንድ በሚቀርቡበት ጊዜ ቦርዱ እንደሚወስነው ጠበቃ ፣ አማካሪዎችና ረዳቶች ይዘው ለመቅረብ ይችላሉ ።

አንቀጽ አሥራ አምስት ።

በተወሰነው ጊዜ ስላለመቅረብ ።

ሀ/ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ወገኖች ማናቸውም ወይም ጉዳይ በሚሰማበት ጊዜ እንዲቀርብ ደንበኛ መጥሪያ የደረሰው ማናቸውም ሰው ስለዚህ ጉዳይ በተወሰነው ጊዜ ቀርቦ ቃሉን ባይሰጥ ፣ ቦርዱ ጉዳዩን ማየቱን ሊቀጥል ይችላል ። በዚህም ምክንያት ይግባኝ ሊባል አይቻልም ።

ለ/ ያልቀረበውም ሰው በተወሰነው ጊዜ ሳይቀርብ የቀረው በራሱ ጥፋት አለመሆኑ ሲታወቅ ከቦርዱ ዘንድ እንዲቀርብ እንደገና ዕድል ይሰጠዋል ።

አንቀጽ አሥራ ስድስት ።

ስለ ማስታረቅ ።

ቦርዱ የቀረበለትን የሥራ ክርክር በስምምነት ለመወሰን የተቻለውን ሁሉ ማድረግ አለ በት ። ለዚሁም ዓላማ አስፈላጊ መስሎ በታየው በማናቸውም የማስታረቂያ ዘዴ ሊሠራበትና ሊጠቀምበት ይችላል ።

አንቀጽ አሥራ ሰባት

ጉዳዩን ስለ ማመዛዘን ።

ሀ/ ቦርዱ ጉዳዩን በሚያይበት ጊዜ የሥራ ክርክሮችን በተቻለ መጠን በፍጥነት መወሰን አስፈላጊና ተገቢም መሆኑን መገንዘብ አለበት ።

www.chilot.me



የፎግስታድ የእንጨት ሥራ ሠራተኞች ማኅበር ይግባኝ ባይ ፤ ጃኮብ ፎግስታድ መልስ ሰጭ (የጠቅላይ ንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት ፡ አዲስ አበባ ፤ ፲፱፻፶፩ ዓ. ም.) የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት ፡ ፩ኛ ቮልዩም ፤ ገጽ ፪፹፫ ።

## ምዕራፍ ፫

## ስለ አሠሪዎች ማኅበርና ስለ ሠራተኞች ማኅበር ።

### አንቀጽ ሃያ ።

### ስለ ማኅበር መብት ።

ሀ/ አሠሪዎች ፡ የአሠሪዎች ማኅበር ለማቋቋምና የማኅበሩ አባሎች ለመሆን ፤ እንዲሁም ሠራተኞች ፡ የሠራተኛ ማኅበር ለማቋቋምና የማኅበሩ አባሎች ለመሆን ይችላሉ ። እነዚህ ድርጅቶች በሚኒስቴሩ ከተመዘገቡ በኋላ ሕጋዊ ሥራዎችን ሁሉ ለመሥራት ይችላሉ ።

ለ/ ማንኛውም አሠሪ በአንድ ጊዜ ከአንድ የአሠሪዎች ማኅበር በላይ አባል ለመሆን አይችልም ። እንዲሁም አንድ ሠራተኛ በአንድ ጊዜ ከአንድ የሠራተኛ ማኅበር በላይ አባል ሊሆን አይችልም ።

ሐ/ ከአምሳ (፶) የሚያንሱ ሠራተኞች ቀጥሮ በሚያሠራ የሥራ ድርጅት ውስጥ የሠራተኛ ማኅበር ማቋቋም አይቻልም ። ሆኖም የዚህ የሥራ ድርጅት ሠራተኞች በጠቅላላ የሠራተኛ ማኅበሮች ውስጥ አባል ለመሆን ይችላሉ ።

መ/ ሚኒስትሩ በአንዳንድ ልዩ አኳኋን በዚህ በ፳ኛው አንቀጽ በፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) የተመለከቱትን ውሳኔዎች ሊያሻሽል ይችላል ።

### አንቀጽ ሐያ አንድ ።

### ስለ መመዝገብ ።

ሀ/ እያንዳንዱ የአሠሪዎች ማኅበርና እንዲሁም እያንዳንዱ የሠራተኞች ማኅበር እንደተቋቋመ ወዲያው በሥራ ድርጅቱ ከፍተኛ ሹም በሚገባ ከተረጋገጡ በኋላ ከዚህ የሚከተሉትን ፤—

፩/ የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ ፤ የውስጥ ደንብና የአባሎችን መብትና ተግባር ወይም የድርጅቱ አስተዳደርና የሥራ አፈጻጸም የሚወስኑትን ሌሎች ሠነዶች ሁለት (፪) ግልባጭ ፤

፪/ የድርጅቱ አባሎች ስምና አድራሻ የተጻፈበትን ዝርዝር (ሊስት) ሁለት (፪) ግልባጭ፤

፫/ ድርጅቱን ያቋቋሙት ወይም እንደ መሥራች ሆነው የሚሠሩት ሰዎች ስም የተጻፈበትን ዝርዝር (ሊስት) ሁለት (፪) ግልባጭ ፤

፬/ የድርጅቱ አባል ለመሆን ለመጀመሪያ ጊዜና ለአባልነትም የሚከፈለውን ሒሳብና የመዋጮውን ድርሻ ልክ ፤ እንዲሁም ከአባሎች የሚፈለገውን ሌላም የገንዘብ መዋጮ የሚገልጸውን ማስታወቂያ ሁለት (፪) ግልባጭ ፤

፭/ የድርጅቱ ሹማምንት ስምና አድራሻ የተጻፈበትን ዝርዝር (ሊስት) ሁለት (፪) ግልባጭ ፤ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት ።

ለ/ የድርጅቱ ሹማምንት ወይም ወኪሎች በተመረጡ ወይም በተሾሙ ቁጥር በድርጅቱ ከፍተኛ ሹም በሚገባ ከተረጋገጠ በኋላ ፤ ድርጅቱ የሹማምንቱ ወይም የወኪሎቹ ስምና አድራሻ የተጻፈበትን የተለወጠውን ዝርዝር (ሊስት) ሁለት (፪) ግልባጭ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት ።

www.chilot.me



ሐ/ በዚህ በሓያ አንደኛው አንቀጽ በፊደል ተራ (ሀ) የተመለከቱት ሠነዶች ለሚኒስትሩ መቅረብ ድርጅቱ በሚኒስትሩ ለመመዝገብ ማመልከቻ እንዳቀረበ ይቆጠራል ። ሚኒስትሩ የቀረቡለት ሠነዶች ያልተሟሉ ወይም የማይበቁ ወይም በዚህ አዋጅ የተጻፈውን የተፃ ለፉ ሆነው ካላገኛቸው በቀር የተባለውን ድርጅት ይመዘግበዋል ።

መ/ ሚኒስትሩ የድርጅቱን መመዝገብ የማይቀበለው የሆነ እንደሆነ የማይቀበልበትን ምክን ያት በመዘርዘር ይኸንኑ ለድርጅቱ ማስታወቅ አለበት ።

ሠ/ በዚህ በ፳፩ኛው አንቀጽ በፊደል ተራ (ሀ) የተዘረዘሩት ሠነዶች ከቀረቡበት ቀን ጀምሮ በሠላሳ (፴) ቀን ውስጥ ለምዝገባ በቀረበለት ማመልከቻ ላይ ሚኒስትሩ ውሳኔ ሳያደርግ ቢቀር ድርጅቱ እንደተመዘገበ ይቆጠራል ።

ረ/ በዚህ በ፳፩ኛው አንቀጽ በፊደል ተራ (መ) ወይም (ሠ) እንደተመለከተው ስለ ድርጅቶች መመዝገብና በዚህ አዋጅ በሦስተኛው አንቀጽ በፊደል ተራ (ሰ) መሠረት ስለ ድርጅቶች መፍረስ የሚሰጠውን ማስታወቂያ ሚኒስቴሩ በብዛት በሚታተም ጋዜጣ ማውጣት አለበት።

### አንቀጽ ሐያ ሁለት ።

### የድርጅቱ የሥራ ወሰን ።

ሀ/ የአሠሪዎች ማኅበርና የሠራተኞች ማኅበር ዋና ዓላማ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን የሥራ ሁኔታዎችና ተግባሮች መወሰንና እንዲሁም የአባሎችን የኤኮኖሚ ፣ የማኅበራዊና የሞ ራል ጥቅም ማጥናት ፣ መጠበቅና ማሳደግ ነው ።

ለ/ እነዚህ ድርጅቶች በተለይ የኤኮኖሚና የማኅበራዊ ኑሮን ለማሳደግ የሥራ ሁኔታዎችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ ያለ ሥጋትና በፈቃደኛነት መነጋገር አለባቸው ።

ሐ/ የአሠሪዎች ማኅበርና የሠራተኞች ማኅበር በማናቸውም አኳኋን ቢሆን የፖለቲካን ዓላማ መከተል ወይም በማናቸውም የፖለቲካ ሥራ ተካፋይ መሆን አይችሉም ።

መ/ የአሠሪዎች ማኅበርና የሠራተኞች ማኅበር በተቻለ መጠን የሥራ ክርክሮችን በሰላማዊ መንገድ እንዲወስኑ ያስፈልጋል ። የኅብረቱ ክርክር ዐቢይ ክፍል ሆኖ የተባሉት ድርጅቶች የፈቃደኛነት ዕርቅ እንዲያደርጉ ሊበረታቱና በሚያደርጉትም የኅብረት ስምምነት ውስጥ በበጎ ፈቃደኛነት የተስማሙ መሆናቸው እንዲገለጽ ያስፈልጋል ።

ሠ/ የአሠሪዎች ማኅበርና የሠራተኞች ማኅበር ማናቸውንም የሥራ ክርክር ወይም ማናቸ ውንም ተገቢ ያልሆነ የሥራ አፈጻጸም ጉዳይ ሲደርስ ለቦርዱ ለማቅረብ መብት አላቸው ።

ረ/ አሠሪዎች ለመጠባበቂያ የሚሆን ገንዘብ ለማጠራቀምና ለመጠበቅ መብት አላቸው ። ይህም መጠባበቂያ ገንዘብ ከሌላው የድርጅቱ ገንዘብ ተለይቶ መቀመጥና መጠበቅ አለበት ። ሂሣቡም በንግድ ሕግ ቁጥር ፬፻፳፰ እና በተከታዩ የተጻፈው ተቃራኒ ቢሆንም እንደ ኪሣራ ተቆጥሮ ለማናቸውም የድርጅቱ ዕዳ አያልፍም ።

## ምዕራፍ አራት ።

## ስለኅብረት ክርክር ።

### ክፍል ፩ ።

### ስለ ኅብረት ክርክርና ስለ ኅብረት ስምምነት ።

### አንቀጽ ሐያ ሦስት ።

### የኅብረት ክርክር ለማድረግ መብት ያላቸው ወገኖች ።

የኅብረት ክርክር ለማድረግ ወኪል ሆኖ ለመሥራት የሚችሉ ፡—

ሀ/ በአንድ አሠሪ ወይም በብዙዎች አሠሪዎች ወይም በአሠሪዎች ማኅበር ስም ሆነው የሚ ሠሩ ሰዎች ፤

www.chilot.me



ለ/ ጉዳዩ በሚመለከተው የሥራ ድርጅት ውስጥ ከሚገኙት ሠራተኞች ለሚበዙት በመወከል በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የሠራተኛ ማኅበሮች ስም ሆነው የሚሠሩ ሰዎች ወይም ፤

ሐ/ እንደዚህ ያለ የሠራተኛ ማኅበር በሌለ ጊዜ ጉዳዩ በሚመለከተው የሥራ ድርጅት ውስጥ ከሚገኙት ሠራተኞች ለሚበዙት ለመወከል የተመረጡና በሚገባ ሥልጣን የተሰጣቸው የሠራተኞች ኮሚቴ ወኪሎች ፤
ብቻ ናቸው ።

## አንቀጽ ሐያ አራት ።

## የኅብረት ስምምነት ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ ።

ሀ/ የስምምነቱ ድርድር በሌላ አኳኋን በግልጽ ካልተወሰነ አንድ የኅብረት ስምምነት ከጸና በኋላ እስከ ሦስት (፫) ዓመት ጊዜ ድረስ ማናቸውም አሠሪ ፤ የአሠሪዎች ማኅበር ሠራተኛ ፤ የሠራተኞች ማኅበር ወይም የሠራተኞች ኮሚቴ ሊቃወመው አይችልም ።

ለ/ ከፍ ያለ የኤኮኖሚ ለውጥ የተደረገ እንደሆነ ቦርዱ በዚህ በሐያ አራተኛው አንቀጽ በፊደል ተራ (ሀ) የተጻፈውን ሊሽረው ይችላል ።

ሐ/ በዚህ አዋጅ ተቃራኒ የሆነ ውሳኔ ተጽፎ ቢገኝም የኅብረቱን ስምምነት ያደረጉት ሁለቱም ወገኖች የተባለውን ስምምነት በማናቸውም ጊዜ ተስማምተው ለማሻሻል ወይም ለመለወጥ ይችላሉ ።

## አንቀጽ ሐያ አምስት ።

## የኅብረት ስምምነት ዓይነት (ፎርም)

ሀ/ የኅብረት ስምምነት በጽሑፍ ሆኖ የተከራካሪዎች ወገኖች ወኪሎች ይፈርሙበታል ።

ለ/ ሚኒስትሩ ስለዚሁ ጉዳይ ባቋቋመው መዝገብ እንዲመዘገብ ስምምነቱ ወዲያው እንደተፈጸመ የያንዳንዱ የኅብረት ስምምነት ሁለት (፪) ግልባጭ በቦርዱ አማካይነት ለሚኒስትሩ መተላለፍ አለበት ።

## ክፍል ፭ ።

## የአሠሪዎችና የሠራተኞች ተግባር ።

## አንቀጽ ሐያ ስድስት ።

## በቅን ልቡና መነጋገር ስለሚገባ ።

በኅብረቱ ክርክር ተካፋይ የሆነው እያንዳንዱ ወገን የንግግሩ ተካፋይ የሆኑት ሌሎችም ወገኖች ሁሉ መብት ያላቸው መሆኑን አውቆ ከእነርሱ ጋር በቅን ልቡና እንዲነጋገር ያስፈልጋል ።

## አንቀጽ ሐያ ሰባት ።

## ሰላማዊ አኳኋን ።

የኅብረት ክርክር የሚያደርጉ ወገኖች በንግግሩ ጊዜ እነርሱን የወከሉአቸው ሰዎች ወይም ድርጅቶች የኅብረቱን ክርክር ከሚያሰናክሉ ወይም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሌሎች ወገኖች ለመጫን ከታቀዱ ሥራዎች እንዲርቁ አስፈላጊውን ሁሉ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው ።

www.chilot.me



## ምዕራፍ አምስት ።

## የተከለከሉ ነገሮች ።

### አንቀጽ ሐያ ስምንት ።

### ተገቢ ያልሆነ ሥራ አፈጻጸም ።

ተገቢ ያልሆነ የሥራ አፈጻጸም ሁሉ ክልክል ነው ።

### አንቀጽ ሐያ ዘጠኝ ።

### የማይፈቀድ አሠራር ።

ማንኛውም ሰው ፦

ሀ/ የአሠሪዎች ማኅበር ወይም የሠራተኞች ማኅበር አባል እንዲሆን ወይም እንዳይሆን ወይም አባልነቱን እንዲተው ለማድረግ በማንኛቸውም ሰው ላይ መዛት ፣ ማስፈራራት ወይም ተገቢ ባልሆነ አኳኋን መጫን ፤

ለ/ ጉዳዩ የሚመለከተው አሠሪ ሳይፈቅድ የተባለው የሠራተኞች ማኅበር አባል እንዲሆኑ ለማባበል በሠራተኞች ማኅበር ስም በሥራ ሰዓት ወይም በአሠሪው መሥሪያ ቤት ውስጥ ሠራተኞቹን መሰብሰብ ፤ አይችልም ።

### አንቀጽ ሠላሳ ።

### አሠሪዎች አድልዎ እንዳያደርጉ ስለመከልከሉ ።

ማናቸውም አሠሪ ፦

ሀ/ ያንድ የሠራተኞች አባል በመሆን ወይም በሠራተኛ ማኅበር ሥራዎች ምክንያት ስለሥራ ሁኔታዎች በሠራተኞች መካከል አድልዎ ማድረግ ፤

ለ/ በሠራተኞች አቀጣጠር ረገድ የሠራተኞች ማኅበር አባል የሆኑትን ካልሆኑት ወይም የሠራተኞች አባል ያልሆኑትን የሠራተኞች ማኅበር አባል ከሆኑት በማግረጥ መቅጠር ወይም በሥራ ላይ ማቆየት ፤

ሐ/ የሠራተኛ ማኅበር አባል በመሆኑ ምክንያት ማናቸውንም ሰው ከሥራ ማሰናበት ፤

መ/ የሠራተኛ ማኅበር እርሱ በፈለገው አኳኋን እንዲቋቋም መጫን ወይም አባል መሆን ወይም በማናቸውም የሠራተኛ ማኅበር ሥራዎች ጣልቃ መግባት ፤ ክልክል ነው ።

ስለሆነ ግን አንድ አሠሪ በቂና ተገቢ በሆነ ምክንያት ማናቸውንም ሠራተኛ ከሥራ አግዶ ለማቆየት ፣ ለማሰናበት ፣ ከሥራ ለማስወጣት ወይም ለማዛወር በዚህ በሠላሳኛው አንቀጽ የተጻፈው አይከለክለውም ።

#### የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ማስታወሻ ።

#### የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ ፤ የሠራተኞች ማኅበር አባል ስለመሆን ።

የአንድ የሠራተኞች ማኅበር ፕሬዚዳንት የሠራተኞች ማኅበር አባል በመሆኑ ብቻ ከሥራ እንዲወጣ የተደረገው ከሕግ ውጭ ስለሆነ ወደ ሥራው እንዲመለስ እንዲደረግ ሲል የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ የሰጠውን ውሳኔ የጠቅላይ ንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት አጸደቀው ።

የሴራ ሚካኤል ሸክላ ፋብሪካ ይግባኝ ባይ ፤ የአንደምሴ የሥራ ማኅበር መልስ ሰጭ

(ጠቅላይ ንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት ፣ አዲስ አበባ ፣ ፲፱፻፶፯ ዓ. ም.) የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት ፣ ፪ኛ ቮልዩም ፣ ገጽ ፯ ።

www.chilot.me



የፍርድ ቤት ውሳኔ ማስታወሻ ።

በአሠሪና በሠራተኛ መካከል ያለው ግንኙነት በደንብ እንዲካሄድ ፣ ሥራ በደንብ እንዲከናወን ፣ አለ መግባባት ሲፈጠር ጉዳዩ በፍጥነት እንዲወሰንና እንደዚሁም እንዲህ ያሉ ጉዳዮች ሲገኙ የሚካሄድበት በፓርላማ ተመክሮበትና ተሻሽሎ የአሁኑ አዋጅ የሆነው የአሠሪና የሠራተኛ ድንጋጌ በፍትሐ ብሔር መሠረት ሠራተኛ ያለአግባብ ከሥራ ተሰናበትኩ በማለት ኪሣራ ለመጠየቅ ያለውን መብት አይዘጋበትም ሲል ከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ ሰጠ ።

ማሞ ይንበርበሩ ከሳሽ ፣ ይርጉ አበበ ተከሳሽ

(ከፍተኛው ፍርድ ቤት ፣ አዲስ አበባ ፣ ፲፱፻፶፮ ዓ. ም.) የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት ፣ ፩ኛ ቮልዩም ፣ ገጽ ፴፪ ።

አንቀጽ ሠላሳ አራት ።

ስለ ፍርድ ቤት መቋቋም ።

የፍርድ ሚኒስትራችን ሕግን ተከትሎ በዚህ አዋጅ መሠረት ለፍርድ ቤቶች የሚቀርቡት ጉዳዮች በተፋጠነና በተሟላ አኳኋን እንዲፈጸሙ ለማድረግ በፍርድ ቤቶች ውስጥ ስለ ሠራተኞች ጉዳይ የተለዩ ክፍሎች እንዲቋቋሙ ያደርጋል ።

አንቀጽ ሠላሳ አምስት ።

የኅብረት ስምምነቶችና የቦርዱ ውሳኔዎች ተፈጻሚ መሆን ስለሚገባቸው ።

ሀ/ የኅብረት ስምምነቶችና የቦርዱ ውሳኔዎች ወይም ብይኖች ጉዳዩ በሚመለከታቸው ሰዎች ሁሉ ላይ ይጸናሉ ።

ለ/ ማናቸውም የኅብረት ስምምነት ወይም የቦርዱ ውሳኔ ወይም ብይን ስለዚሁ ጉዳይ ጸንቶ ከሚገኘው ከማንኛውም ሕግ ይልቅ ለሠራተኞች የበለጠ መብት የሚሰጥ ሆኖ ሲገኝ በሕጉ ፈንታ የተባለው ስምምነት ወይም ውሳኔ ወይም ብይን ተፈጻሚነት ይኖረዋል ።

አንቀጽ ሠላሳ ስድስት ።

ስለ ሕጎች ፣ ደንቦች ወይም ትእዛዞች መሻር ።

በዚህ አዋጅ በሌላ አኳኋን በግልጽ ካልተወሰነ በቀር በዚህ አዋጅ ስለተመለከቱት ጉዳዮች በጽሑፍም ሆነ በልማድ ከዚህ በፊት ሲሠራባቸው የቆዩት ሕጎች ፣ ደንቦች ወይም ትእዛዞች በዚህ ተሽረዋል ።

አንቀጽ ሰላሳ ሰባት ።

ስለ ሕግ ክፍል ማስታወቂያ ።

ሚኒስትሩ በዚህ አዋጅ የተጻፈውን በሚገባ ለማስፈጸም ደንቦች ሊያወጣ ይችላል ።

የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ማስታወሻ ።

ስለ ሠራተኞች ጉዳይ ደንብ የማውጣት ሥልጣን ለሕዝባዊ ኑሮ እድገትና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ስለመስጠቱ

ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ በነጋሪት ጋዜጣ በቁጥር ፪፻፲/፲፱፻፶፮ ዓ. ም. የወጣው አዋጅ አንቀጽ ፴፮ የሕዝባዊ ኑሮ እድገትና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ለሠራተኛ የበለጠ መብት ለመስጠት የፍትሐ ብሔርን

www.chilot.me



## ፫/ ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ፤

፩/ «ሠራተኛ» ሲባል በ፲፱፻፶፪ ዓ. ም. በወጣው የፍትሐ ብሔር ሕግ በ፪ሺ፭፻፲፪ኛው አንቀጽ እንደተመለከተው የሥራ ውል ግዴታ የገባ ማናቸውም ሰው ማለት ነው። ይኸውም በሥራ ክርክር ወይም አንድ አሠሪ ባደረገው ተገቢ ያልሆነ አፈጻጸም ምክንያት ከሥራ ውጭ ሆኖ ሌላ በቂና ተመሳሳይ ሥራ ያላገኘውንም ሰው ይጨምራል ። ሆኖም የዚህ ቃል ትርጉም የሚከተሉትን ዓይነት ሰዎች አይጨምርም ፤

ሀ/ በሥራ አስኪያጅነት ፤ በዲሬክተርነት ፤ በተቆጣጣሪነት ወይም የአንድ አሠሪ ወኪል በመሆን የተቀጠረን ማናቸውንም ሰው ወይም በአሠሪው ስም ይህንን የመሳሰለ ሥራ የሚሠራውን ሰው ፤

ለ/ የቤት አሽከርን ፤

ሐ/ ለተወሰነ ጊዜ ተቀጥረው ከሚሠሩት ሰዎች በቀር ከአሥር የማያንሱ ቀዋሚ ሠራተኞች በሚገኙበት እርሻ ውስጥ የሚሠራን የእርሻ ወይም የከብት እርባታ ሠራተኛን ፤

መ/ በመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ጠቅላይ መሥሪያ ቤትና የመንግሥት ሠራተኞች የ፲፱፻፶፬ ዓ. ም. ትእዛዝ በአንቀጽ ፫ እንደተወሰነው የመንግሥት ሠራተኞች የሆኑትን ። ስለሆነም መንግሥትና መንግሥታዊ የአስተዳደር ወይም የቴክኒክ መሥሪያ ቤቶች በማያስተዳድሩአቸው ኢንዱስትሪዎች ፤ ንግድ ቤቶች ወይም ለትርፍ የሚሠሩ ሰዎች ለዚህ ደንብ አፈጻጸም እንደ መንግሥት ሠራተኞች አይቆጠሩም ።

፪/ «አሠሪ» ሲባል በዚህ ደንብ እንደተወሰነው ሠራተኛን ቀጥሮ የሚያሠራ ማናቸውም ሰው ማለት ነው ። ይኸውም መንግሥት ፤ የመንግሥት የአስተዳደር ወይም የቴክኒክ መሥሪያ ቤቶች የሚያስተዳድሩአቸውን ኢንዱስትሪዎች ፤ ንግድ ቤቶች ወይም ለትርፍ የሚሠሩ ሌሎች የሥራ ድርጅቶችን ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለአንድ አሠሪ ጥቅም በማስገኘት ወይም ወኪል በመሆን የሚሠራውን ማናቸውንም ሰው ይጨምራል ።

፫/ «እየተቋረጠ የሚሠራ ሥራ» ሲባል ዘወትር ሳይሆን አልፎ አልፎ የሚሠራ ሆኖ ይኸው ሥራ በሚፈጸምበት ወይም ሥራው የሚከናወንበት መሣሪያ በሚገኝበት ስፍራ የሠራተኛውን የዘወትር መገኘት የሚጠይቅ ሥራ ማለት ነው ።

፬/ «ሕጋዊ ውሳኔዎች» ሲባል ስለ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የወጡት ሕጎች ፤ የተመዘገቡ የኅብረት ስምምነቶች ፤ በዕርቅ ወይም በፍርድ የተበየኑና የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ የሰጣቸው ውሳኔዎች ሁሉ ማለት ነው ።

፭/ «በሰዓት የሚከፈል መደበኛ አበል» ሲባል አንድ ሠራተኛ ተቀጥሮ በሚያገለግልበት ጊዜ ከደንበኛው የሥራ ሰዓት በላይ ለሠራበት የተከፈለው የትርፍ ሰዓት ሒሳብ ሳይታሰብ ፤ በመጨረሻዎቹ አሥር ቀኖች ወይም ሠራተኛው ከተቀጠረ አሥር ቀኖች ያልሞላው እንደሆነ በነዚሁ በሠራባቸው ቀናት ውስጥ የተከፈለው ወይም ሊከፈለው የሚገባው ሒሳብ በሰዓት ታስቦ የተገኘው መካከለኛ (አቬሬጅ) ሒሳብ ማለት ነው ።

### የተጠቀሱ ሕጎች

የፍ. ሕ. ፲፱/በተ. የ. ፪ (፲፱፻፶፪) አን. ፪ሺ፭፻፲፪ ። የመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ጠቅላይ መሥሪያ ቤትና የመንግሥት ሠራተኞች የ፲፱፻፶፬ ዓ. ም. ትእዛዝ ፤ ፳፩/፫ (፲፱፻፶፬) ት. ፳፫ አን. ፫ ፤ ፫ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፪—፫ ።

www.chilot.me



፲/ ትእዛዙ ስለሚጸናበት ጊዜ ።

ይህ ትእዛዝ በነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ኅዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፶፮ ዓ.ም.

## ፳፫/፲፱ (፲፱፻፶፮) አ. ፪፻፹፱

## የሥራ ሁኔታዎች ደረጃ ስለመወሰንና ማስፈጸም የወጣ አዋጅ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እኛ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

በንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችን ውስጥ የሚገኘው የሠራተኛው ሕዝባችን ሕይወት፣ ሙሉ ሰውነቱ፣ ጤንነቱና የሕሊና ክብሩ (ሞራሉ) እንዲጠበቅ የሥራ ሁኔታዎችን ደረጃ መስጠትና መወሰን አስፈላጊ ስለሆነ፤

ተሻሽሎ በወጣው ሕገ መንግሥታችን በ፴፬ኛውና በ፹፰ኛው አንቀጾች የተጻፈውን ተመልክተንና የሕግ መምሪያና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቶቻችን የመከሩበትን ዓይተን ቀጥሎ ያለውን አውጀናል ።

### ምዕራፍ ፩ ።

### ጠቅላላ ።

፩/ አጭር አርእስት

ይህ አዋጅ «በ፲፱፻፶፮ ዓ.ም. ስለሥራ ሁኔታዎች ደረጃ የወጣ አዋጅ» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

፪/ ስለተሻሩ ሕጎች

በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. ከወጣው የፍትሐ ብሔር ሕግ በስተቀር በቁጥር ፺፰/፲፱፻፵፬ ዓ.ም. ስለ ፋብሪካ መቆጣጠር በወጣው አዋጅ ውስጥ ሠራተኛና አሠሪን የሚመለከቱት አንቀጾችና በዚህ አዋጅ ውስጥ ስለተመለከቱት ጉዳዮች ከዚህ ቀደም በጽሑፍም ሆነ በልማድ ሲሠራባቸው የቆዩት ሌሎች ሕጎች ሁሉ በዚህ አዋጅ ተሽረዋል ።

የተጠቀሰው ሕግ

የፍ.ሕ. ፲፱/በተ. የ. ፪ (፲፱፻፶፪) ።

፫/ ትርጓሜዎች

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩/ «አደጋ» ሲባል አንድ ሠራተኛ ሥራውን ሲፈጽም ወይም ከሥራው ጋር ግንኙነት ባለው ምክንያት በድንገት ያልታሰበ አደጋ ስለደረሰበት የሞተ እንደሆነ ወይም

www.chilot.me



አባሎች የአገልግሎታቸው ጊዜ በማናቸውም አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ እንዲያልቅ የመጀመሪያው ሹመት ሲሰጥ የአንድ (፩)፣ የሁለት (፪) እና የሦስት (፫) ዓመት አገልግሎት ጊዜ ተለይቶ መታወቅ አለበት ። አባሎቹንም እንደገና ለመሾም ይቻላል ።

፫/ ቦርዱ ሚኒስትሩ ከሚኒስቴሩ ውስጥ በሚወክላቸው ባለሥልጣኖች አማካይነት ስለ ጠቅላላ የሥራ ሁኔታዎች ወይም ስለአንድ የተለየ የሥራ ሁኔታ ምክር ለመስጠትና አሳብ ለማቅረብ ለሚኒስትሩ ኃላፊ ነው ።

## ምዕራፍ ፫

## የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ መቆጣጠሪያ መ/ቤት ሥልጣንና ተግባር ።

፯/ ስለሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪዎች ሥልጣንና ተግባር ።

የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ መቆጣጠሪያ መ/ቤት በትእዛዙ በ፩ኛው አንቀጽ የተመለከተውን ኃላፊነቱን ለመፈጸም የሥራ ሁኔታ ተቈጣጣሪዎች ፤

፩/ በማናቸውም የሥራ ሰዓት በቅድሚያ ሳያስታውቁ ሠራተኞች ተቀጥረው በሚሠሩበት ማናቸውም ሥፍራ ለመግባት ፤

፪/ ሕጋዊ ውሳኔዎች ሁሉ በሚገባ መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ የሚያስፈልገውን ማናቸውንም ምርመራ ፤ ሙከራ ወይም ጥያቄ ለማድረግ ፤ በተለይም በእነዚህ ብቻ ሳይወሰኑ ፤

ሀ/ የማናቸውንም ሕጋዊ ውሳኔ አፈጻጸም ስለሚመለከቱ ጉዳዮች ማንኛውንም አሠሪ ወይም ሠራተኛ ብቻውን ወይም ምስክሮች ባሉበት ለመጠየቅ ፤

ለ/ በሕጋዊ ውሳኔዎች መሠረት መኖር የሚገባቸውን ጽሑፎች ፣ መዝገቦችና ሌሎችን ሠነዶች ለመቆጣጠርና ለመገልበጥ ወይም ከእነዚህ ጽሑፎች ውስጥ ለመቅዳት ፤

ሐ/ ሠራተኞች ተቀጥረው በሚሠሩበት ሥፍራ በሕጋዊ ውሳኔዎች መሠረት ሊለጠፉ የሚገባቸው ማስታወቂያዎች መለጠፋቸውን ለማረጋገጥና ፤

መ/ ሠራተኞች ተቀጥረው በሚሠሩበት ሥፍራ የሚገኘውን ማናቸውንም ነገር በመጠኑ ወስደው በሠራተኞች ላይ ጉዳት የሚደርስ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሥልጣን ይኖራቸዋል ። ሆኖም ለዓይነት ስለሚወሰደው ነገር ለባለ ንብረቱ በቅድሚያ ሲነገረውና ራሱ ወኪል ሊወስድ አስፈላጊ የሆነው ነገር በሚወሰድበት ጊዜ በሥፍራው ለመገኘት መብት አለው ።

፰/ ስለሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪዎች የማስፈጸም ሥልጣን ።

፩/ የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪ በማናቸውም ድርጅት አጥር ግቢ ውስጥ በፋብሪካው ፤ በመኪናው ፤ በመሣሪያዎቹ ወይም በዕቃዎቹ ወይም የድርጅቱ ሥራ በሚካሄድበት ዘዴ ምክንያት ለሠራተኞቹ ጤንነትና ደኅንነት አሥጊ ሆኖ ሲያገኝ ሁኔታውን ለማሻሻል ከዚህ በታች የተመለከቱትን እርምጃዎች ይወስዳል ።

ሀ/ እንዲህ ያለውን የሥራ ሁኔታ ለማረም አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪው አሠሪውን ያዘዋል ።

www.chilot.me



ለ/ አሠሪው ትእዛዙን ከተቀበለ በኋላ ፤ በመጠነኛ ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን እርምጃ ሳይወስድ ቢቀር የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪው ፤

፩/ ለሠራተኞች ጤንነትና ደኅንነት የሚያሠጋ ወይም አደጋን የሚያስከትል የሆነው የሥራ ሁኔታ ይወገድ ዘንድ አስፈላጊው ለውጥ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲፈጸም ፤

፪/ ሁኔታው በሠራተኞች ጤንነትና ደኅንነት ላይ ወዲያውኑ አደጋ የሚያደርስ ሲሆን ግን ፤ አደጋውን ለመከላከል ማናቸውንም አስፈላጊ እርምጃ ጊዜ ሳይወስድ እንዲፈጸም ላሠሪው ትእዛዝ ይሰጣል ።

ሐ/ የሥራ ተቆጣጣሪው በቴክኒክ ወይም በሕግ ረገድ ጥርጣሬ የሚያሳድርበት ጉዳይ ሲያጋጥመው ወዲያውኑ አስፈላጊው ውሳኔ እንዲሰጥና በውሳኔውም መሠረት አስፈላጊው ትእዛዝ እንዲተላለፍ ጉዳዩን ላስተዳዳሪው ማቅረብ አለበት ።

፪/ አንድ የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪ በአንቀጽ ፺ በንዑስ አንቀጽ ፩ (ሀ) ወይም (ለ) መሠረት በሚሰጠው ትእዛዝ አሠሪው ያልተስማማ እንደሆነ ፤ ወዲያውኑ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላል ። ሆኖም በሠራተኞቹ ደኅንነት ወይም ጤንነት ላይ ወዲያውኑ አደጋ የሚያደርሰውን ሁኔታ ለመከላከል በንዑስ አንቀጽ ፩ (ለ) ፪ መሠረት የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪው የሰጠው ትእዛዝ ይግባኙ እስኪታይ ድረስ ከመፈጸም አይታገድም ።

፫/ የፍርድ ሚኒስትራችን ሕግን ተከትሎ በዚህ አዋጅ መሠረት ለፍርድ ቤቶች የሚቀርቡትን ጉዳዮች በተፋጠነና በተሟላ አኳኋን እንዲፈጸሙ ለማድረግ በፍርድ ቤቶች ውስጥ ስለ አሠሪና ሠራተኞች ጉዳይ የተለዩ ክፍሎች እንዲቋቋሙ ያደርጋል ።

፬/ የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪዎችን ተግባር ስለመወሰን ።

፩/ የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ መቆጣጠሪያ መ/ቤትና ተቆጣጣሪዎች ሥራቸውን ሁሉ ያለአድልዎ ትክክለኛ በሆነ መንገድ መሥራት አለባቸው ። ይሁን እንጂ ከሠራተኞቹና ከአሠሪዎቹ ወይም ከድርጅቶቻቸው የሚቀርቡላቸውን ተገቢ መስለው የታዩዋቸውን ምክርና አሳብ ተቀብለው ማመዛዘን ይኖርባቸዋል ።

፪/ የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪዎች በሥራ ክርክሮችና በኅብረት ክርክሮች ውስጥ በአስማሚነት ሆነ ወይም በሽምግልና መልክ በምንም ዓይነት ጣልቃ መግባት የለባቸውም ።

፫/ ማንኛውም የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪ ባለንብረት ወይም የጥቅም ተካፋይ የሆነበትን የሥራ ድርጅት እንዲቆጣጠር አይፈቀድለትም ።

፬/ ማንኛውም የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪ በዚህ ሕግ መሠረት የመቆጣጠር ተግባሩን ሲፈጽም ያገኘውን ማናቸውንም የፋብሪካ ፤ የንግድ ወይም የሴሎች የሥራ ክፍሎችን ምሥጢር በዚህ ሥራ ላይ ሳለ ወይም ከተሰናበተ በኋላ ፤ ለማንም ሰው መግለጽ የለበትም ።

፭/ ማንኛውም የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪ ስለ አንድ ጉድለት ወይም የሕግ ውሳኔዎችን ስለመተላለፍ አቤቱታ ሲደርሰው አቤቱታው ከየት እንደደረሰው ለማንም ሌላ ሰው መግለጽ አይገባውም ። በተለይም የቁጥጥር ጉብኝት የሚያደርገው ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ መቆጣጠሪያ መ/ቤት አቤቱታ ስለቀረበ መሆኑን ለአሠሪዎች ሆነ ለወኪሎቻቸው መግለጽ የለበትም ።

፮/ የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪ የመቆጣጠር ተግባሩን ለመፈጸም በአንድ ድርጅት የሥራ ቦታ ሲገኝ ፤ የሥራውን አፈጻጸም የሚያስተጓጉልበት ካልሆነ በቀር በድርጅቱ ውስጥ መገኘቱን ለአሠሪው ማስታወቅ አለበት ።

www.chilot.me



የተጠቀሰው ሕግ

ፍ.ሕ. ፲፱/በተ. የ. (፲፱፻፶፱) አን. ፪ሺ፭፻፺፭—፪ሺ፭፻፶፱ ።

ምዕራፍ ፫ ።

## ስለ ልዩ ሁኔታዎች ውሳኔ ።

### ፲፫/ አካለ መጠን ያላደረሱ ሴቶችና ወንዶች ልጆችን ስለ መቅጠር ።

፩/ ዕድሜው ከአሥራ አራት ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ልጅ የቅርብ ቤተ ሰቦቹ በሚሠሩበት ድርጅት ውስጥ ካልሆነ በቀር በኢንዱስትሪ ሥራ ድርጅት ውስጥ ሠራተኛ ሆኖ አይቀጠርም ።

፪/ ዕድሜው ከአሥራ አራት ዓመት በላይ ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ልጅ ፤

ሀ/ ከወላጆቹ አንዱ ወይም ሞግዚቱ በጽሑፍ ገልጾ ካልተስማማ በስተቀር ፤

ለ/ አደገኛ የሥራ ድርጅት ተብሎ በተመደበ ሥራ ውስጥ ፤

ሐ/ በሌሊት ሥራ ፤

ሌሊትም ሲባል ፦

፩/ ዕድሜው ከአሥራ ስድስት ዓመት በታች ለሆነና አካለ መጠን ላላደረሰ ልጅ ከምሽቱ አራት ሰዓት እስከ ንጋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ያለውን ጊዜ ፤

፪/ ዕድሜው በአሥራ ስድስትና በአሥራ ስምንት ዓመት መሐከል ለሆነ አካለ መጠን ላላደረሰ ልጅ ከምሽቱ አራት ሰዓት እስከ ንጋቱ አንድ ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ መደዳውን ከሰባት ሰዓት በላይ ማለት ነው ።

መ/ በቀን ከስምንት ሰዓት ወይም በሳምንት ከአርባ ስምንት ሰዓት የበለጠና ፤

ሠ/ በቁጥር ሥራ ወይም በመገጣጠም ሥራ መሥመር ላይ (አሲምብሊ ላይን) ተቀጥሮ እንዲሠራ አይፈቀድም ።

፫/ ዕድሜው ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች የሆነ ሠራተኛ ሁሉ ጸንተው በሚገኙ ሕጋዊ ውሳኔዎች መሠረት በግዴታ መከታተል የሚገባውን የማሠልጠኛ ትምህርት እንዲከታተል አሠሪው በቂ ጊዜ መስጠት አለበት ።

፬/ ማንኛውም አሠሪ አካለ መጠን ያላደረሱ ልጆችን ከመቅጠሩ በፊት በራሱ ወጪ አስፈላጊው የሕክምና ምርመራ እንዲሰጣቸው ማድረግ አለበት ። ከተቀጠሩም በኋላ ሚኒስትሩ የሥራውን ዓይነት በመመልከት በሚወስነው ጊዜ የሕክምና ምርመራ እንዲሰጣቸው ያደርጋል ። አካለ መጠን ያላደረሰ ማንኛውም ልጅ አካሉ ወይም አቅሙ አይፈቅድለትም ተብሎ በተወሰነ ባንድ ዓይነት ሥራ ውስጥ ተቀጥሮ እንዲሠራ ወይም ሥራውን እንዲቀጥል አይፈቀድም ።

፭/ አካለ መጠን ስላላደረሱ ልጆች አቀጣጠር በሚገባ ለመቆጣጠር እንዲቻል ማንኛውም አሠሪ የአሠሪና የሠራተኛ ጉዳይ መቆጣጠሪያ መ/ቤት አስፈላጊ ነው ሲል በሚወስነው መሠረት ተገቢውን ዝርዝር የያዘ መዝገብ መያዝ አለበት ።

፮/ ሚኒስትሩ አስፈላጊ ሲሆን ቦርዱን አማክሮ ከዚህ በላይ በአንቀጽ (፲፫) በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተመለከቱት ውሳኔዎች መፈጸማቸው እንዲቀር መፍቀድ ይችላል ።

www.chilot.me



፲፬/ ስለ ሴቶች አቀጣጠር ።

አሠሪዎች የጾታ ልዩነት ሳያደርጉ ለተመሳሳይ ሥራ እኩል ደመወዝ መክፈል አለባቸው።

ምዕራፍ ፮ ።

ስለ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ።

፲፭/ ስለ ተሻሉ የሥራ ሁኔታዎች ።

በግል የሥራ ውለታ ፤ በሠራተኛ መተዳደሪያ ደንቦች በተመዘገቡ የኅብረት ስምምነቶች፤ በብይን ወይም አሁን ጸንተው በሚገኙ ወይም ለወደፊት በሚወጡ ሌሎች ሕጋዊ ውሳኔዎች መሠረት ፤ ሠራተኞች ያገኙዋቸውን የተሻሉ የሥራ ሁኔታዎች ሁሉ ይህ አዋጅ አይቀንስባቸውም ።

፲፮/ ደንቦችን ስለ ማውጣት ።

ሚኒስትሩ ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም ደንቦችን ማውጣት ይችላል ።

፲፯/ ስለ ቅጣት ።

ይህንን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው በ፲፱፻፵፱ ዓ. ም. በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል ።

የተጠቀሰው ሕግ

የወ.መ.ሕ. ፲፯/በተ. የ. ፩ (፲፱፻፵፱) ።

፲፰/ አዋጁ ስለሚጸናበት ጊዜ ።

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ዛሬ ሚያዝያ ፳፰ ቀን ፲፱፻፶፰ ዓ. ም.

www.chilot.me



፯/ <u>የገንዘብ ዝግጅት ፡፡</u>

፩/ በሚከተለው ሁኔታ የሚሰበሰበው ገንዘብ የሚጠራቀምበት ሂሣብ ይቋቋማል ፡፡

ሀ/ ለአስተዳደሩ የሚደረገው ዳረጎት ፤ መዋጮና ስጦታ ፤

ለ/ በማናቸውም አስተዳደሩ በሚፈጽመው የሥራ ክንውን ምክንያት የሚገኝ ገቢና እንዲሁም ታሪካዊ ስፍራዎችንና ሐውልቶችን ለመጐብኘት የሚከፈለው ገንዘብ ፤

ሐ/ በጥንታዊ ታሪካዊ ቅርሶች ዲሬክተር ተዘጋጅቶ ቦርዱ በሚያጸድቀው በጀት መሠረት መንግሥት ለአስተዳደሩ የሚያደርገው ዓመታዊ የድጋፍ መዋጮ ፤

፪/ ይህ ገንዘብ የተጣለበትን ተግባርና ኃላፊነት ለመፈጸም በሚያስችለው አኳኋን ሕጋዊ በሆነ መንገድ በሚያዝበት በአስተዳደሩ ስም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም በሌላ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወክለው ባንክ ውስጥ በሚከፈት ልዩ የማጠራቀሚያ ሂሣብ ይቀመጣል ፡፡

፫/ አስተዳደሩ ስለሥራው ክንውን ሁኔታና ስለገንዘቡም ወጭና ገቢ የተጠናቀቀ የሂሣብ መዝገብ በመያዝ ፤ እያንዳንዱ የበጀት ዓመት ባለቀ በሦስት ወር ውስጥ ያለፈውን ዓመት የገንዘብ ሁኔታ የሚገልጽ ራፖር እያዘጋጀ ለቦርዱ ፤ ለዋና ኦዲተርና ለገንዘብ ሚኒስትር ያቀርባል ፡፡

፰/ <u>ደንብ ስለማውጣት ፡፡</u>

አስተዳደሩ ይህ ትእዛዝ የሚያዘውን በተሻለ መንገድ እንዲፈጸም ለማድረግ ደንብ ለማውጣት ይችላል ፡፡

፱/ ትእዛዙ የሚጸናበት ቀን ፡፡

ይህ ትእዛዝ <u>በነጋሪት ጋዜጣ</u> ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ <u>፲፩</u> ቀን <u>፲፱፻፶፰</u> ዓ. ም.

www.chilot.me



## ፳/፫ (፲፱፻፵፯) አ. ፺፬

## ስለትምህርት የገንዘብ ወጪ አወሳሰን አዋጅ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እኛ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

ለሕዝባችን ሁሉ ትምህርት በሰፊው እንዲደርሰው ሳናቋርጥ ያሰብንበት በመሆኑና ሕዝባችንም በጠቅላይ ግዛቶች ውስጥ የትምህርት ሥራ አካሄድ ተካፋይ የሚሆንበት ጊዜው በመድረሱ ፤

በሕገ መንግሥታችን በ፹፰ኛው ክፍል እንደተመለከተው የሕግ መምሪያና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቶች የመከሩበትን ተመልክተንና ፈቅደን የሚከተለውን አውጀናል ።

፩/ ይህ አዋጅ ስለትምህርት የገንዘብ ወጪ አወሳሰን የ፲፱፻፵፯ ዓ.ም. አዋጅ ተብሎ ይጠቀሳል ፤ በነጋሪት ጋዜጣ ከታተመበትም ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

፪/ በያንዳንዱ ጠቅላይ ግዛት ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት አባሎች የሚገኙበት ከዚህ በታች በ፫ኛውና በ፬ኛው ቁጥር እንደተጻፈው ሆኖ የትምህርት ቦርድ ቆሞአል ።

   ሀ/ ከጠቅላይ ግዛት የማዘጋጃ ቤት አማካሪዎች አንድ አባል ፤ እርሱም በማዘጋጃ ቤት አማካሪዎች ብቻ በምሥጢር የዕጣ ምርጫ ይመረጣል ።

   ለ/ ለሕግ መምሪያ ምክር ቤት ምርጫ በሚደረግበት አኳኋን ከጠቅላይ ግዛቱ ከያንዳንዱ አውራጃ አንድ አባል ይመረጣል ። የአመራረጡም ሥርዓት በሕግ መምሪያ ምክር ቤት እንደሚደረገው አኳኋን ይፈጸማል ። የመጀመሪያው ምርጫ ይህ አዋጅ ከሚጸናበት ቀን አንስቶ ከ፮ ወር በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ደግሞም በያመቱ በጥቅምት ፳፫ ቀን ይደረጋል ።

### የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) የእንግሊዝኛው ቅጅ «በምሥጢር በሚደረግ ምርጫ ይመረጣሉ» ይላል ።

፫/ ጠቅላይ ገዥው በሹመቱ ላይ ለጠቅላይ ግዛቱ የትምህርት ቦርድ አባል ነው ። የቦርዱም ፕሬዚዳንት እርሱ ይሆናል ። ጠቅላይ ገዥው በሌለ ጊዜ የጠቅላይ ግዛቱ ዋና ዲሬክተር ፕሬዚዳንት ይሆናል ፤ እርሱም በሌለ ጊዜ የጠቅላይ ግዛቱ ዋና ጸሐፊ ፕሬዚዳንት ይሆናል ።

፬/ የጠቅላይ ግዛቱ የትምህርት ሥራ አስኪያጅና በዋናው ከተማ ውስጥ የሚገኘው የዋናው ትምህርት ቤት ሥራ መሪ በዚህ ሥራቸው ላይ ሳሉ የጠቅላይ ግዛቱ የትምህርት ቦርድ አባሎች ይሆናሉ ።

፭/ በሥራቸው አባሎች ከሆኑት ከአገረ ገዥውና ከየትምህርት ቤቱ አባሎች በቀር ለጠቅላይ ግዛቱ የትምህርት ቦርድ አባሎች ለመሆን የሚመረጡት ሰዎች ዕድሜአቸው ፳፭ ዓመት የሞላቸውና በተወከሉበትም በጠቅላይ ግዛቱ ከአምስት ዓመት የማያንስ ጊዜ የኖሩ እንዲሆኑ ያስፈልጋል ።

### የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

የዚህ አንቀጽ የእንግሊዝኛው ቅጅ «ዕድሜያቸው ከ፳፩ ዓመት የማያንስ» ይላል ።

www.chilot.me



ለመሸጥ ፣ በውስጡም ሆነ በውጭ ያለውን መብቱን ፣ ስሙን ወይም ጥቅሙን ለማዛወር ፣ ዩኒቬርሲቲውን ሊጠቅም የሚችለውን መሣሪያዎችና ሠነዶች ሁሉ እንዲሁም በሌሎች አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች ለመሥራት ፤

መ/ ባለው ገንዘብ ወይም በችሮታ ለመተዳደሪያ የተቀበለውን ሀብት በሙሉ ወይንም በከፊል እሥራ ላይ ለማዋል ፤

ሠ/ ለዩኒቬርሲቲው አገልግሎት አስፈላጊ ወይም ምቹ ቢሆን ቤቶችን ለመሥራት ፣ በደንብ ለመያዝ ፣ ለመለወጥ ፣ ለመጠገን ፣ ሁሉንም የዩኒቬርስቲ ቤቶችና አጥር ግቢ ለማደስና ለማሻሻል ፤ ይህንን ለመሳሰለ ሥራና ለዩኒቬርስቲው ዕቃዎችና መሣሪያዎች መግገርያ ተፈላጊውን ገንዘብ ለማውጣት ፤

ረ/ የዓመቱ በጀት እስኪፈቀድ ድረስ አስፈላጊውን ወጭ ለማድረግ ፤ የተመደበውን በጀት ሳያልፍ ብዛቱ ያልተወሰነ ገንዘብ ለመበደር ፤

ሰ/ ከማንኛውም ባለሥልጣን ፣ ማኅበር ፣ የግል ድርጅት ፣ የመንግሥት ፣ የማዘጋጃ ቤት ወረዳ ወይንም ሌላ ቦታ ለዩኒቬርስቲው ሥራና ግብ ተስማሚ ለሚሆን ዓላማ በገንዘብ ረገድ ለመዋዋል ፣ ወይንም ለመስማማት ፣ ከላይ ከተጠቀሱት ከየትኛውም ክፍልና እንዲሁም ይህን ከመሳሰሉት ድርጅቶች ወይንም መሥሪያ ቤቶች መብቶችን ፣ ጥቅሞችንና ኮንሴስዮኖችን የሚያስፈልጉና ሊሠራባቸው የሚቻል ከሆነ ለማግኘት እንዲሁም እነዚህን መሰሎች በሆኑ መብቶች ፣ ጥቅሞችና ኮንሲስዮኖች መሥራትና መጠቀም ፤

ሸ/ የዩኒቬርሲቲውን ዓላማ እግቡ ለማድረስና ሥልጣኑንም በሥራ ላይ ለማዋል ጠቃሚ ወይንም አስፈላጊ መስሎ የሚታየውን ማንኛውንም ነገር መፈጸም ።

## የአስተዳደር ቦርድ ።

፩/ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አባሎች ሁነው የሚመክሩበት አንድ የአስተዳደር ቦርድ ተቋቁሞአል ።

ሀ/ የቦርዱ ኤክስ ኦፊሲዮ አባል ፤

ፕሬዚዳንቱ ፤

ለ/ የተሾሙ አባሎች ፤

ከትምህርት ፣ ከእርሻና ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከያንዳንዳቸው አንዳንድ አባልና በተጨማሪ በእኛ የተሾሙ አምስት አባሎች ፤

ሐ/ የተመረጡ አባሎች ፤

የዩኒቬርስቲ ትምህርታቸውን ጨርሰው የሚወጡት ተማሪዎች ቁጥራቸው ሁለት መቶ (፪፻) ሲሞላ ከመካከላቸው አንድ ሰው የቦርድ አባል ሊመርጡ ይችላሉ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

የእንግሊዝኛው ቅጂ «በኛ የሚመረጡ ስምንት አባሎች ---» ይላል ።

፪/ ከነዋሪ መምህራንና ሠራተኞች መካከል ከፕሬዚዳንቱ በስተቀር የቦርዱ አባል ለመሆን ሊሾም ወይም ሊመረጥ አይችልም ።

፫/ ሀ/ ቦርዱ ለሚያደርጋቸው ስብሰባዎች ሊቀ መንበር የሚሆን ከአባሎቹ መካከል አንድ ሰው ይመረጣል ።

www.chilot.me



፲፫/ ፕሬዚዳንቱ የጉባዔው ሊቀ መንበር ይሆናል ። የአካዳሚው ምክትል ፕሬዚዳንትም ም/ሊቀ መንበር ሆኖ ይሠራል ። በያመቱ መጀመሪያ ስብሰባ ላይ የጉባዔው ጸሐፊ ይመረጣል ።

፲፬/ ሀ/ ጉባዔው በየተርሙ መጀመሪያ ባሉት አራት ሳምንቶች ውስጥና ሊቀ መንበሩ በሚወስናቸው ጊዜያት ስብሰባ ያደርጋል ።

ለ/ ከሦስት የማያንሱ የጉባዔው አባሎች በጠየቁ ጊዜ ሊቀ መንበሩ ስብሰባ እንዲ ጠራ ያደርጋል ።

ሐ/ ከጉባዔው አባሎች ከአምስት እጅ ሦስት በስብሰባው ላይ ሲገኙ የስብሰባው ውሳኔ ይጸናል ።

፲፭/ ቦርዱ በሚሰጠው ጠቅላላና ልዩ ልዩ መምሪያ መሠረት ጉባዔው የሚከተሉትን ይፈጽማል ።

ሀ/ ለስብሰባው አመራር ደንብ ያወጣል ።

ለ/ በተቋቋሙት ፋኩልቲዎችና እንዲሁም ቅርንጫፎች ክፍሎችና እንስቲቲው ሽኖች ውስጥ እንዶአስፈላጊነቱ መጠን ኮርሶችንና ትምህርቶችን ይሰጣል ፤ ያጸቁማል ።

ሐ/ በዩኒቬርሲቲው ውስጥ ትምህርታቸውን ለፈጸሙ ተማሪዎች የሚሰጠውን ዲግሪ ፣ ዲፕሎምና የምስክር ወረቀት እንደየደረጃው እየወሰነ እንዲሰጥ ያደር ጋል ።

መ/ ፋኩልቲዎች ፣ የዩኒበርሲቲው ቅርንጫፍ ድርጅቶች ፣ ክፍሎችና ኢንስቲቲውሽ ኖች እንዲቋቋሙ ለቦርዱ አሳብ ማቅረብና እነዚህም የሚመሩበትን ደንብና የትምህርቱንም ደረጃ ሌላውንም ተፈላጊ ነገሮች ሁሉ ይወስናል ።

ሠ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ሆነ በውጭ አገር ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ጋር ቦርዱ በሚፈቅደው መሠረት አስፈላጊ የአካዳሚክ ስምምነቶችን ያደርጋል ።

ረ/ ቦርዱ ሲፈቅድ ማንኛውም ኢንስቲትውት የዩኒቬርሲቲው ጥገኛ ለመሆን ሲጠ ይቅ ይህንኑ ይወስናል ።

ሰ/ አስፈላጊ የሆነውን ማንኛውንም የዩኒቬርሲቲ መግቢያ ጠቅላላ ደንብ ያወጣል።

ሸ/ የፈተናን አሰጣጥ ዘዴና ሁኔቴ እንዲሁም የዲግሪን ፣ የዲፕሎምና የምስክር ወረ ቀትን ጠቅላላ ደረጃ ይወስናል ።

ቀ/ በዲስፕሊን በኩል በጠቅላላውም ሆነ በተለይ የሚቀርቡትን ችግሮች አስፈላ ጊውን እየፈጸመ ያስወግዳል ። በዲስፕሊን በኩል ጉድለት የሚገኝበት ተማሪ እንዲቀጣ ፤ ለተወሰነ ጊዜ ከትምህርት እንዲታገድ ወይም ከትምህርት ቤት እን ዲወጣ ለቦርዱ እያቀረበና እያስወሰነ አስፈላጊውን ይፈጽማል ።

በ/ በጠቅላላው በዩኒቬርሲቲው ውስጣዊ አስተዳደር ያሉትን ጠቅላላና ዝርዝር ጉዳዮች እያጠና ውሳኔ ይሰጣል ። አካዳሚክ ነክ በሆኑ ጉዳዮች በዩኒቬርሲቲው አባሎችና ልዩ ልዩ ድርጅቶች የሚቀርበውን ክስ ይሰማል ።

፲፮/ ሀ/ ማንኛውም የጉባኤው ውሳኔ በተሰበሰቡት አባሎች ድምፅ ብልጫ ይወሰናል ። ሁለቱም ወገን እኩል ሲሆን ግን የሊቀ መንበሩ ተጨማሪ ድምፅ የሚደገፈው አሳብ ይጸናል ።

ለ/ የምክር ቤቱ ውሳኔ በቃለ ጉባዔው መዝገብ እየሰፈረ ሊቀ መንበሩና ጸሐፊው ይፈርሙበታል ።

www.chilot.me



## የዩኒቨርሲቲው ቻንስለር ።

፲፯/ ሀ/ የዩኒቨርሲቲው ቻንስለር እኛ ራሳችን በማንሆንበት ጊዜ ተተኪ የሚሆን አንድ ቻንስለር በኛ ይሾማል ።

ለ/ ቻንስለሩ ለሥራው በማይገኝበት ጊዜ የቻንስለርነቱን ሥራ የሚያከናውን አንድ ምክትል ቻንስለር በኛ ይሾማል ።

፲፰/ ቻንስለሩ ዲግሪ ፣ ዲፕሎምና የምስክር ወረቀት በሚሰጥበትና በማንኛውም የምረቃ ቀን በዩኒቨርሲቲው ተገኝቶ ዲግሪዎችንና ሰርቲፊኬቶችን ይሰጣል ።

፲፱/ በኛ የሚሾመው ፕሬዚዳንት የሚሠራበትን ሁኔታና የሚቀጠርበትን ውል ቦርዱ ይወስናል ።

፳/ ሀ/ ፕሬዚዳንቱ የዩኒቨርሲቲው ሥራ መሪና አስፈጻሚ ይሆናል ።

ለ/ የዩኒቨርስቲው መምህራን ና ሠራተኞች ከፕሬዚዳንቱ ሥር ሆነው እርሱ ወይንም ኃላፊነት የሰጣቸው ሌሎች ሹማምንት የሚያዋጡትን መምሪያና ትእዛዝ እየተቀበሉ ይፈጽማሉ ።

፳፩/ ፕሬዚዳንቱ ከጉባኤው ጋር እየተመካከረና ቦርዱ በሚያጸድቀው መሠረት መምህራንና ሠራተኞች የሚቀጠሩበትን ደንብና የሥራቸውንም ሁኔታ ይወስናል ።

፳፪/ ሀ/ ፕሬዚዳንቱ ከጉባኤው ጋር እየተመካከረ የዩኒቨርሲቲውን ያመት በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል ።

የዩኒቨርሲቲው ባጀት ለቦርዱ የሚቀርበው ባጀቱ እሥራ ላይ ከሚውልበት ዓመት ቀደም ብሎ ከጥር ፴ ቀን በፊት መሆን አለበት ።

ለ/ የዩኒቨርሲቲውን በጀት በተፈቀደው መሠረት እንዲሠራበት ለማድረግ ሥልጣን አለው ።

ሐ/ ፕሬዚዳንቱ የዩኒቨርሲቲውን የዓመት የሥራ እርምጃ ሪፖርር ለቦርዱ ያቀርባል ።

መ/ ፕሬዚዳንቱ በየዓመቱ በቦርዱ በሚመረጡት ኦዲተሮች የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ እንዲመረመር ያደርጋል ።

## ምክትል ፕሬዚዳንቶች ።

፳፫/ ሀ/ ቦርዱ ለምክትል ፕሬዚዳንትነት በፕሬዚዳንቱ ከሚቀርቡለት ዕጩዎች ሁለት ሰዎች መርጦ ለኛ አቅርቦ እንዲሾሙ ያደርጋል ።

ለ/ አንዱ ምክትል ፕሬዚዳንት ስለአካዳሚክ ጉዳይ ፣ ሁለተኛው ደግሞ ስለአስተዳደርና ስለልማት ጉዳይ ኃላፊዎች ይሆናሉ ።

፳፬/ ፕሬዚዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ ወይም ፕሬዚዳንቱ በማናቸውም ምክንያት ሥራውን ለማካሄድ በማይችልበት ጊዜ የአካዳሚኩ ምክትል ፕሬዚዳንት ተተክቶ የፕሬዚዳንትነቱን ሥራ ይሠራል ።

## የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ድርጅት አቋም ።

፳፭/ ዩኒቨርሲቲው ፋኩልቲዎች ፣ ሴንተሮች ፣ ልዩ ልዩ ድርጅቶችና ኢንስቲቲውሽኖች ይኖሩታል ።

www.chilot.me



ሀ/ ሊቀ መንበር የሚሆነው የፋኩልቲው ዲን ።

ለ/ በፋኩልቲው ውስጥ ሙሉ ጊዜያቸውን በሚያስተምሩ አባሎች የሚመረጡ አምስት መምህራን ።

፴/ እያንዳንዱ የአካዳሚክ ኮሚሽን ከዚህ የሚከተሉትን ሥራዎች ይፈጽማል ፡—

ሀ/ እያንዳንዱ ፋኩልቲ በክፍሉ የሚሰጡትን የትምህርት ፕሮግራሞች እያዘ ጋጀ ይወስናል ። እንዲሁም የዩኒቨርሲቲውን ጠቅላላ አመራር ሳያቃውስ አስፈላጊ ሲሆን ማናቸውንም የፕሮግራም መለዋወጥ ሊፈጽም ይችላል።

ለ/ እያንዳንዱ ፋኩልቲ በክፍሉ ውስጥ የሚሰጠውን ዓመታዊ ወይም የመጨ ረሻ ወይም ሌሎች ፈተናዎች ያዘጋጃል ።

ሐ/ ዲግሪ ፣ ዲፕሎም ወይም ሌላ ዓይነት የምስክር ወረቀት የሚገባቸውን ተማ ሪዎችና የሚሰጣቸውን ማዕርግ ለይቶ ለጉባኤው ያቀርባል ።

መ/ ተማሪዎችን ወደ ከፍተኛ ክፍል ለማዛወር የሚያስፈልገውን ለጉባዔው ያቀርባል ።

ሠ/ ፋኩልቲውን የሚመለከት ማንኛውንም የአካዳሚ ጉዳይ እየተከታተለ ይፈጽማል ።

፴፩/ ሀ/ በያንዳንዱ ተርም እያንዳንዱ የአካዳሚክ ኮሚሽን ከአምስት ያላነሱ ስብ ሰባዎች ማድረግ አለበት ።

ለ/ ስብሰባዎችም የሚደረጉት ፣

፩/ የተርሙ ሥራ በተጀመረ በሁለት (፪) ሳምንቶች ውስጥ ፤

፪/ ተማሪዎቹን ለማስመረቅ ከሚሰጠው የመጨረሻ ፈተና በፊት ባሉ አሥር (፲) ቀናት ውስጥ በዚህ ስብሰባ ፈተናውን የሚወስዱ ተማሪ ዎች ይመረጣሉ ፤ የሚሰጠውም ፈተና ይወሰናል ፤

፫/ የመጨረሻው ፈተና ከተሰጠ በኋላ በፈተናው ያለፉት ተማሪዎች ዝርዝር ይወሰናል ፤

፬/ የመጨረሻው ፈተና ከመሰጠቱ ከሰባት (፯) ቀን በፊት ፈተናው ይወ ሰናል ፤

፭/ ፈተናው ከተሰጠና ወረቀቶቹ ከታረሙ በኋላ ቀጥሎ ምን ዓይነት አመ ራር እንደሚወሰድ ይወሰናል ።

ሐ/ የአካዳሚክ ኮሚሽን ሊቀ መንበር አስፈላጊ መስሎ ሲታየው በማናቸውም ጊዜ አባሎቹ እንዲሰበሰቡ ማድረግ ይችላል ። እንዲሁም ኮሚሽኑ አባሎቹ ከሦስት ያላነሱ ሲጠይቁ ሊቀ መንበሩ ስብሰባውን ይጠራል ።

መ/ በማንኛውም ስብሰባ ቢሆን የአካዳሚኩ ኮሚሽን የሚያደርገው ውሳኔ የሚ ጸናው የተሰበሰቡት አባሎች የኮሚሽኑ ሦስት አምስተኛ ሲሆኑ ነው ።

ሠ/ የአካዴሚኩ ኮሚሽን የሚያደርገው ውሣኔ የሚጸናው በድምፅ ብልጫ ነው። ሁለቱም ወገኖች እኩል ሲሆን የሊቀ መንበሩ ተጨማሪ ድምፅ የሚደግፈው ወገን ይጸናል ።

ረ/ የአካዴሚክ ኮሚሽኑ የሚያደርገው ማንኛውም ውሳኔ በቃለ ጉባኤው መዝ ገብ ሠፍሮ ሊቀ መንበሩና ጸሐፊው ይፈርሙበታል ።

፴፪/ ይህ ቻርተር ከቦርዱ አባሎች ከሦስቱ እጅ ሁለቱ እንዲሻሻል ሲስማሙ ቦርዱ ይህንኑ ለኛ አቅርቦ አስፈላጊው መሻሻል ይደረጋል ።

አዲስ አበባ የካቲት ፳፭ ቀን ፲፱፻፶ ዓ. ም.

www.chilot.me



፳፯/፲፱ (፲፱፻፷) ት. ፶፪

## የአሥመራ ዩኒቨርሲቲ ቻርተር ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

የአሥመራ ዩኒቨርሲቲ ታህሣሥ ፲፫ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ.ም. በ «ፒያ ማትሬስ ኔግሪሺያ» መንፈሳዊ ድርጅት ተቋቁሞ ጥር ፲፱ ቀን ፲፱፻፷ ዓ.ም. በኛ በኦፊሴል ስለተመረቀ እና ፡—

በትምህርት ረገድ መንግሥታችን የሚያከናውናቸውን ሥራዎች ለማሟላት የግል ድርጅቶች ወይም ሰዎች በሥራው ተካፋይ እንዲሆኑ ማበረታታትና ማነቃቃት ተግባራችን ስለሆነ ፤ ይህ ቻርተር ከዚህ በታች በተዘረዘረው አኳኋን እንዲሠራበት ፈቅደናል ።

፩/ አጭር አርእስት ።

ይህ ቻርተር «የአሥመራ ዩኒቨርሲቲ ቻርተር» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

፪/ ትርጓሜ ።

በዚህ ቻርተር ተባእታይ ተውላጠ ስም ለሁለቱም ጾታዎች ማለት ለወንድም ለሴትም የሚያገለግል ሆኖ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካላስፈለገ በቀር ፤

፩/ «የአካዳሚክ ባለሥልጣኖች» ማለት በዚህ ቻርተር በአንቀጽ ፬ ውስጥ የተዘረዘሩት የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚ ባለሥልጣኖች ማለት ነው ።

፪/ «የአካዳሚክ ኮሚሽን» ማለት በዚህ ቻርተር በአንቀጽ ፲፫ መሠረት የተቋቋመው የዩኒቨርሲቲው የእያንዳንዱ ክፍል (ፋኩልቲ) ወይም ኮሌጅ የአካዳሚክ ኮሚሽን ማለት ነው ።

፫/ «ቦርድ» ማለት በዚህ ቻርተር በአንቀጽ ፲፫ መሠረት የተቋቋመው የዩኒቨርሲቲው የአስተዳደር ቦርድ ማለት ነው ።

፬/ «መንፈሳዊ ድርጅት» ማለት የ«ፒያ ማትሬስ ኔግሪሺያ መንፈሳዊ ድርጅት» ማለት ነው ።

፭/ «መዋጮ ከፋይ አባሎች» ማለት ከየዓመቱ ከሃምሳ ሺህ የኢትዮጵያ ብር ያላነሰ ገንዘብ ለዩኒቨርሲቲው ስጦታ የሚያደርጉ የግል ድርጅቶች ወይም ሰዎች ማለት ነው ።

፮/ «የፋኩልቲው ምክር ቤት» ማለት በዚህ ቻርተር አንቀጽ ፲፭ መሠረት የተቋቋመ የአሥመራ ዩኒቨርሲቲ የፋኩልቲ ምክር ቤት ማለት ነው ።

፯/ «የሙሉ ጊዜ መምህራን» የሚባሉት በዩኒቨርሲቲው ከተቀጠሩት መምህራን መካከል ከዩኒቨርሲቲው ሥራ ሌላ የማይሠሩ የሙሉ ጊዜ መምህራን ማለት ነው።

፰/ «ሚኒስትር» እና «ሚኒስቴር» ማለት የትምህርትና የሥነ ጥበብ ሚኒስትርና ሚኒስቴር ማለት ነው ።

፱/ «ፕሬዚዴንት» ማለት የአሥመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዴንት ማለት ነው ።

፲/ «የፕሬዚዴንት ምክር ቤት» ማለት በዚህ ቻርተር አንቀጽ ፲፯ መሠረት የተቋቋመ የፕሬዚዴንቱ ምክር ቤት ማለት ነው ።

www.chilot.me



፲፩/ «ሠራተኞች» የሚለው ቃል መምህራንንና የአስተዳደር ሠራተኞችን ይጨምራል።

፲፪/ «መምህራን» ማለት ፕሮፌሴሮችን ፣ ተባባሪ ፕሮፌሰሮችን ፣ ረዳት ፕሮፌሰሮችን፣ ሌክቸረርስን ፣ ረዳት ሌክቸረርስን ፣ ጐብኚ ፕሮፌሰሮችን ፣ ተጋባዥ ሌክቸረርስን ፣ የከፍተኛ ምርመራ ጥናት ሠራተኞችንና በአሥመራ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በማስተማር ላይ የሚገኙትን ሁሉ ይጨምራል ።

፲፫/ «ዩኒቨርሲቲ» ማለት በኢትዮጵያ የአሥመራ ዩኒቨርሲቲ ማለት ነው ።

፲፬/ «ም/ፕሬዚዴንት» ማለት በዚህ ቻርተር አንቀጽ ፲፭ መሠረት የሚሾም የዩኒቨርሲቲው ም/ፕሬዚዴንት ማለት ነው ።

## ፫/ የዩኒቨርሲቲው መቋቋም ።

የአሥመራ ዩኒቨርሲቲ በስሙና በሥራው እንደ አንድ አካል ተጠሪ ሆኖ በመቋቋም ዩኒቨርሲቲው እንደሚፈቅደው እየተለወጠ ወይም እየተሻሻለ የሚሠራበት አንድ የታወቀ ማኅተም ይዞ ዘመን ሳይወሰንበት በዚህ ቻርተር በተመለከተው መሠረት ሥራውን እንዲያካሂድ ፈቅደናል ።

## ፬/ ተግባርና ዓላማ ።

፩/ ዩኒቨርሲቲው የተቋቋመው ለትምህርት ዕድገት ለመርዳትና በሊበራል ፣ በሳይንቲፊክና በአስተዳደር ሞያዎች የአካዳሚክ ዲግሪ እንዲያገኙ ወጣቶችን ዝግጁ ለማድረግ ነው ።

፪/ ዩኒቨርሲቲው የተቋቋመው በመሠረቱ ለኢትዮጵያ ተማሪዎች ቢሆንም የሃይማኖት ፣ የዘር ወይም የጐሣ ልዩነት ሳይኖር አስፈላጊው ችሎታ ላላቸው ለማናቸውም ዜጋ ለወንዶችም ሆነ ለሴቶች ተማሪዎች ክፍት ነው ።

## ፭/ ተግባርና ሥልጣን ።

የዩኒቨርሲቲው ሕጋዊ አካል ያለው ሆኖ ከጠባዩ ጋር የሚስማሙት መብቶችና ግዴታዎች ሁሉ አሉት ። በነዚሁም መብቶችና ግዴታዎች ሥልጣን ያለው የአስተዳደሩ ክፍል በአንድነትና በነጠላ ይሠራባቸዋል ።

ዩኒቨርሲቲው ከዚህ በላይ በተመለከተው ብቻ ሳይወሰን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የኢትዮጵያ ሕጎችና ይህንን ቻርተር መሠረት በማድረግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተግባሮችና ሥልጣኖች ይኖሩታል ። እነዚህም ፦

፩/ በትምህርት የሚገኙ የአካዳሚ የምስክር ወረቀቶች ፣ ዲፕሎማዎችና ዲግሪዎች ወይም የክብር ዲግሪ ለመስጠት ፤

፪/ በአስተዳደር ቦርድ ዘንድ አስፈላጊ ሆነው የሚገኙትን ፋኩልቲዎች ፣ ኮሌጆች፣ ትምህርት ቤቶችና ሌሎችንም የትምህርት ድርጅቶች ለመክፈት ፤

፫/ በጠቅላላና በተለይ የሚሠራባቸውን ሥርዓቶችና ደንቦች ለመወሰን ፤

፬/ አስፈላጊ መስሎ እንደታየው የሚዳሰስም ፣ ሆነ የማይዳሰስ የሚንቀሳቀስ ሆነ የማይንቀሳቀስ ማናቸውንም ዓይነት ሀብት በዕርዳታ ፣ በማዛወር ፣ በግዢ ፣ በኪራይ ፣ በስጦታ ፣ በክፍያ ፣ በውርስ ፣ ወይም በሌላ አኳኋን ለማግኘት ለመውሰድና ለመቀበል ፤

፭/ ሀብቱን በሙሉም ሆነ በከፊል ፣ እንዲሁም ማናቸውም መብት የባለቤትነት ማስረጃ ወይም ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን ጥቅም ለመሸጥ ፣ ለመለወጥ ፣ ለማ

www.chilot.me



ከራየትና ፤ በዋስትና ለማስያዝ ወይም በሌላ አኳኋን እንዳስፈለገው ለማዋል ፤ ዋጋ ያላቸውን ሠነዶች ለማዘጋጀት ፤ ለመፈጸምና ይህንኑ በሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ የሆኑትን ሥራዎችና ሌሎችንም ነገሮች ሁሉ ለማከናወን ፤

፯/ ያለውን ወይም በአደራ ስም የያዘውን ገንዘብ ወይም በከፊል በሚጠቅም ሥራ ላይ ለማዋል ወይም ለማበደር ፤

፰/ የዩኒቨርሲቲውን መደበኛና ካፒታል ወጪ ለማስገኘት አስፈላጊ የሆነውን ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለመበደር፤

፱/ የዩኒቨርሲቲውን ዓላማና ተግባር ለመፈጸም ከሚረዳ ከማናቸውም ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት ከተሰጠው ሰው ወይም ሰዎች እንደዚሁም የመንግሥትም ሆነ የግል ከማንኛውም ባለሥልጣን ጋር ኮንትራት ለማድረግ ወይም ማናቸውንም ስምምነት ለመዋዋል ፤

፲/ የዩኒቨርሲቲውን ተግባርና ዓላማ ለመፈጸምና በሥልጣኑም ለመሥራት የሚያስፈልጉትን ወይም የሚረዱትን ሌሎች ሥራዎች ሁሉ ለማከናወን ።

፮/ የሚኒስትሩ ኃላፊነት ።

ሚኒስትሩ በመላ ኢትዮጵያ ለትምህርት ሥራ አመራር በጠቅላላው ኃላፊ በመሆኑ የዩኒቨርሲቲውን ተግባርና ሥራ ለመቆጣጠር ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ብቻ ላይ ወሰን በተለይም ፡—

፩/ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ስለሚሰጠው የትምህርት ካሪኩለም ሚኒስትሩ ያቋቋመው የትምህርት ደረጃ መጠበቁንና መፈጸሙን ፤

፪/ የአካዳሚ የምስክር ወረቀቶችን ፤ ዲፕሎማዎችንና ዲግሪዎችን ለመስጠት ሚኒስትሩ ያቋቋመው የትምህርት ደረጃ መጠበቁንና መፈጸሙን ፤

፫/ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ለዩኒቨርሲቲው መምህርነት ሚኒስትሩ የመደበውን የትምህርት ደረጃና ችሎታ የፈጸሙ መሆናቸውን ፤

፬/ ዩኒቨርሲቲው ተማሪዎችን የሚቀበልበት የትምህርት ደረጃ በኢትዮጵያ ውስጥ ሌሎች ተመሳሳይ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን የሚቀበሉበትን የትምህርት ደረጃ የተከተለ መሆኑን ለመቆጣጠር ፤

፭/ ዩኒቨርሲቲው የሚቀበለው የትምህርት ዋጋ ሚኒስትሩ ለአገሪቱ ከመደበው በላይ እንዳይሆን ለመቆጣጠር ፤ ሥልጣንና ኃላፊነት አለው ።

፯/ የአስተዳደር አቋሞች ።

በዩኒቨርሲቲው የአስተዳደር አቋም ውስጥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሰዎችና አካሎች ይገኙበታል ።

፩/ ሰዎች ፤

ሀ/ ቻንስለሩ

ለ/ ም/ቻንስለሩ

ሐ/ ፕሬዚዴንቱ

መ/ ም/ፕሬዚዴንቶች

ሠ/ የፋኩልቲና የኮሌጅ ዲኖች ፤

www.chilot.me



፪/ አካሎች ፣

ሀ/ የአስተዳደር ቦርድ

ለ/ የፋኩልቲ ምክር ቤት

ሐ/ የአካዳሚ ኮሚሽን

መ/ የፕሬዚዴንቱ ምክር ቤት ፤

፰/ ቻንስለር ፣ የቻንስለሩ ሥልጣን ።

፩/ የዩኒቨርሲቲው ቻንስለር እኛ ራሳችን በማንሆንበት ጊዜ ፣ ተተኪ የሚሆን አንድ ቻንስለር በኛ ይሾማል ፤

፪/ ቻንስለሩ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ሥልጣኖች ይኖሩታል ፤

ሀ/ ዲግሪ ፣ ዲፕሎማና የምስክር ወረቀት በሚሰጥበትና በማናቸውም የምረቃ ቀን በዩኒቨርሲቲው ተገኝቶ ዲግሪዎችን ለመስጠት ፤

ለ/ ፋኩልቲዎች ፣ ኮሌጆች ፣ ትምህርት ቤቶችና የትምህርት ድርጅቶች እንዲቋቋሙ ወይም እንዲዘጉ ለመፍቀድ ፤

ሐ/ የዩኒቨርሲቲውን ፕሬዚዴንት ሹመት ለመፍቀድ ፤

መ/ ለአስተዳደር ቦርድ ሁለት አባሎች ለመሾም ፤

፱/ ምክትል ቻንስለር ፣ የምክትል ቻንስለሩ ተግባርና ኃላፊነት ።

፩/ ለመንፈሳዊ ድርጅት የበላይ ኃላፊ የሚሆን አንድ ም/ቻንስለር ይኖራል ።

፪/ ምክትል ቻንስለሩ ከዚህ በታች ያለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል ።

ሀ/ ቻንስለሩን አስፈቅዶ ፕሬዚዴንቱን ለመሾም ፤

ለ/ ልዩ ልዩ ዲኖችን ለመሾም ፤

ሐ/ ቻንስለሩን አስፈቅዶ ፋኩልቲዎች ፣ ኮሌጆች ፣ ትምህርት ቤቶችንና የትምህርት ድርጅቶች እንዲቋቋሙ ወይም እንዲዘጉ ለመፍቀድ ፤

መ/ የአስተዳደር ሹማምንቶችን ሹመት ለመፍቀድ እና ፤

ሠ/ በቦርዱ አሳሳቢነት በዓመቱ በጀት ውስጥ ያልተመደበውን ድንገተኛ ወጪ ለመፍቀድ ።

፲/ ፕሬዚዴንት ፣ የፕሬዚዴንቱ ሥልጣን ።

፩/ ቻንስለሩን አስፈቅዶ በምክትል ቻንስለሩ የሚሾም አንድ የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዴንት ይኖራል ። ፕሬዚዴንቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ሕጋዊና መደበኛ መኖሪያ ያለው መሆን አለበት ።

፪/ ፕሬዚዳንቱ የዩኒቨርሲቲው የበላይ ሥራ አስፈጻሚ በመሆኑ የዩኒቨርሲቲውን ሥራ በሚገባና በተሟላ አኳኋን ለመፈጸም ኃላፊ ይሆናል ።

፫/ የዩኒቨርሲቲው ሠራተኞችና ተማሪዎች ሁሉ የፕሬዚዴንቱ ታዛዦች ስለሆኑ በቀጥታ በርሱ ወይም ሥልጣን በሰጣቸው ሠራተኞች አማካይነት የሚሰጣቸውን መምሪያና ትእዛዝ መፈጸም አለባቸው ።

www.chilot.me



፬/ ከዚህ በላይ በክፍል (፫) ከተዘረዘሩት ሥልጣኖች በቀር ፕሬዚዳንቱ የሚከተለው ሥልጣን አለው ።

ሀ/ የፋኩልቲውን ምክር ቤት አስፈቅዶ ሁለቱን ምክትል ፕሬዚዴንቶች ለመ ሾም ፤

ለ/ ምክትሉን ቻንስለር አስፈቅዶ የአስተዳደር ሹማምንቶችን ሁሉ ለመሾም ፤

ሐ/ በምክትሉ ቻንስለር የሚሾሙትን ዲኖች መርጦ ለማቅረብ ፤

፭/ ምክትል ፕሬዚዳንቶች የአስተዳደር ሹማምንቶችና ዲኖች ፕሬዚዳንቱ እስከፈቀደ ድረስ በሥራቸው ላይ ይቆያሉ ።

፲፩/ ም/ፕሬዚዴንቶች ፤ የም/ፕሬዚዴንቶች ኃላፊነት ።

፩/ በዚህ ቻርተር አንቀጽ ፲ ክፍል (፬) መሠረት የሚሾሙ የዩኒቨርሲቲው ሁለት ምክትል ፕሬዚዴንቶች ይኖራሉ ።

፪/ አንዱ ምክትል ፕሬዚዴንት ለአካዳሚክ ጉዳይ ኃላፊ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ምልክት ፕሬዚዴንት ለአስተዳደሩ ፤ ለገንዘብ ጉዳይና ለሂሳብ ቁጥጥሩ ኃላፊ ይሆናል ።

፫/ ፕሬዚዳንቱ በማይኖርበት ወይም ፕሬዚዳንቱ በማናቸውም ምክንያት ሥራውን ለማካሄድ በማይችልበት ጊዜ የአካዳሚኩ ምክትል ፕሬዚዳንት ተተክቶ የፕሬዚዴ ንቱን ሥራ ይሠራል ።

፲፪/ ዲኖች ፤ የዲኖች ኃላፊነት ።

፩/ በዚህ ቻርተር በአንቀጽ ፱ በክፍል (፪) (ለ) በተጻፈው መሠረት የሚሾም የፋኩሊቲ ወይም የኮሌጅ የበላይ ኃላፊ የሚሆን አንድ ዲን ይኖራል ።

፪/ እያንዳንዱ ዲን የየፋኩልቲውን ወይም የየኮሌጁን ደንብ መሠረት በማድረግ ፋኩልቲውን ወይም ኮሌጁን ለሚመለከቱ የአካዳሚክና የሥነ ሥርዓት ጉዳዮች ኃላፊ ይሆናል ።

፲፫/ የአስተዳደር ቦርድ ፤ የአስተዳደሩ ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት ።

፩/ የአስተዳደር ቦርድ ቀጥሎ የተዘረዘሩት አባሎች ይኖሩታል ።

ሀ/ በቻንስለሩ የሚሾሙ ሁለት አባሎች ፤

ለ/ የትምህርት ሚኒስትር ወይም ከሚኒስትሩ የሚወከል ፤

ሐ/ በመንፈሳዊ ድርጅት የሚሾሙ አምስት አባሎች ፤

መ/ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዴንት ፤

ሠ/ ሁለቱ ምክትል ፕሬዚዳንቶች ፤

ረ/ ለሁለት ዓመት ጊዜ እንዲያገለግል በፋኩልቲው ምክር ቤት የተመረጠ አንድ አባል ፤

ሰ/ ለሁለት ዓመት ጊዜ እንዲያገለግሉ ቻንስለሩን አስፈቅዶ ከመዋጮ ከፋዮች መካከል ምክትል ቻንስለሩ የመረጣቸው ሁለት አባሎች ፤

፪/ ሀ/ የቦርዱ አባሎች በቦርዱ ስብሰባ ሊቀ መንበር ሆኖ የሚሠራ ከአባሎቹ መካ ከል አንድ ሊቀ መንበር ይመርጣሉ ፤

ለ/ በማናቸውም የቦርዱ ስብሰባ ሊቀ መንበሩ በሌለ ጊዜ በስብሰባው የተገኙት አባሎች የስብሰባው ሊቀ መንበር ሆኖ የሚሠራ ከአባሎቹ መካከል አንድ አባል ይመርጣሉ ፤

www.chilot.me



ሐ/ የእያንዳንዱ ፋኩልቲና ኮሌጆች ፡ ዲኖች ፤

መ/ የፋኩልቲው ክፍል ሆነው ያልተቋቋሙት ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ድርጅቶች ኃላፊዎች ፤

ሠ/ በየአካዳሚክ ኮሚሽኖቻቸው የተመረጡ ከእያንዳንዱ ፋኩልቲና ኮሌጅ ሁለት አባሎች ፤

፪/ ሀ/ ፕሬዚዳንት የምክር ቤቱ ሊቀ መንበር ሆኖ ይሠራል ። የአካዳሚኩ ምክትል ፕሬዚዴንት ደግሞ የምክር ቤቱ ም/ሊቀ መንበር ሆኖ ይሠራል ።

ለ/ ምክር ቤቱ በዓመት ሁለት ጊዜና ሊቀ መንበሩ በሚወስነው በሌላም ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደረጋል ።

ሐ/ ከፋኩልቲው ምክር ቤት ከሦስት የማያንሱ አባሎች ስብሰባ እንዲደረግ ከጠየቁ ሊቀ መንበሩ ስብሰባ እንዲደረግ ጥሪ ማድረግ አለበት ።

፫/ ከቦርዱ በሚሰጠው ጠቅላላ ፖሊስና መምሪያ እንደዚሁም በዚህ ቻርተር የተጸፈውን መሠረት በማድረግ የፋኩልቲው ምክር ቤት ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ለመፈጸም ተግባርና ሥልጣን ይኖረዋል ።

ሀ/ የእያንዳንዱን ፋኩልቲ የትምህርት መስጫ ጊዜ ለመመርመር ፤ ለማስተባበርና የዩኒቨርሲቲውን ጠቅላላ የትምህርት መስጫ ጊዜ ለመወሰን ፤

ለ/ ልዩ ልዩ የምስክር ወረቀቶችን ፤ ዲፕሎማዎችና ዲግሪዎችን ለማግኘት የሚያስችለውን የጥናት ፕላን ለመፍቀድና በትምህርት የሚገኘውን ስለ ክብር ዲግሪ የሚሰጥበትን ለመወሰን ፤

ሐ/ ስለትምህርት አሰጣጥና ሥነ ሥርዓት ጉዳዮች ውሳኔ ለማድረግ ፤

መ/ ፕሬዚዳንቱ ለሚያቀርብለት ጉዳይ አስተያየት ለመስጠት ፤

ሠ/ የምክትል ፕሬዚዴንቶችን ሹመት ለመፍቀድና የፕሬዚዴንቱ ምክር ቤት አሳብ ሲያቀርብ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በአካዳሚ ደረጃ የሚሰጠውን እድገት ለመፍቀድ ፤

ረ/ በየሁለት ዓመት ለቦርዱ አንድ አባል ለመምረጥ ፤

ሰ/ ስለዩኒቨርሲቲው መልካም አስተዳደር በሚወጡት ጠቅላላና ልዩ ደንቦች በተሰጠው በማናቸውም ሥልጣን ለመሥራት ፤

፲፩/ የአካዳሚክ ኮሚሽንስ ፡ ተግባራቸውና ሥልጣናቸው ።

፩/ እያንዳንዱ ፋኩልቲ ወይም ኮሌጅ አንድ የአካዳሚ ኮሚሽን ይኖረዋል ።

፪/ የአካዳሚኩ ኮሚሽን ከዚህ የሚከተሉት አባሎች ይኖሩታል ።

ሀ/ የኮሚሽኑ ሊቀ መንበር የሚሆነው የፋኩልቲው ወይም የኮሌጁ ዲን ፤

ለ/ ፋኩልቲውን ወይም የኮሌጁን በመምህርነት ሙሉ ጊዜ የሚያገለግሉ ፕሮፌሰሮች ፤ ተባባሪ ፕሮፌሰሮች እና ረዳት ፕሮፌሰሮች ፤

፫/ ሀ/ እያንዳንዱ የአካዳሚክ ኮሚሽን በዓመት አራት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል ።

ለ/ ሊቀ መንበሩ አስፈላጊ መስሎ ከታየው የአካዳሚኩ ኮሚሽን በማናቸውም ጊዜ እንዲሰበሰብ ጥሪ ማድረግ ይችላል ። እንደዚሁም ከአካዳሚኩ ኮሚሽን ሦስት አባሎች ከጠየቁ ስብሰባ እንዲደረግ ጥሪ ማድረግ አለበት ።

፬/ የአካዳሚኩ ኮሚሽን የሚከተለው ተግባርና ሥልጣን ይኖረዋል ።

www.chilot.me



ሀ/ በፋኩልቲው ወይም በኮሌጁ የሚሰጡትን የምስክር ወረቀቶች ዲፕሎማዎችና ዲግሪዎች ለማግኘት የሚያስፈልገውን የጥናት ፕሮግራምና ልዩ ልዩ ትምህርት የሚሰጥበትን የትምህርት ሥሌዳ ማዘጋጀት ፤

ለ/ የትምህርት አሰጣጥን ዘዴ ለማሻሻል አስፈላጊውን አሳብ ማቅረብ ፤

ሐ/ የፋኩልቲውን ወይም የኮሌጁን የአካዳሚክና የሥነ ሥርዓት ጠባይ በሚመለከቱ ጉዳዮች ውሳኔ መስጠት ፤

መ/ ዩኒቬርሲቲው ለፋኩልቲው ወይም ለኮሌጁ የሚሾማቸውን የደረጃ እድገት የሚሰጣቸውን ወይም ከሥራ የሚያሰናብታቸውን መምህራን ስም ለፕሬዚዳንቱ ማቅረብ ፤

ሠ/ ከሌሎቹ ዩኒቬርሲቲዎች ወይም የትምህርት ድርጅቶች ተማሪዎችን የሚቀበልበትን የትምህርት ደረጃ መወሰን እና ፤

ረ/ ዲኑ በሚያቀርብለት በማናቸውም ጉዳይ ላይ አስተያየት መስጠት ፤

## ፲፯/ የፕሬዚዴንቱ ምክር ቤት ፤ ተግባሩና ሥልጣኑ ።

፩/ የፕሬዚዴንቱ ምክር ቤት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አባሎች ይኖሩታል ።

ሀ/ የምክር ቤቱ ሊቀመንበር የሚሆነው ፕሬዚዴንቱ ፤

ለ/ ምክትል ፕሬዚዴንቶች ፤

ሐ/ ዲኖች ፤

መ/ በቀዋሚነት ወይም በጊዜያዊነት በፕሬዚዳንቱ የሚሾሙ ሌሎች ሹማምንቶች ፤

፪/ ሀ/ የፕሬዚዴንቱ ምክር ቤት በየሁለት ወር መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል ።

ለ/ ሊቀ መንበሩ አስፈላጊ መስሎ ከታየው ስብሰባ እንዲደረግ በማናቸውም ጊዜ ጥሪ ለማድረግ ይችላል ። እንደዚሁም ከፕሬዚዴንቱ ምክር ቤት ሦስት አባሎች ከጠየቁ ስብሰባ እንዲደረግ ጥሪ ማድረግ አለበት ።

፫/ የፕሬዚዴንቱ ምክር ቤት የዩኒቬርሲቲውን ሥራ በማካሄድ ረገድ የፕሬዚዴንቱ ረዳት ከመሆኑም በላይ የቦርዱን ፤ የፋኩሊቲውን ምክር ቤትና የአካዳሚኩ ኮሚሺን ውሳኔዎችን ለማስተባበርና ለማስፈጸም ኃላፊ ይሆናል ። ከዚህ በላይ በተሰጠው ኃላፊነት ብቻ ሳይወሰን የፕሬዚዴንቱ ምክር ቤት በተለይ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ለመፈጸም ተግባርና ሥልጣን ይኖረዋል ።

ሀ/ በቦርዱ ፤ በፋኩሊቲው ምክር ቤት እና በአካዳሚኪ ኮሚሽኖች የተሰጡትን ውሳኔዎች መፈጸም ወይም ለሌሎች ኮሚቴዎች አሳልፎ መስጠት ፤

ለ/ እንዲፈቀድ ለቦርዱ የሚቀርበውን የፋኩሊቲውን ምክር ቤትና የአካዳሚክ ኮሚሽን አሳብ መመርመር ፤ ማስተባበርና ስለዚሁም ልዩ ስብሰባ እንዲደረግ ለፕሬዚዴንቱ አሳብ ማቅረብ ፤

ሐ/ እንዲፈቀድ ለቦርዱ ከመቅረቡ አስቀድሞ በጀቱን ማጥናት ፤ እንደዚሁም ለዩኒቬርሲቲው ንብረት አስተዳደር ኃላፊ መሆን ፤ እና

መ/ የአካዳሚክ ኮሚሽን በሚያቀርበው አሳብ መሠረት የዩኒቬርሲቲውን ልዩ ልዩ ሠራተኞች መሾም የደረጃ እድገት መስጠት ፤ ከሥራ ማሰናበት ወይም የሥራ መልቀቂያ ጥያቄዎች መቀበል ።

## ፲፰/ የዩኒቬርሲቲው አካሎች ስብሰባና የድምፅ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት ።

ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ውሳኔዎችና በዚህ ቻርተር በተጻፉት አግባብ ባላቸው ሌሎች ውሳኔዎች መሠረት የዩኒቬርሲቲው አካሎች ለየስብሰባቸው ደንብ ያወጣሉ ።

www.chilot.me



፭/ የእያንዳንዱ ስብሰባ ንግግርና ውሳኔ እያንዳንዱ የዩኒቨርሲቲው አካል በሚመርጠው ጸሐፊ በቃለ ጉባዔ መዝገብ ላይ እንዲሠፍር ተደርጎ ሊቀ መንበሩና ጸሐፊው ይፈር ሙበታል ።

፮/ የዩኒቨርሲቲው አካሎች የእያንዳንዱን ስብሰባ ማስታወቂያ ስብሰባው ሊደረግ ከተ ወሰነበት ቢያንስ ከሦስት ቀን አስቀድሞ ለእያንዳንዱ አባል በጽሑፍ ይሰጠዋል ።

፫/ ከእያንዳንዱ የዩኒቨርሲቲው አካል ከጠቅላላው አባሎች ግማሾቹና አንድ ሌላ ተጨ ማሪ በስብሰባው ከተገኙ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስፈልገው ቁጥር (ኮረም) እንደተ ገኘ ይቆጠራል ።

፬/ ውሳኔ የሚሰጠው በስብሰባው በተገኙት አባሎች የድምፅ ብልጫ ሲሆን ፤ ድምፁም እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ የሊቀ መንበሩ ተጨማሪ ድምፅ የሚደግፈው ወገን የጸና ይሆናል ።

፲፭/ <u>የአካዳሚ ድርጅትና ቋንቋ ።</u>

፩/ ሀ/ ዩኒቨርሲቲው በፋኩሊቲዎች ፣ በኮሌጆች ፣ ትምህርት ቤቶች ፣ የትምህርት ድርጅ ቶችና ከፍተኛና አነስተኛ የትምህርት ክፍሎች ይከፋፈላል ።

ለ/ ፋኩሊቲዎች ተማሪው በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ዲግሪ የሚያገኝባቸውን የተወ ሰኑ ትምህርቶች የማስተማር ኃላፊነት ይኖራቸዋል ።

ሐ/ ኮሌጆች በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በመጀመሪያዎቹ ሁለት የትምህርት ዓመታት ተማሪዎቹን ወደፋኩሊቲው ከመግባታቸው በፊት የማዘጋጀት ኃላፊነት ይኖ ራቸዋል ።

፪/ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ትምህርት የሚሰጥባቸው ብዙዎች አነስተኛ ክፍ ሎች አንድ ከፍተኛ የትምህርት ክፍል ይሆናሉ ። እንዲሁም ጠቅላላ ተመሳሳይ ትምህርት የሚሰጥባቸው ብዙዎች ከፍተኛ የትምህርት ክፍሎች እንደ አንድ ፋኩ ልቲ ይሆናሉ ።

፫/ አንድ ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ድርጅት ተማሪው ምርምር የሚያደርግ በት ወይም በአካዳሚ ጥናት ረገድ በአንድ ሙያ የሚሰለጥንበት የጥናት ቦታ የሚዘ ጋጀት ኃላፊነት ይኖረዋል ። ይህ ዓይነቱ ትምህርት ቤት ከአንድ ዓይነት ፋኩልቲ ጋር የተያያዘ ሊሆን ወይም ለብቻው ሊቋቋም ይችላል ።

፬/ ሀ/ የዩኒቨርሲቲው መደበኛ ቋንቋ አማርኛ መሆን አለበት ።

ለ/ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ትምህርት የሚሰጥበት ቋንቋ በመሠረቱ አማርኛና እንግሊዝኛ መሆን አለበት ።

፲፮/ <u>የአካዳሚ ደረጃና መምህራን ።</u>

ከዲኑ በስተቀር እያንዳንዱ ፋኩልቲና ኮሌጅ ፣ ፕሮፌሰሮች ፣ ተባባሪ ፕሮፌሰሮች ፣ ረዳት ፕሮፌሰሮች ፣ ሌክቸረርና ረዳት ሌክቸረሮች ይኖሩታል ።

የእነዚህ መምህራን የአካዳሚ ደረጃ እንደሚከተለው መሆን አለበት ።

፩/ አንድ ፕሮፌሰር የዶክተር ዲግሪ ያለው ሆኖ ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ ወይም ከፍተኛ ደረጃ ካለው የትምህርት ድርጅት የዚሁ ተመሳሳይ ዲግሪ ያለው ሆኖ መጀመሪያ ስላደረገው ምርምር ወይም ውጤት ማስረጃ መስጠትና ቢያንስ የአሥር ዓመት የአካዳሚ የሥራ ልምድ ወይም በልዩ ሙያው በሊቃውንት ዘንድ ስመ ጥሩ መሆን አለበት ።

፪/ አንድ ተባባሪ ፕሮፌሰር የዶክተርነት ዲግሪ ወይም የዚሁ ተመሳሳይ ያለው ሆኖ በመጀመሪያ ባደረገው ምርምር የማስተማር ጥላነት ያለው መሆኑን ማሳየትና ቢያ

www.chilot.me



ንስ የሰባት ዓመት የአካዳሚ የሥራ ልምድ ያለው ወይም በልዩ ሙያው በሲታው ንት ዘንድ ስመ ጥሩ መሆን አለበት ።

፫/ አንድ ረዳት ፕሮፌሰር በሚያስተምረው ትምህርት የማስትሬት ዲግሪ ወይም ከከብር ጋር የቢ.ኤ.ዲግሪ ኖሮት ቢያንስ የሦስት ዓመት የአካዳሚ የሥራ ልምድ ያለው መሆን አለበት ።

፬/ አንድ ሌክቸረር በሚያስተምረው ትምህርት የባቸለር ዲግሪ ኖሮት ቢያንስ የአንድ ዓመት የአካዳሚ ሥራ ልምድ ያለው መሆን አለበት ።

፭/ አንድ ረዳት ሌክቸረር በሚያስተምረው ትምህርት የባችለር ዲግሪ ያለው መሆን አለበት ።

፳/ ስለሥነ ሥርዓት አከባበር ።

ፕሬዚዴንቱ ወይም ወኪሉ ከቦርዱ የሚሰጠውን ጠቅላላ ፖሊስና መምሪያ ጠብቆ ሥነ ሥርዓትን በሚያጓድሉ የዩኒቬርሲቲው ሠራተኞችና ተማሪዎች ላይ አስፈላጊውን የሥነ ሥርዓት ማስከበሪያ እርምጃ ሊወስድ ይችላል ።

የሥነ ሥርዓት እርምጃ የተወሰደበት ማንኛውም የዩኒቬርሲቲው ሠራተኛ ወይም በሥነ ሥርዓት ምክንያት ከትምህርት ቤት እንዲወገድ የተወሰነበት ተማሪ ለቦርዱ ይግባኝ ለማለት መብት አለው ። ቦርዱም የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል ።

፳፩/ ደንብ ።

ቦርዱ ይህንን ቻርተር በተሻሻለ አኳኋን ለማስፈጸም የውስጥ ደንብ ሊያወጣ ይችላል ።

፳፪/ ስለ ቻርተሩ መሻሻል ።

ይህ ቻርተር እንዲሻሻል ከቦርዱ አባሎች ከሦስቱ እጅ ሁለት እጅ ወይም ከዚህ የበለጡ አባሎች አሳብ ሲያቀርቡ ቦርዱ ይህንኑ ለእኛ አቅርቦ አስፈላጊው መሻሻል ይደረጋል ።

፳፫/ የሚጸናበት ጊዜ ።

ይህ ቻርተር በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ. ም.

፳፰/፩ (፲፱፻፷፩) ት.፶፩

የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት ፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት ብሔራዊ ኮሚሽን በኢትዮጵያ ለማቋቋም የወጣ ትእዛዝ ፣

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ዓለም በትምህርት ፣ በሳይንስና በባህል ረገድ የሚያደርገውን ጠቃሚ እርምጃ ሕዝባችን ለአእምሮው ማጐልመሻና ለኑሮው ማዳበሪያ እንዲያውለውና እንዲሁም ኢትዮጵያ በትምህርት ፣

www.chilot.me



በሳይንስና በባህል ረገድ ስለምታደርገው እርምጃ መረጃዎች በሚገባ እንዲሰበሰቡ ፣ እንዲጠበቁና ለዓለም እንዲሠራጩ ለማድረግ የዘወትር ዓላማችንና ሐሳባችን ስለሆነ ፤

ይህንኑም ዓላማችንን ከግቡ ለማድረስ የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት ፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ከዚህ በኋላ «ዩኔስኮ» እየተባለ የሚጠራ) ብሔራዊ ኮሚሽን እንዲቋቋም አስፈላጊ መሆኑን ተመልክተን ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤታችንም መክሮ ያቀረበልንን ፈቅደን በተሻሻለው ሕገ መንግሥታችን በአንቀጽ ፳፯ መሠረት ቀጥሎ ያለውን አዘናል ።

## ፩/ አርእስት ።

### ፩/ አጭር አርእስት ።

ይህ ትእዛዝ «የዩኔስኮ ብሔራዊ ኮሚሽን የተቋቋመበት የ፲፱፻፷፩ ዓ.ም. ትእዛዝ» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

## ፪/ የኮሚሽኑ መቋቋም ።

### ፪/ የኮሚሽኑ መቋቋም ።

በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር የሚደገፍ ከዚህ በኋላ «ኮሚሽን» እየተባለ የሚጠራ አንድ ራሱን የቻለ የዩኒስኮ ብሔራዊ ኮሚሽን በዚህ ትእዛዝ ተቋቋሟል ።

## ፫/ ዓላማዎችና ተግባሮች ።

### ፫/ ዓላማዎች ።

የኮሚሽኑ ዓላማዎች ከዚህ የሚከተሉት ይሆናሉ ።

፩/ ከዩኔስኮ ጋር በቅርብ በመተባበር በኢትዮጵያ ውስጥ የትምህርት ፤ የሳይንስና የባህልን ሥራዎች ማበረታታትና ማስፋፋት ፤

፪/ በኢትዮጵያ ሕዝብና በዓለም ሕዝብ መካከል የትምህርት ፤ የሳይንስና የባህል መለዋወጥ እየተስፋፋ እንዲሄድ መርዳት ፤

### ፬/ ተግባሮች ።

፩/ ኮሚሽኑ ዓላማዎቹንና ተግባሮቹን ለመፈጸም ተገቢ በሆኑት አካሎች አማካይነት ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ይፈጽማል ።

ሀ/ ከዓላማዎቹ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ጥናት ማድረግና የጥናቱን ውጤቶች አሳትሞ ማውጣት ፤

ለ/ ከዩኔስኮ ጋራ ግንኙነት ያላቸውን በኢትዮጵያ ውስጥ የትምህርት ፤ የሳይንስና የባሕልን ሥራዎች ማስተባበርና ማስፋፋት ፤

ሐ/ በሀገሪቱ ውስጥ ካሉ የመንግሥትና የግል ድርጅቶች ጋር መተባበርና ከዩኔስኮ ጋራ ስላላቸው የሥራ ግንኙነት ለነዚህ ድርጅቶች ምክር መስጠት ፤

መ/ የራሱን ዓላማዎች ለመፈጸም ከዩኔስኮ ጋር ፕሮግራሞች የሚስፋፉበትን መንገድና ዘዴ ማጥናትና የዩኔስኮ ፕሮግራሞች በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገባ መፈጸማቸውን መከታተል ፤

www.chilot.me



፬/ ፕሬዚዳንቱ በማንኛውም ጊዜና በየጊዜው የጠቅላላውን ጉባዔ አባሎች ቁጥር ለማሳደግ ይችላል ፤ ሆኖም የአባሎቹ ቁጥር እንዲያድግ ሲደረግ የኤክስ ኦፊሺዮ አባሎች ቁጥርና የልዩ አባሎች ቁጥር እኩል ማደግ አለበት ።

፲/ ምክትል ፕሬዚዴንት ።

ጠቅላላው ጉባዔ ከኮሚሽኑ ልዩ አባሎች መካከል ለሁለት (፪) ዓመት የሚያገለግል አንድ ምክትል ፕሬዚዴንት ይመርጣል ። ምክትሉ ፕሬዚዴንት እንደገና ለመመረጥ ይችላል ።

፲፩/ ተግባርና ሥልጣን ።

ጠቅላላው ጉባዔ ከዚህ የሚከተሉት ተግባሮችና ሥልጣኖች ይኖሩታል ።

፩/ የሥራ አስፈጻሚውን ምክር ቤት የዓመት ሪፖርት ተቀብሎ መፍቀድ ፤

፪/ የኮሚሽኑ የዓመት የበጀት ግምት ተቀብሎ መፍቀድ ፤

፫/ ኮሚሽኑ ስለሚፈጽማቸው ፕሮግራሞችና የኮሚሽኑን ሥራ ለማፋጠን ስለሚረዱት ሌሎች እርምጃዎች ለሥራ አስፈጻሚው ምክር ቤት አሳብ ማቅረብ ፤

፬/ ተጨማሪ ድርጅቶችና ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ ለሥራ አስፈጻሚው ምክር ቤት አሳብ ማቅረብ ።

፲፪/ ስብሰባና ሥነ ሥርዓት ።

፩/ ጠቅላላው ጉባዔ በየዓመቱ ቢያንስ ሁለት (፪) ጊዜና ከአባሎቹ የሚበዙት ከጠየቁ ወይም ፕሬዚዳንቱ ጥሪ ካደረገ ከዚህም የበለጠ ጊዜ ይሰበሰባል ። የመጀመሪያው ስብሰባ ይህ ትእዛዝ ከሚጸናበት ቀን ጀምሮ በሁለት (፪) ወር ጊዜ ውስጥ ይሆናል ።

፪/ ጠቅላላው ጉባዔ የራሱን የሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል ።

፯/ ቀዋሚ ጽሕፈት ቤት ።

፲፫/ አቋምና አላፊነት ።

፩/ ቀዋሚው ጽሕፈት ቤት አንድ ዋና ጸሐፊና ለኮሚሽኑ ሥራ አስፈላጊ የሆኑት ሠራተኞች ይኖሩታል ።

፪/ ቀዋሚው ጽሕፈት ቤት ሪፖርር የሚያቀርበውና ተጠያቂ የሚሆነው በቀጥታ ለሥራ አስፈጻሚው ምክር ቤት ነው ።

፲፬/ ዋና ጸሐፊ ።

፩/ ዋናው ጸሐፊ በትምህርት ፤ ፕሮግራም በማዘጋጀትና በአስተዳደር ረገድ ሰፊ የሆነ የሥራ ልምድና እንዲሁም ጥልቅ ከሆነ የብሔራዊነት ፤ የትምህርት ፤ የሳይንስና የባህል ስሜት ጋራ ችሎታ ያለው ሰው ሆኖ በጠቅላላው ጉባዔ ፕሬዚዴንት አሳሳቢነት በኖ ይሾማል ።

፪/ ዋናው ጸሐፊ የኮሚሽኑ የአስተዳደር ዋና ሹም ይሆናል ፤

፫/ ዋናው ጸሐፊ ለሥራ አስፈጻሚው ምክር ቤትና ለጠቅላላው ጉባዔ የአስተዳደር ሹም ሆኖ ይሠራል ። እርሱም በስብሰባው ድምፅ የመስጠት መብት አይኑረው እንጂ በሥራ አስፈጻሚው ምክር ቤትና በጠቅላላው ጉባዔ ስብሰባዎች ሁሉ ይገኛል ።

www.chilot.me



፲፰/  <u>በጀት ።</u>

፩/ ዋናው ጸሐፊ ከሥራ አስፈጻሚው ምክር ቤት ጋራ በመመካከር የዓመቱን የበጀት ግምትና ፕሮግራም ያዘጋጃል ።

፪/ ከመንግሥቱ በሚሰጠው የበጀት ክፍል ሥራ አስፈጻሚው ምክር ቤት ከተስማማ በት በኋላ እንዲፈቀድና ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለመንግሥት ይቀርባል ።

፱/ <u>የመጨረሻ ውሳኔዎች ።</u>

፲፱/ <u>ትእዛዙ የሚጸናበት ቀን ።</u>

ይህ ትእዛዝ <u>በነጋሪት ጋዜጣ</u> ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ጥር ፳፫ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ.ም.

፷፰/፲፱ (፲፱፻፷፩) ት. ፶፰

የሥራ እስኪያጆች ማሠልጠኛ ድርጅትን ለማቋቋም
<u>የወጣ ትእዛዝ ።</u>

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እኛ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

በዘመናዊ ዕውቀት የደረጁ ሥራ እስኪያጆች ማሠልጠን ፣ ማበረታታትና ማደርጀት እንዲሁም ሕዝባችን በጠቅላላው የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዕድገት በብዛትና በተሟላ ሁኔታ ተካፋይ እንዲሆን መደገፍና መርዳት አስፈላጊ ስለሆነ ፤

እነዚህም የማሠልጠንና የማደርጀት ዓላማዎች በተሟላና በተፋጠነ ሁኔታ ሲፈጸሙ የሚቻለው እንደዚህ የመሰሉትን አገልግሎቶች የመስጠቱና የማስተባበሩ ኃላፊነት የሚሰጠው እራሱን የቻለ የመንግሥት ባለሥልጣን በማቋቋም ስለሆነ ፤

በተሻሻለው ሕገ መንግሥታችን በአንቀጽ ፳፯ መሠረት የሚኒስትሮች ምክር ቤታችን መክሮበት ያቀረበልንን ተመልክተን የሚከተለውን አዝዘናል ።

፩/ <u>አጭር አርእስት ፤</u>

ይህ ትእዛዝ «የሥራ እስኪያጆች ማሠልጠኛ ድርጅት የተቋቋመበት የ<u>፲፱፻፷፩</u> ዓ.ም. ትእዛዝ» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

፪/ <u>ትርጓሜ ፤</u>

በዚህ ትእዛዝ ውስጥ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጓሜ ካላስፈለገው በቀር ፤

ሀ/ «ቦርድ» ማለት በዚህ ትእዛዝ አንቀጽ ፲ መሠረት የተቋቋመ ሥራ አስፈጻሚ ቦርድ ማለት ነው ፤

www.chilot.me



ለ/ «ዋና ሥራ አስኪያጅ» ማለት በዚህ ትእዛዝ በአንቀጽ ፯ መሠረት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆኖ የሚሾመው ሹም ማለት ነው ፤

ሐ/ «ጉባዔ» ማለት በዚህ ትእዛዝ አንቀጽ ፰ የሚቋቋመው ብሔራዊ ጉባዔ ማለት ነው።

፫/ የድርጅቱ መቋቋም ፤

ከዚህ ቀጥሎ «ድርጅት» እየተባለ የሚጠራ አንድ ራሱን የቻለ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የሥራ አስኪያጆች ማሠልጠኛ ድርጅት በዚህ ትእዛዝ ተቋቁሟል ። የድርጅቱም ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ውስጥ ይሆናል ።

፬/ የድርጅቱ ዓላማዎች ፤

የድርጅቱ ዓላማዎች ሕዝባችን በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የኢንዱስትሪና የኤኮኖሚ ዕድገት በብዛትና በተሟላ ሁኔታ ተካፋይ እንዲሆን በቀጥታ ርዳታና በኤክስቴንሽን አገልግሎቶች አማካይነት መደገፍና መርዳት ሲሆኑ በተለይም ፤

ሀ/ ተቋቁመው ለሚገኙት ወይም ወደፊት ሥራ ለሚወጥኑ ሁሉ በጥቃቅን የሥራ ድርጅቶች የገቢር የሆነ የማሠልጠኛና የአማካሪነት አገልግሎት በመስጠት ፤

ለ/ ለሥራ ወጣኞች የኤክስቴንሽን አገልግሎትና ሌላም ዓይነት ርዳታ ለሚሰጡ ድርጅቶች በሥራ አስኪያጅነትና በሥራ ወጣኝነት የአማካሪነት አገልግሎት በመስጠት ፤

ሐ/ ለሕዝብ አገልግሎትና ጥቅም በሚሰጡ ድርጅቶች ቅምር በከፍተኞች የመንግሥትና የግል የሥራ ድርጅቶች ውስጥ ለሚሠሩ ሥራ አስኪያጆች የሥራ አስኪያጅነት ልምምድ በመስጠት ፤

፭/ ስምምነት ፤

ድርጅቱ አገልግሎቶቹን ለማስፋፋትና ዓላማዎቹን ለመፈጸም መንግሥት ስለድርጅቱ ሥራዎች ከማንኛውም ወገን ወይም ወገኖች ጋር የተዋዋለውን ወይም የሚዋዋለውን ማንኛውንም ስምምነት በሥራ ላይ ለማዋል ይችላል ።

፮/ ቦርድ ፤

ሀ/ የድርጅቱ ሥራ ከዚህ ቀጥሎ «ቦርድ» እየተባለ በሚጠራው በአንድ ሥራ አስፈጻሚ ቦርድ ጠቅላላ ቁጥጥር ስር ይሆናል ። ቦርዱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሰዎች ይገኙበታል ።

፩/ የቦርዱ ሊቀ መንበር የሚሆነው የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገትና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትራችን ፤

፪/ የንግድ ፣ የኢንዱስትሪና የቱሪዝም ሚኒስትራችን ፤

፫/ የእርሻ ሚኒስትራችን ፤

፬/ የትምህርትና የሥነ ጥበብ ሚኒስትራችን ፤

፭/ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ።

ለ/ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የድርጅቱ ሥልጣኖች ሁሉ ለቦርዱ ተሰጥተዋል ።

ቦርዱም ድርጅቱን በሚገባ ለማስተዳደር አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ በሥልጣኑ እንዲሠራበት ዋናውን ሥራ አስኪያጅ ይወክላል ።

www.chilot.me



፭/ በመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ጠቅላይ መሥሪያ ቤትና የመንግሥት ሠራተኞች ትእዛዝ (በትእዛዝ ቁጥር ፳፫/፶፬ ማሻሻያና በታረመው) እንደዚሁም በደንቡ መሠረት ፤

ሀ/ የድርጅቱን ሥራ በሚገባ ለማካሄድ የሚያስፈልጉትን ሠራተኞች ለመምረጥና ለመቅጠር ፤

ለ/ ከላይ እንደተጠቀሰው የተቀጠሩትን ሠራተኞች ከሥራ ለማሰናበት ፤

ሐ/ የድርጅቱን ከፍተኛ ሹማምንት ቅጥርና የሥራ ስንብት ለመፍቀድ ፤

፮/ የውስጥ ደንቦችና ሥነ ሥርዓቶችን ለመፍቀድ ፤

፯/ በተገቢው መንገድ በኩል ከማንኛውም መንግሥት ወይም መንግሥታት ወይም ከሌላ ምንጭ የውጭ ርዳታ ለመጠየቅ ፤

፰/ ድርጅቱ ለሚሰጠው አገልግሎት ተገቢ ገንዘብ ለማስከፈል ፤

፱/ የድርጅቱን ዓመታዊ ፕሮግራምና በጀት ለመፍቀድ ፤

፲/ ከዚህ በላይ በተሰጠው ጠቅላላ ሥልጣን ብቻ ሳይወሰን ድርጅቱ በተለይ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ለመፈጸም ይችላል ።

ሀ/ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመግዛት ለንብረቱ ባለቤት ለመሆንና ንብረቱን ለመሸጥ ፤ ለመለወጥ ፤

ለ/ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ለማከራየትና ለመበደር ፤

ሐ/ ከሌሎች ጋር ውል ለመግባት ፤

መ/ ለመክሰስና ለመከሰስ ፤

ሐ/ ቦርዱ በያንዳንዱ የበጀት ዓመት ውስጥ በየሦስት (፫) ወር አንድ ጊዜና ለድርጅቱ ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሌሎችም ጊዜያቶች በሊቀ መንበሩ ይሰበሰባል ።

<u>የተጠቀሰው ሕግ</u>

የመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደርያ ጠቅላይ መ/ቤትን ስለማቋቋም ፤ ፳፩/፫ (፲፱፻፷፱) ት. ፳፫ ፣ ፳ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፪ ።

፯/ <u>ዋና ሥራ አስኪያጅ ፤</u>

በሕዝባዊ ኑሮ ዕድገትና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትራችን አሳሳቢነት በቦርዱ የሚሾም አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ ይኖራል ። ዋናው ሥራ አስኪያጅ በቦርዱ ጠቅላላ ተቆጣጣሪነት የድርጅቱን ሥራ በሚገባ ለማካሄድ ፤ ለማስተዳደርና ለመምራት ኃላፊ ይሆናል ። ዋናው ሥራ አስኪያጅ ከቦርዱ በሚሰጡት ሥልጣኖች ሁሉ ይሠራባቸዋል ። በበኩሉም ድርጅቱን በሚገባ ለማስተዳደር አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ሥራውን ፤ ተግባሩንና ሥልጣኑን አስፈላጊ ለሆኑት ለሌሎች የድርጅቱ ከፍተኛ ሹማምንት በከፊል ለመስጠት ይችላል ።

፰/ <u>ብሔራዊ ጉባዔ ፤</u>

ሀ/ ድርጅቱ አንድ ብሔራዊ ጉባዔ ይኖረዋል ፤ ጉባዔውም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አባሎች ይገኙበታል ።

www.chilot.me



፩/ የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገትና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትራችን ፤

፪/ የንግድ ፡ የኢንዱስትሪና የቱሪዝም ሚኒስትራችን ፤

፫/ የእርሻ ሚኒስትራችን ፤

፬/ የትምህርትና የሥነ ጥበብ ሚኒስትራችን ፤

፭/ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቬርሲቲ ፕሬዚዴንት ፤

፮/ የንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዴንት ፤

፯/ የኢትዮጵያ አሠሪዎች ማኅበር ፕሬዚዴንት ፤

፰/ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ፕሬዚዴንት ፤

ለ/ ጉባዔው በሕዝባዊ ኑሮ ዕድገትና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትራችን ሊቀ መንበርነት ይሰበሰባል ።

ሐ/ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ የጉባዔው ሥራ አስፈጻሚ ጸሐፊ ሆኖ ያገለግላል ።

መ/ ጉባዔው የድርጅቱን ጠቅላላ መምሪያ ለማውጣትና ለመወሰን ኃላፊ ይሆናል ።

፱/ የድርጅቱ ገቢ ፤

ሀ/ መንግሥት ከሚሰጠው የገንዘብ መዋጮ ፤

ለ/ ከግል ፡ ከሕዝብና ከማንኛውም ምንጭ ወይም ምንጮች ለድርጅቱ ከሚደረገው የገንዘብ መዋጮ ስጦታና ክፍያ ፤

ሐ/ ድርጅቱ ለሚሰጠው አገልግሎት ከሚከፈል ገንዘብ ፤

መ/ ድርጅቱ ከሚቀበለው ከማንኛውም ሌላ ገንዘብ የሚገኝ ይሆናል ።

፲/ የድርጅቱ ገንዘብ የማይዘዋወር ስለመሆኑ ፤

በዚህ ትእዛዝ በአንቀጽ ፱ መሠረት የተጠራቀመው ገንዘብ በድርጅቱ ሂሳብ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም ይህ ባንክ በሚወክለው በሌላ ባንክ ተቀማጭ ሆኖ ቦርዱ በየጊዜው ለሚወስናቸው ጉዳዮች በድርጅቱ ወጭ ይሆናል ።

፲፩/ ዓመታዊ ፕላንና ሪፖርት ፤

ሀ/ ዋና ሥራ አስኪያጁ ስለመጭው ዓመት የድርጅቱን ሥራ ፕላን አዘጋጅቶ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት ፤

ለ/ በያንዳንዱ የበጀት ዓመት ማለቂያ ዋና ሥራ አስኪያጁ ስለድርጅቱ ሥራ የዓመት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት ።

፲፪/ ትእዛዙ የሚጸናበት ቀን ፤

ይህ ትእዛዝ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሰኔ ፲ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ.ም.

www.chilot.me



## ፳፰/፲፰ (፲፱፻፷፩) ት. ፶፰

## ብሔራዊ የትምህርት ኮሚሽን ለማቋቋም የወጣ ትእዛዝ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምራ ያፈራችው ትምህርትና ሥልጣኔ ያላት አገር በለሆነች ፤ በአሁኑ ክፍለ ዘመን ደግሞ ኅብረተሰቡን ወደ ዘመናዊ ሥልጣኔና ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ለማራመድ ስለወሰነች ፤

ትምህርት ለትውልድ እየተላለፈና እየተሻሻለ የሚሔድ ነዋሪ ሀብት በመሆኑ ፤ ሕዝቡም በጠቅላላ የአንድነት ኑሮውን ለማበልጸግና ለማጠንከር የሚያስችለው ፤ ልማትም የሚመራበትን ሁኔታ የሚያረጋግጥና ወደ ከፍተኛ ደረጃ የመድረስም ተስፋ ዓይነተኛ መግሪያ በመሆኑ ፤

የኢትዮጵያን የትምህርት አጳም እያጠና ሐሳብ የሚያቀርብ ብሔራዊ የትምህርት ኮሚሽን ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ ስለአገኘነው ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤታችን መክሮ ያቀረበልንን ዓይተን ፤ በተሻሻለው ሕገ መንግሥታችን አንቀጽ ፳፯ መሠረት ቀጥሎ ያለውን አዘናል ።

### ፩/ አጭር አርእስት ፤

ይህ ትእዛዝ «ብሔራዊ የትምህርት ኮሚሽን የተቋቋመበት የ፲፱፻፷፩ ዓ.ም. ትእዛዝ» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

### ፪/ ብሔራዊ የትምህርት ኮሚሽን መቋቋም ፤

በዚህ ትእዛዝ የተመለከቱትን ሥራዎች የሚያከናውን ብሔራዊ የትምህርት ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ «ኮሚሽን» ተብሎ የተሰየመ) ተቋቁሟል ። ኮሚሽኑ ኃላፊነቱ በቀጥታ ለጠቅላይ ሚኒስትራችን ይሆናል ።

### ፫/ ሥራ ፤

ኮሚሽኑ የሚቀጥሉትን ሥራዎች ይፈጽማል ፤

ሀ/ ትምህርት በኢትዮጵያ በጠቅላላው ሊኖረው የሚገባው ዓላማና ግብ ከጥንቱና ከአሁኑ የተሻለውን አዋህዶና አዛምዶ ኅብረተ ሰቡ በአንድነት በዓላማዊም ሆነ በመንፈሳዊ ረገድ ከፍተኛ ብልጽግናን የሚያገኝበትን መንገድና ዘዴ እያጠና ማቅረብ ፤

ለ/ በአገሪቱ ፍላጎትና ችሎታ መጠን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ በብዛትም ሆነ በዓይነት ተመሳሳይና የተመጣጠነ የትምህርት ዕድል የሚያገኝበትን መንገድ በየጊዜው እያጠና ማቅረብ ፤

ሐ/ የአንደኛ ፤ የሁለተኛና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ዓላማ በጠቅላላው ከአገሪቱ ፍላጎት ጋር ተዛምዶ እንዲቀናበር ፤ አረማመዱም የተፈለገውን ውጤት የሚሰጥበትን መንገድ ማጥናትና ማቅረብ ፤

መ/ የኢትዮጵያ የትምህርት ዓላማ ቅድሚያው ለልማት በመሆኑ የአእምሮ ዕውቀትና የእጅ ሙያ እንዲሁም በዕድሜ ለገፉት ሰዎች የሚሰጠው ከሞያ ጋር የተያያዘ

www.chilot.me



ትምህርት ተዛምዶ የያንዳንዱ ምድብ ትምህርት ውጤት በኅብረተ ሰቡ ኑሮ ውስጥ ሰምሮ እንዲገኝ፤ ከመጀመሪያ ጀምሮ በየደረጃውና በያቅጣጫው ጠቃሚነቱ ታውቆ ለአገሪቱ ልማት መፋጠን ዓይነተኛ መሣሪያ የሚሆንበትን ዘዴ እየመረመረና እያ ጠና ውጤቱን መግለጽ ።

፬/ ሥራውን የሚያካሄድበት ሁኔታ ፤

ኮሚሺኑ ሥራውን የሚያከናውነው ከዚህ በሚከተለው አኳኋን ነው ።

ሀ/ ከላይ የተዘረዘሩትን ሥራዎች ለማከናወን ኮሚሺኑ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ማንኛውንም ሰው ወይም ድርጅት ትምህርት ነክ በሆነ ጉዳይ ላይ በጽሑ ፍም ሆነ በቃል ለመጠየቅ ይቻላል ፤

ለ/ ልዩ ጥልቅ ጥናቶች ሲያስፈልግ በየጊዜው መምሪያ ሃሳብ በመስጠት እያስጠና ያቀርባል ፤

ሐ/ ትምህርትን ከሚደግፉ ከልዩ ልዩ ድርጅቶች ጋር የሐሳብ መለዋወጥና ሲያ ስፈልግም የጥናት ዕርዳታ ለመጠየቅ ይችላል ፤

መ/ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የሥራውን ውጤት መግለጫ ለጠቅላይ ሚኒስትራችን ያቀርባል ፤

ሠ/ ኮሚሺኑ የራሱን የሥራ አፈጻጸም ሥነ ሥርዓት ያወጣል ።

፭/ አቋም ፤

ሀ/ ኮሚሺኑ በኛ የሚሾሙ ቁጥራቸው ከሃያ አንድ የማይበልጥ አባሎች ይኖሩታል ። ከአባሎቹ መካከል አንድ ሊቀ መንበርና አንድ ምክትል ሊቀ መንበር በኛ ይሾማሉ።

ለ/ ኮሚሺኑ ቋሚ ጽሕፈት ቤትና ጽሕፈት ቤቱንም የሚመራ አንድ ዋና ጸሐፊና አስፈላጊውም ሠራተኞች ይኖሩታል ።

፮/ በጀት ፤

ኮሚሺኑ ከመንግሥት የሚሰጥ ዓመታዊ በጀት ይኖረዋል ።

፯/ ትእዛዙ ስለሚጸናበት ጊዜ ፤

ይህ ትእዛዝ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ. ም.

www.chilot.me



## ክፍል ፴

# የሕዝብ ጤና ጥበቃ ።

### ፮/፪ (፲፱፻፴፱) መ. ፸፯ *

### የዋናው መድኃኒት ቤት ኮርፖሬሽን ቻርተር

በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛትም ሆነ በውጪም አገር መድኃኒቶችንና የሕክምና የፋርማሲም መሣሪያዎች ለመሰብሰብና ለማስቀመጥ ለማከፋፈልም ሙሉ ሥልጣን ያለው ዋናው የመድኃኒት ቤት ኮርፖሬሽን ተብሎ የመንግሥት ኮርፖሬሽን የሚቋቋምበትንና የሚሠራበትን መወሰን ስለፈለግንና፤

የተባለውም ዋናው የመድኃኒት ቤት ኮርፖሬሽን በመንግሥታችን ቻርተር እንዲቋቋም የሚሻል ሆኖ ስለተሰማን፤

በፈቃዳችንና አሳባችን በዚህ የመንግሥታችን ቻርተር እኛና የእኛ ወራሾች የመድኃኒት ቤት ኮርፖሬሽን በስምም በሥራም ዋናው የመድኃኒት ቤት ኮርፖሬሽን ተብሎ የተቋቋመ ሆኖና በዚህ የመንግሥት ቻርተር እንደተገለጸው የኮርፖሬሽኑ ዲሬክተሮች ጉባዔ በተሰጣቸው ሥልጣን ሊለውጡት የሚቻል የጋራ ማኅተም ያለው እንዲሆን ፈቅደናል ። ደግሞም ቀጥሎ ያለውን ፈቅደናል ።

፩/ የኮርፖሬሽኑ ስም ዋናው የመድኃኒት ኮርፖሬሽን ሆኖ ከእንግዲህ ወዲህ ኮርፖሬሽን እየተባለ ይጠራል ።

፪/ የኮርፖሬሽኑ ዋናው የጽሕፈት ቤትና የንግድ ቤት በአዲስ አበባ በአርበኞች መንገድ በሚገኘው የመድኃኒት ቤቶች ውስጥ ነው ። ኮርፖሬሽኑም በማናቸውም ጊዜ ኢትዮጵያዊ መሆን አለበት ።

፫/ ኮርፖሬሽኑ የሚሠራቸው ሥራዎች፣ ዓይነትና የሥራውም ዓላማና ምክንያት እንደሚከተለው ነው ።

በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት ውስጥም ሆነ በውጪም ማናቸውንም ዓይነት የመድኃኒት፣ የሕክምናና የፋርማሲ ዕቃዎችንና መሣሪያዎችን በመግዛት፣ በመሰብሰብና በማከፋፈል እንደወኪልና ስለኢትዮጵያ መንግሥትም ሆኖ እንዲሠራ ነው ።

በኢትዮጵያም ሆነ በውጭ አገር ማናቸውም ዓይነት መድኃኒት፣ የሕክምናና የፋርማሲ ዕቃዎችና መሣሪያዎች በግዥም ሆነ በሌላ መንገድ ለመሰብሰብና ለማከማቸት፣ ለማከፋፈልና ለማበደር፣ ለመበደርም እንደዚሁም ይህን የተመለከተውን ሥራ ለመፈጸም የሚመቹትን የቤትና ቦታ የሚጨበጡና የማይጨበጡም ንብረቶችን በግዥም ሆነ በሌላ መንገድም እጅ ማድረግ ።

በኢትዮጵያም ሆነ በውጭ አገር መድኃኒቶችንና የሕክምና የፋርማሲም መሣሪያዎችን ስለመሸጥና ስለማከፋፈል ውል መዋዋል ። እንደዚሁም ይህን የተመለከተውን ሥራ ለመፈጸም የሚሆኑትን የሚጨበጡና የማይጨበጡ ንብረቶችን መያዝና መስጠት፣ መግዛትና መሸጥ ወይም በኮሚሲዮን እጅ ማድረግ፣ ደግሞም ሕግ በሚፈቅደው መሠ

---

* የመግቢያ የግርጌ ማስረጃ

በ፳/፯ (፲፱፻፶፫) መ. ፪፻፹ ተሻሻለ፤ በን. ሕ. ፺፱/በተ. የ. ፫ (፲፱፻፶፪) በግ. ሳ. ተሻሻለ ።

www.chilot.me



## የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳/፮ (፲፱፻፶፫) መ. ፪፻፹ አን. ፪ ተሻሻለ ።

፯/ የባለድርሻዎቹ ንብረትና ርስት በድርሻቸው ልክ ከሚደርሳቸው በላይ እንደ ከፋይ አይሆንም ።

፰/ የሥራው አካሄድና የዲሬክተሮቹ ፤ የባለድርሻዎቹ በጠቅላላውም የኮርፖሬሽኑ ሥልጣን ተጣርቶ ይለይና ይወሰን ዘንድ የሚከተለው ተጨማሪ ድንጋጌ ተሰጥቷል ።

ሀ/ ለዲሬክተሮችና ሌላም የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች ለኮርፖሬሽኑ ስለሚያደረጉት አገልግሎት የሚከፈለውን ደመወዝ የዲሬክተሮች ጉባዔ በድምፅ ብልጫ ይወስናል።

ለ/ የዲሬክተሮች ጉባዔ የኮርፖሬሽኑን ዝርዝር የውስጥ ደንብ ይነድፋል ፤ የኮርፖሬሽኑ ማኅተም ይኖረዋል ፤ ይህ ማኅተም ለማናቸውም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሚጻፉ ደብዳቤዎች በዋናው ላይና እንደዚሁም ኮርፖሬሽኑ ከአንድ ሺህ ብር (የኢት. ፩ሺ) በላይ ባለዕዳ የሚሆንበትን በሚያስረዱ ሠነዶች ላይ ይታተማል ።

መ/ ዲሬክተሮቹ ፤ ከሚገኘው ነፃ ትርፍ ላይ ሃምሳ በመቶ (50%) በተለይ ለመጠባበቂያ እንዲቀመጥ ያደርጋሉ ፤ ይህም አደራረግ መጠባበቂያው የካፒታሉ ሁለት እስረኛ እስኪሆን ድረስ ይቀጥላል ፤ ቀጥሎ ከተመለከተው አኳኋን በቀርም ዲሬክተሮቹ ለያንዳንዱ ባለድርሻ የሚደርሰውን የትርፍ ድርሻ መወሰንና ማከፋፈል ይችላሉ ። የኮርፖሬሽኑ አቋቋሚዎች ግን ኮርፖሬሽኑን በማቋቋም ስለአደረጉት አገልግሎት ምንም ዋጋ አይሰጣቸውም ።

ሠ/ በማናቸውም የዲሬክተሮቹ ስብሰባ ቢያንስ ግማሻቸው እንዲገኙበት ያስፈልጋል ፤ የሚቆረጠውም በድምፅ ብልጫ ሆኖ የድምፁ ልክ እኩል ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ፕሬዚዴንቱ ያለበት ወገን ድምፅ መቁረጫ ይሆናል ።

ረ/ አስፈላጊ ሲሆን የኮርፖሬሽኑን አለኝታ ሁሉ የዲሬክተሮች ጉባዔ ገምቶ ይወስናል። በዚሁም አኳኋን የሚደረገው ግምት ከኮርፖሬሽኑ ጋር ግንኙነት ላላቸው ሰዎች ሁሉ የመጨረሻ ውሳኔ ነው ። እንደዚህ ያለውም ውሳኔ ሲደረግ ስለባለደንበኛነት ምንም ግምት አይታሰብም ። በአደራረጉም ላይ የዲሬክተሮች ጉባዔ የኮርፖሬሽኑን አለኝታ የተቻለውን ያህል በጊዜው የገበያ ዋጋ መሠረት እንዲሆን እያደረገ ኮርፖሬሽኑ ያለበትንም ዕዳ ድንገተኛውንና ቀደም ብሎ የተከፈለውንም ጭምር ማሰብ አለባቸው ። እንደዚህ ያለውን ውሳኔ በማከናወን ላይ የዲሬክተሮቹ ጉባዔ ማናቸውም የሕዝብ ሆነ ፣ ወይም የንግድ ቤት ሂሳብ ሠራተኛ የዲሬክተሮች ጉባዔ የሚፈቅደው ከሆነ እንዲረዳ ማድረግ ይችላሉ ። ይህም የሂሳብ ሠራተኛ የኮርፖሬሽኑ መርማሪም ሊሆን ይችላል ፤ እንዲሆን ግን ግዴታ የለበትም ። ማናቸውም ሰው ስለ ውሳኔው የፕሬዚደንቱንና የገንዘብ ያገር ወይም የጸሐፊውን ምስክርነት በመቀበሉ በማናቸውም ዓይነት አላፊነት ተጠያቂ አይሆንም ።

ቀ/ ዋጋ እየተቀበለ ሥራውን በሙሉ ወይም በክፍሉ ከሚያካሂድለት ወይም ከሚያካሂዱለት ከሌላ ኮርፖሬሽን ወይም የንግድ ማኅበር ወይም ትረስት ጋር በየጊዜው ኮርፖሬሽኑ መዋዋል ይችላል ፤

በ/ በዚህ በኮርፖሬሽኑ ሠነድ ላይ በሌላ ክፍልና በየጊዜውም በሚወጡ ዝርዝር ደንቦች ላይ ከሚመለከተው በቀር የኮርፖሬሽኑ ሥራ ሙሉ ሥልጣን ተሰጥቷቸው የዲሬክተሮቹ ጉባዔ ይካሄዳል ። ስለዚህ የዲሬክተሮች ጉባዔ በየጊዜው እንደተሰማው የሚከተለውን ይፈጽም ዘንድ ተጣርቶ ሥልጣን ተሰጥቶታል ፡-

www.chilot.me



፮/ ባለድርሻዎቹ ያስናዱት ፤ ወይም ያስናዱዋቸው ዝርዝር ደንቦች የማሻሻሉን ሥልጣን በወሰኑበት ዝርዝር ደንብ ከተከለከለው በቀር ማናቸውንም የኮርፖሬሽኑን ዝርዝር ደንብ ለማሻሻል እንዲችል ፤

፯/ ለኮርፖሬሽኑ ከሚቀረው የተጣራ ትርፍ ገንዘብ ላይ ለባለድርሻዎች ለማከፋፈል ወይም ለማናገጃው ገንዘብ መጠባበቂያ ይሆን ዘንድ ወይም በዚህ ሁኔታ ከተወሰነው ከማናቸውም ክፍል ጋራ ለማይቃወስ ሌላ ጉዳይ ይሆን ዘንድ ለመወሰን እንዲችል ፤

፰/ ከኮርፖሬሽኑ ዲሬክተሮች የሚበዙት ለኮርፖሬሽኑ ጥቅም ነው በማለት የኮርፖሬሽኑን ሥራ ወደ ሌላ ባለድምፅ ትረስት እንዲተላለፍ ባደረጉ ጊዜ በማስተላለፍ ፤ ወይም ዕቃውን በማዘዋወር ምክንያት ፤ ወይም የተባለው ትረስት በመፍረሱ ምክንያት የሚደርሰውን ወጪ ኮርፖሬሽኑ እንዲከፍል ለማድረግ እንዲችል ፤

፱/ ከትልቁ መዝገብ ዋና ፤ ወይም ኮፒ በቀር ባለድርሻዎች ሊመለከቷቸው የሚችሉትን አሁን ያሉትንና ወደ ፊትም የሚኖሩትንም የሒሳብ ደብተሮች ስንቱንና እስከየት በምን አኳኋንና በምን ቦታ የኮርፖሬሽኑ ለድርሻዎች መመርመር እንደሚፈቅድላቸው መወሰን እንዲችል ፡ ማናቸውም ባለድርሻ በኮርፖሬሽኑ ሕግ ፤ ወይም የዲሬክተሮች ጉባዔ ውሳኔ የኮርፖሬሽኑ ባለድርሻዎች በድምፅ ብልጫ ካልተፈቀዱለት በቀር የሒሳብ ደብተሮችንና ማስረጃዎችን መመርመር አይችልም ።

ተ/ ዲሬክተሮቹ በዲሬክተርነት ፣ በሠራተኛነት ፣ በባለድርሻነት ፣ በአባልነት ፣ በባለአደራነት ፤ በባለጥቅምነትና በሌላም መንገድ አብረው ከተያያዙበት ኮርፖሬሽን የንግድ ማኅበር ፤ ትረስት ሌላም ማኅበር ጋር ኮርፖሬሽኑ በሽያጭነትም ቢሆን በገዢነት መዋዋል ይችላል ። ዲሬክተሮቹ ከሁለቱም ወገን ባለጥቅም መሆናቸው ዕንቅፋት አይሆንም ። ይህም ምክንያት ሆኖ የንግዱ ግንኙነት በዚህ አይታጎደም ። እንደዚሁም በማናቸውም ዲሬክተር በዚህ አደራረግ በሚያገኘው ጥቅም በኮርፖሬሽኑም ሆነ በባለድርሻዎቹም ተጠያቂነት የለበትም ። ቢሆንም የኮርፖሬሽኑ ዲሬክተርነት ወይም ሠራተኛነት ካልተሰጠው ባለድርሻ በቀር ፤ ዲሬክተር ወይም ሠራተኛ የሆነ እንደሆነ ፤ ይህንኑ ዲሬክተሮች ሁሉ እንዲያውቁት መግለጽ አለበት ።

በሌላ ኮርፖሬሽን ንግድ ትረስት ወይም የንግድ ማኅበር ያነስተኛ ድርሻ ባለቤት ፤ ወይም ጥቅም መሆን ይህን ኮርፖሬሽን የሚቃወም ሆኖ አይቆጠርም ።

ቸ/ ዕቃን እንደዚሁም የኮርፖሬሽኑን ርስትና ማናቸውንም አለኝታን የባለደንበኛነት መብትም ጭምር ለመሸጥ ወይም ስለመለወጥ በድምፅ ብልጫ በተቆረጠ ጊዜ ዋጋው በሙሉ ፤ ወይም በክፍሉ የሌላ ኮርፖሬሽን ንግድ ፣ ትረስት ፣ ወይም የንግድ ማኅበር ባለድርሻ ፣ ባለገንዘብ ፣ ባለመያዣ ፣ መሆኑን በሚያስረዳ ሁኔታ ሊከፈል ይቻላል ።

ነ/ ኮርፖሬሽኑ እንዲፈርስ ወይም የሚያፈርሰው አደራረግ በድምፅ ብልጫ በተቆጠረ ጊዜ ከአበዳሪዎችና በላጭ አስተያየት ከተሰጣቸው ባለድርሻዎች መብት በቀር የዲሬክተሮች ጉባዔ የኮርፖሬሽኑን በጥሬ ገንዘብ ፤ ወይም በዕቃና በርስት ያለውን ሀብት በሙሉ ፤ ወይም በክፍሉ ባንድ ጊዜ ፤ ወይም በቀስታ ለባለድርሻዎች ለመከፈልና የድርሻውን ልክ ለማወቅ የተባለውን የኮርፖሬሽኑን ሀብት የዋጋ ግምት ያወጣ ዘንድ ሥልጣን ይሰጠዋል ። አከፋፈሉም በፍጹም ባይሆን እንኳ የተቻለውን ያህል ትክክል እንዲሆን ያስፈልጋል ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

የዚህ አንቀጽ ንዑስ ክፍል (ቀ) የእንግሊዝኛው ፍች «ዋጋ እየተቀበለ» የሚል አነጋገር የለውም ።

www.chilot.me



## ፪/፲፩ (፲፱፻፴፫) ሕ. ፳፮*

## በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. ስለሕዝብ ጤና ጥበቃ በወጣው አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦች ።

እነዚህ ደንቦች የ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. የሕዝብ ጤና ጥበቃ አዋጅ የ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. አዋጅ ቁጥር ፳፮ አንቀጽ ፫ (ተ) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በአገር ግዛት ሚኒስቴር የወጡ ናቸው ።

፩/ እነዚህ ደንቦች «በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. ስለውሽ በሽታ የወጡ» ደንቦች ተብለው ሊጠቀሱ ይቻላል ።

፪/ በነዚህ ደንቦች አኳኋን ውሽ ሲባል ሴት ውሽና ቡችላ ጭምር ነው ።

፫/ ማንኛውም ማስረጃ ምልክት ያለበትና የሌለበትም ውሻ ቢሆን የውሻ በሽታ ይዞት በአደባባይ ውስጥ የተገኘ እንደሆነ ማንኛውም የፖሊስ ሹምና ወይም ይህንን ሥራ እንዲሠራ ከፖሊስ ጠቅላይ ሹም የተፈቀደለት ማንኛውም ሰው ሊገድለው ይችላል ።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፱ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ.ም.

---

* የመግቢያ የግርጌ ማስረጃ

የሕዝብ ጤና ጥበቃ አዋጅ ፣ ፪/፪ (፲፱፻፴፬) አ. ፳፮ አን. ፫ (ተ) በ፯/፲፪ (፲፱፻፴፱) አ. ፺፩ አን. ፲፯ ተሻረ ፤ የመሻሪያው አንቀጽ በተሻረው አንቀጽ መሠረት የወጡት ደንቦች ሁሉ በሥራ ላይ እንዲቆዩ በግልጽ ይናገራል ።

ቀደም ሲል ባገር ግዛት ሚኒስትር ይከናወን የነበረው የጤና ጥበቃ ሥራ በ፯/፯ (፲፱፻፴፰) ት. ፩ ለሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስትር ተዛወረ ።

የዚህ ሕግ ክፍል ማስታወቂያ አንቀጽ ፩ የአማርኛው ቅጅ ንዑስ አንቀጽ ፪ የለውም ።

www.chilot.me



«ተሸከርካሪ» ማለት ማናቸውንም ዓይነት አይሮፕላን በባቡርና ሌላም የማመላለሻ መሣሪያ ሁሉ ማለት ነው ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፯/፯ (፲፱፻፵፱) ት. ፬ ፡ ፫ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፩ ፤ «የሕዝብ ጤና ጥበቃ ምክትል ሚኒስትር» እና «የሕዝብ ጤና ጥበቃ ክፍል» እየተባለ ቀድሞ በዚህ አዋጅ ይነበብ የነበረው «የሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስትር እና «የሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር» ተብሎ እንዲነበብ ተደርጐ ተሻሻለ ።

በሰባተኛው ፓራግራፍ ለ «የጸና የጤና ምስክር» የሚለውን ትርጓሜ ሲሰጥ በእንግሊዝኛው ቅጂ «የስድስት ወሩ የመጨረሻ ስድስት ቀኖች አይቆጠሩም» ይላል ።

## ክፍል ፪

### ስለ ኳራንቲን ።

፫/ ማናቸውም ሰው ወይም ተሽከርካሪ በተፈቀደው የመግቢያ ስፍራ ካልሆነ በቀር ፣ በማናቸውም ስፍራ ወደ ኢትዮጵያ መግባት ክልክል ነው ።

፬/ በነዚህ ደንቦች የታቀዱት መከላከያዎች በሚገባ ተደራጅተው ተፈጻሚነታቸውን የሚያረጋግጥ ማስታወቂያ በጤና ጥበቃ ሚኒስትር በጋዜጣ እስኪወጣ ድረስ ፣ በሽታው ከገባበት አገር ወይም ሥፍራ በእግር ፣ በከብት ፣ በማናቸውም ተሽከርካሪ የሚመጣ ፣ ወይም በዚያ ያለፈ ሰው ወይም ተሽከርካሪ ወደ ኢትዮጵያ መግባት ክልክል ነው ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፯/፯ (፲፱፻፵፱) ት. ፬ ፡ ፫ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፩ በግ. ሳ. ተሻሻለ ፤ (ቀድሞ በዚህ አንቀጽ «የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ምክትል ምኒስትር» እየተባለ ይነበብ የነበረው በግልጽ ሳይነገር የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ተብሎ እንዲነበብ ተደረገ ።)

፭/ ሀ/ ያንድ ተሽከርካሪ ኃላፊ የሆነ ሰው ወደ ተፈቀደው የመግቢያ ሥፍራ በደረሰ ጊዜ ፤

፩/ ተሽከርካሪው ተመርምሮ እንዲያልፍ እስኪፈቀድለት ድረስ እተሽከርካሪው ውስጥ ያሉት ሰዎች እውጭ ካሉት ጋር እንዳይገናኙ ወይም ጭነቱ እንዳይራገፍ ማድረግ ፤

፪/ የኳራንቲን ሹም የሚሰጠውን ትእዛዝ መፈጸም ደግሞም ፤

፫/ ወረቀቶችን ሁሉ ለኳራንቲኑ ሹም ማቅረብና የሚጠይቀውን ሁሉ በመሐላ መልስ መስጠት ፣ ደግሞም ስለሕዝብ ጤና ጥበቃ አስፈላጊ የሆነትን እሱ የሚያውቃቸውን ሁሉ ማስታወቅ አለበት ።

ለ/ በእንደዚህ ያለ ተሽከርካሪ የሚገኙ ሠራተኞችና መንገደኞች የኳራንቲን ሹም አስፈላጊ መስሎ ሲታየው የሚያቀርብላቸውን ጥያቄ ምለው መልስ መስጠት ግዴታቸው ነው ።

፮/ ቀጥሎ በተመለከቱት ላይ የኳራንቲን ሥርዓት ይፈጸምባቸዋል ፤

ሀ/ የሚገባ በሆነ ዓይነት ወይም በተተካከለ ሁኔታ የጤና ሠነዶች ያልያዘ ተሽከርካሪ ፤ ደግሞም

ለ/ የጸና የጤና ምስክር ሳይዝ የመጣ ሰው ፤ ወይም የያዘው የጤና ምስክር ያልተስተካከለ ሲሆን ፤

www.chilot.me



ሐ/ በመታገድ ውስጥ ባሉ ሰዎች መሐከል ፤ አዲስ የኮሌራ ሕመም የተነሳ እንደሆነ ወይም መነሳቱ ያጠራጠረ እንደሆነ በቀሩት ሰዎች ላይ ወይም ከነዚህ አዲስ ሕመምተኞች ጋር በተገናኙት ሰዎች ላይ የመታገድ ጊዜ ይቀጠልባቸዋል ።

ክፍል ፫

የንግድና የመንገደኞች ዕቃ ከበሽታ እንዲለይ ስለመጠበቅ ።

፲፪/ ሀ/ በሦስተኛው አንቀጽ የተጻፈውን ሳይለቅ በመሬትም ሆነ በአየር መመላለሻ ወዳገር ውስጥ የሚገባ ፤ ወይም ባገር ውስጥ የሚተላለፍ የንግድና የመንገደኛ ዕቃ ከመግባት አይከለከልም ፤ ወይም ከበሽታ አስተላላፊነት ለማንጻት አስፈላጊ ሆኖ ከሚገኘው ጊዜ የበለጠ በድምበሮችና በወደብ ከተማዎች ታግዶ አይቀይም ።

ለ/ ገላ ንክ ልብስና ሌላም ዓይነት ልብስ ያልጋ ልብስ ፤ ፍራሽና ትራስ ፤ በቅርብ ጊዜ ተለብሶ የነበረ ሁሉ ከበሽታ አስተላላፊነት እንዲነጻ ይደረጋል ።

ስለሆነ ግን የትኩስ ዓሣ ፤ የዛጐል ዓሣ ፤ ቅጠላቅጠል ወይም የኳራንቲን ሹም ዘር ዝሮ ያስታወቃቸው ለሰው ምግብ የሚሆኑ ሌሎች ነገሮች ሁሉ የኮሌራን ጀርም ያጠፋል ተብሎ በሚገመት አኳኋን እንዲነጻ ካልተደረገ ወዳገር ውስጥ እንዳይገባ ይከላከላል ።

፲፫/ እንዲህ ባለው አያያዝ እንዲነፃ ለማድረግ የኳራንቲን ሹም የሚስማማ መስሎ በታየው ሁኔታና ስፍራ ሆኖ በተቻለ መጠን በዕቃ ላይ የሚመጣው ጉዳት ያነሰ በሚሆንበት አኳኋን ይፈጸማል ።

፲፬/ የኳራንቲን ሹም አስፈላጊ መስሎ ቢታየው የልብስንና ዋጋቸው ቀላል የሆኑትን ሌሎች ዕቃዎች ለንግድ ጉዳይ በብዙ ተጭነው ያልመጡ የሆኑትን ጨርቃጨርቅ ጭምር እንዲቃጠሉ ለማድረግ ይችላል ።

፲፭/ ሀ/ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ከበሽታ በማንጻት ወይም በሌላ አያያዝ ወይም በ፲፬ኛው አንቀጽ መሠረት በተጻፈው አኳኋን ዕቃ በማጥፋት ኪሣራ ይከፈል እንደሆነና ደግሞም የሚከፈለውን መጠን ይወስናል ። በነዚህም ነገሮች የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል ።

ለ/ የንግድ ዕቃ ወይም የመንገደኛ ሻንጣ በነዚህ ደንቦች በተጻፈው መሠረት ደንብ ሲፈጸምባቸው የኳራንቲን ሹም ባለጥቅሙ በጠየቀው ጊዜ የተፈጸመባቸውን ሁኔታዎች የሚያሳይ የምስክር ወረቀት በነፃ ይሰጠዋል ።

ሐ/ ከበሽታ ስለማንጻትና ስለሌላም ሥራዎች የሚከፈለውን ገንዘብ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ይወስናል ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፯/፯ (፲፱፻፵) ት. ፩ ፤ ፫ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፩ በግ.ሳ. ተሻሻለ ፤ (ቀድሞ በዚህ አንቀጽ «የጤና ጥበቃ ምክትል ሚኒስትር» እየተባለ ይነበብ የነበረው በግልጽ ሳይነገር «የጤና ጥበቃ ሚኒስትር» ተብሎ እንዲነበብ ተደረገ ።)

ክፍል ፬

ልዩ ልዩ ።

፲፮/ የኮሌራ የመጀመሪያ ምልክቶች የታየባቸው ፤ ነገር ግን የኮሌራ ጀርም ያልተገኘባቸው ወይም የተገኙባቸው ጀርሞች በትክክል የኮሌራ ጀርም የማይመስሉ ሆነው የተገኙባቸው ፤ ስለኮሌራ እንዲደረግ የታዘዘው ይፈጸምባቸዋል ።

www.chilot.me



፲፯/ አንድ ተሸከርካሪ ወዲያው እንደመጣ ተመርምረው የሚገኙት በሽታ አስተላላፊዎች የኳራንቲን ሹም እንደሚወስነው የጥበቃ ወይም የምርመራ ሥርዓት ይፈጸምባቸዋል ።

፲፰/ በሽታ በተገኘባቸው ተሽከርካሪዎች የሚከተለው ሁኔታ ይፈጸምባቸዋል ።

ሀ/ የሕክምና ምርመራ ፤

ለ/ ሕመምተኞቹን በፍጥነት ከሰው መለየት ፤

ሐ/ የተሽከርካሪው ሠራተኞችና መንገደኞች ተሽከርካሪው ከደረሰበት ቀን አንስቶ እስከ ፭ ቀን ድረስ በመታገድ ወይም በምርመራ ሥርዓት እንዲቆዩ ማድረግ ፤ ስለሆነ ግን የጸና የጤና ምስክር ያላቸው ሰዎች የምርመራ ሥርዓት እንጂ የመታገድ ሥርዓት አይፈጸምባቸውም ።

መ/ የተሠራበት ያልጋ ልብስ ፣ ትራስና ፍራሽ ፤ የሚለበስ ጨርቅ ፤ ሌሎችም ነገሮች ፣ ምግቦችም ጭምር ለመግቢያ በተፈቀደው ስፍራ የኳራንቲን ሹም በቅርብ ጊዜ ውስጥ ከበሽታ ተነካክቷል ብሎ የሚጠረጠረው ሁሉ ከበሽታ አስተላላፊነት እንዲነጻ ይደረጋል ፤

ሠ/ ኮሌራ የያዛቸው ሰዎች የመጡበት ተሽከርካሪ ወይም የኳራንቲኑ ሹም ከበሽታ ተነካክቷል ብሎ የሚጠረጥረው ተሽከርካሪ ከበሽታ እንዲነፃ ይደረጋል ።

ረ/ ጭነት በኳራንቲን ሹም ተመልካችነት ይራገፋል ። እሱም ተሸካሚዎቹ በበሽታ እንዳይነደፉ ለመከልከል አስፈላጊውን ያደርጋል ። እነዚህ ሠራተኞች እራገፈው ከጨረሱበት ቀን አንሥቶ ከምስት ቀን ለማይበልጥ ጊዜ በመታገድ ወይም በምርመራ ሥርዓት እንዲቆዩ ይደረጋል ።

ሰ/ በተሽከርካሪው ውስጥ የተገኘ የመጠጥ ውሀ በተጠረጠረ ጊዜ ከበሽታ እንዲነጸ ከተደረገ በኋላ ይፈስሳል የውሀ በርሚሎችም እንደዚሁ ከበሽታ እንዲነጹ ከሆኑ በኋላ ጤናማ የሚጠጣ ውሀ ይሞላባቸዋል ።

፲፱/ ኮሌራ አለበት በማለት በሚያጠራጥረው መኪና የመጡ መንገደኞችና ሠራተኞች መኪናው ከገባ በኋላ ከ፭ ቀን ላልበለጠ ጊዜ በምርመራው ውስጥ ሊቆዩ ግዴታ አለባቸው፣ ሠራተኞቹም በዚሁ ጊዜ ከመኪናው ወይም ከኳራንቲን ሹም በተወሰነላቸው ቦታ መቆየት አለባቸው ።

፳/ በሽታ ካለበት ቦታ በአየር ወይም በምድር ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ሰዎች ለኳራንቲን ሹም የኮሌራ መድኃኒት ክትባት እንዳላቸው የሚበቃ ማስረጃ ሲሰጡ ለጊዜው የቆመውን ትእዛዝ ከመፈጸም በመሰላቸው መጠን የኳራንቲን ሹሞች ነፃነት ሊሰጡ ይችላሉ።

፳፩/ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ከዚህ በላይ የተጻፈውን ደንብ ሳይታወም በተፈቀደላቸው መግቢያ በታዎች ለመመርመርና ለማገድ ለሰዎች ፣ ለሸቀጥ ፤ ለዕቃም እንዲመረምሩና በሽታውን የማያስተላልፍ መድኃኒት እንዲደረግባቸው ፤ ሰዎችም እንዲከተቡ መመርመሪያና ማገጃ ዝግጁ ጣቢያዎች ያቆማል ።

## የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፷/፯ (፲፱፻፶፱) ት. ፬ ፣ ፫ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፭ በግ.ሰ. ተሻሻለ ፤ (ቀድሞ በዚህ አንቀጽ «የጤና ጥበቃ ምክትል ሚኒስትር» እየተባለ ይነበብ የነበረው ፣ በግልጽ ሳይነገር «የጤና ጥበቃ ሚኒስትር» ተብሎ እንዲነበብ ተደረገ ።)

፳፪/ አስፈላጊነቱ እየታየ የኳራንቲኑ ሹም በባቡርና በሌላም መኪና የተያዘውን የሚጠጣውን ውሀ ሁሉ ንጹሕና ጠቃሚ እንዲሆን አስፈላጊውን መድኃኒት ሊያደርግበት ይችላል ።

www.chilot.me



ጠቅላይ ገዥዎችና ከንቲባዎች ወይም የከተማ ሹሞች የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በወከለው የጤና ጥበቃ ሹም አማካይነት በግዛት አገራቸው ውስጥ የተላላፊ በሽታዎችን ሁኔታ ስለመከላከል በመንግሥት በኩል ያለውን ተግባር ለመፈጸም ኃላፊዎች ናቸው ።

፩/ በዚህ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ መሠረት ለነዚህ በሽታዎች ለምርመራ ለሕክምና ለክትባት መድኃኒት ለመርጨት ተባዮችን ለማስወገድ በሽተኞችን አግልሎ ለማከም የሚደረገው እርዳታ በነፃ ነው ።

፯/ ተላላፊ በሽታዎች እንዳይስፋፉ ላስፈላጊው ጥንቃቄ ለመፈጸም ወይም ለመከላከል የሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ቀጥሎ የሚገኙትን ጉዳዮች በልዩ ሐኪም ወይም በወኪሉ ለማዘዝ ሥልጣን አለው ።

ሀ/ የተላላፊ በሽታ ያደረባቸውን ፤ ወይም የተነደፉትን ወይም ተነድፈዋል በመባል የሚጠረጠሩትን ሰዎች መቆጣጠርና መመርመር በሆስፒታል ወይም በሌላ ቦታ ተወስነው እንዲቀመጡና እንዲጠበቁ ማድረግ ፤

ለ/ የየመኖሪያ ቤቶችን መጐብኘትና ማስመርመር ፤

ሐ/ በማናቸውም ሰው አጥር ግቢ የሚገኘውን የውኃ ማስቀመጫ ገንዳዎችን (ማከማቻዎችን) የውሀ ጉድጓዶችን ፤ ስገራ ቤቶችን ፤ የሽንት መሽኒያዎችን ፤ የጉድፍ መጣያ ጉድጓዶችንና ለጽዳት ተግባር አስፈላጊ የሆኑትን ማስመስመርና ተላላፊ በሽታዎችን ለማራባት የሚያጠራጥሩትን ወይም የሚያስጉትን ስለበሽታው መበፋፋትና መከላከል ፤ ማስወገድ ጠቃሚ መስለው የሚታዩትን ነገር ሁሉ እንዲወገዱ ማስደረግ ፤

መ/ በተላላፊ በሽታ ለሚሰቃዩት ወይም ለሚጠረጠሩት ሰዎች የሕክምና ዕርዳታ ማድረግና የማስታመሚያ ሥፍራ መስጠት ፤

ሠ/ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት ውስጥ የሚጐዳኙትን የውጭ አገር ሰዎች መቆጣጠርና መከታተል ፤

ረ/ ወደ ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት ውስጥ በሚገቡት ፤ ወይም በሚወጡት ሰዎች ላይ የሚደረገው መቆጣጠር በኢንተርናሲዮናል ሳኒታሪ ኮንቬንሽን በተደነቡት ደንቦች መሠረት መሆኑን መጠባበቅ ፤

ሰ/ የመድኃኒት መርጨትን አይጦችን ማጥፋትንና የክትባትን ሥራ መከታተል ፤

ሸ/ የሬሣን ቀብርና የበድንን መወገድ መቆጣጠር ፤

ቀ/ ከዚህ በተረፈ የሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል ወይም ለመቃወም ጠቃሚ መስሎ ወደሚታየው ሥፍራ ሁሉ ሰው መላክና አስፈላጊውን ማድረግ ።

፰/ ወደ ሰው የሚተላለፍ ተላላፊ በሽታ በእንስሳዎች መካከል ቢነሣ የእርሻ ሚኒስቴር ከበሽታው ለመጠንቀቅ ለሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ማስታወቂያ ሲልክለት ይኸው ሚኒስቴር በሽታውን ለመከላከል ከእርሻ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ይሠራል ።

## ፪ኛ/ ክፍል

## በሽታ ለተላለፈበት አገር የወጣ ልዩ ደንብ

፱/ ሀ/ የሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት በማናቸውም ክፍል አገር አደገኛ የሆነ ተላላፊ በሽታ መነሣቱን ወይም መግባቱን በማናቸውም አኳኋን ከተረዳ በኋላ በነጋሪት ጋዜጣ ወይም በሌላ በተራ ጋዜጣና ማስታወቂያ አሳትሞ በሥፍራው ላይ በሽታ የተነሳበት መሆኑን አስታውቆ በዚህ ደንብ የተመለከቱት ዘዴዎች በቶሎ እንዲፈጸሙ ያደርጋል ።

ለ/ የሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሽታ በተነሣበት ግዛት ክፍል የተላላፊ በሽታዎች ተከላካይ ባለሥልጣን ወይም ለዚሁ ሥራ የሚጠቅሙ ባለሥልጣኖች ይሾማል ።

፱/ አደገኛ ተላላፊ በሽታ ሲነሣ ማስታወቅ ግዴታ ስለሆነ ፤ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ሰዎች ሕመምተኛ መኖሩን ሲያረጋግጡ ወዲያው እንደሰሙ በቀበሌው ለሚገኘው የተላላፊ በሽታዎች ተከላካይ ባለሥልጣን ወይም ባቅራቢያው ለሚገኘው የፖሊስ ጣቢያ ማስታወቅ ይገባቸዋል ።

ሀ/ በሽተኛውን የሚያክም ሐኪም የሕክምናውን ሥራ ሳያቋርጥ ፤

ለ/ ሕመምተኛው ዕድሜው ከዐሥራ ስምንት ዓመት በላይ እንዳይሆን ፤

ሐ/ እንደዚህ ያለ በሽተኛ የሚኖርበት የቤተ ሰብ አሳዳሪ ፤

መ/ እንደዚህ ያለ በሽተኛ የሚገኝበት የማንኛውም ሥፍራ ቤትና ቦታ ኃላፊ ።

፲/ አንድ አደገኛ ተላላፊ በሽታ መነሣቱን ያንድ የጦር ሠራዊት ሹም ፤ የፖሊስ ሹም ፤ አስታማሚ ሞግዚት ፤ የጥርስ ሐኪም ፤ ኬሚስት ፤ መድኃኒት ቀማሚ ፤ የጽዳት ሹም ፤ ወይም የአንድ ዲስፔንስሪ አዛዥ ሲሰማ ወዲያው በቀበሌው ለሚገኘው ለተላላፊ በሽታዎች ተከላካይ ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት ።

፲፩/ ሀ/ አንድ ሰው አደገኛ በሆነ ተላላፊ በሽታ መሰታየቱን ወይም በበሽታ መጠርጠሩን ሐኪሙ ወይም የተላላፊ በሽታዎች ባለሥልጣን ሲያውቀው ይኸው ባለሥልጣን ታማሚው በሆስፒታል መታከም ፤ ወይም በሆስፒታል ውስጥ ደንበኛ መቀበያ በሆነው ሥፍራ ተለይቶ ሊጠበቅ ወይም በተለየ ቦታ መኖር ያሻው እንደሆነ መወሰን አለበት ።

ለ/ የተላላፊ በሽታዎች ተከላካይ ባለሥልጣን በ(ሀ) ክፍል በተጠቀሰው ንዑስ አንቀጽ መሠረት ፤ የሚፈጸመውን አገልግሎትና ዘዴዎች ባለማቋረጥ ለሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በየጊዜያቱ ማስታወቅ አለበት ።

፲፪/ ሐኪሙ ወይም የተላላፊ በሽታዎች ተከላካይ ባለሥልጣን አንድ ሰው አደገኛ በሆነው ተላላፊ በሽታ መታመሙን ወይም መጠርጠሩን በተረዳ ጊዜ አስፈላጊ ቢሆን በግዴታ በሽተኛውን ይዞ ወደ ሆስፒታል እንዲወሰድ ወይም ለዚህ ጉዳይ በተዘጋጀው ቦታ ተለይቶ እንዲቀመጥ ያደርጋል ። በሽተኛው ከፈረበት ሆስፒታል ወይም ቦታ ያለ ኃላፊው ትእዛዝ ሊለቀቅ ወይም ሊሰናበት አይችልም ።

፲፫/ ሐኪሙ ወይም የተላላፊ በሽታዎች ተከላካይ ባለሥልጣን በ፲፪ኛው አንቀጽ የተጠቀሱትን በሽተኞች ለመውሰድና በተለዩ ሆስፒታሎች ወይም ቦታዎች ለመጠበቅ የፖሊስን ዕርዳታ ሊጠይቅ ይችላል ።

## ፫ኛ/ ክፍል

## ልዩ ልዩ

፲፬/ ሀ/ ማንም ሰው እነዚህን ደንቦች የሚቃወም ወይም ተላልፎ የሚገኝ ፤

ለ/ በሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወይም በነዚህ ደንቦች መሠረት አንድ ሐኪም ፤ ወይም የተላላፊ በሽታዎች ተከላካይ ባለሥልጣን ያወጣውን ትእዛዝ እያወቀ የሚያፈርስ ፤

ሐ/ በዚህ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ የተሰጠውን የሚፈጽመውን ሠራተኛ ሥራ እንዲሰናከል የሚያደርግ ከወንጀለኛ ተቀጥሮ ተከሶ ስለሕዝብ ጤና አጠባበቅ በወጣው ጣው በ፺፩ ቁጥር አዋጅ በ፲፫ኛው አንቀጽ ይቀጣል ።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፩ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ. ም.

www.chilot.me



፱/ ሀ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ሚኒስትሩ በነጋሪት ጋዜጣ ቢሆንም ወይም በሌሎች ጋዜጣዎች የፈቃድ ወረቀት የተቀበለውን ሰው ሞያውንና ስሙን እንዲሁም የፈቃድ ወረቀት የተወሰደበትን ወይም እንዲቆይ የተደረገውን ሁሉ ስሙንና አድራሻውን ጭምር በመዝገብ እንዲጻፍ ያደርጋል ።

ለ/ በያመቱ በመስከረም ወር በሚታተመው የነጋሪት ጋዜጣ በመዝገቡ ውስጥ ምን ያህል የሕክምና ሠራተኞች እንደቀሩ ስማቸውንና አድራሻቸውን ሞያቸውንም ጭምር ሚኒስትሩ እንዲታተም ያደርጋል ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

ሁል ጊዜ በመስከረም ወር ውስጥ በሚታተመው ነጋሪት ጋዜጣ ውስጥ የሚወጣው የሕክምና ሠራተኞች ስም ዝርዝር ጊዜያዊ በመሆኑ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንዲታተም አልተደረገም ።

፲/ ሀ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ማንኛውም ሰው ቢሆን የፈቃድ ወረቀት ካልያዘ በቀር ሐኪም ነኝ ፤ የጥርስ ሐኪም ነኝ ፤ መድኃኒት ቀማሚ ነኝ ፤ አዋላጅ ነኝ ፤ የዓይን ሐኪም ነኝ፤ ወይም አስታማሚ ነኝ ብሎ በቃልም ሆነ በደብዳቤ የሕክምና ሞያውን ለማስታወቅ አይችልም ።

ለ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ማናቸውም ፈቃድ የተቀበለ ሰው በያዘው በተቀበለው ፈቃድ ሥራውን ይሠራል እንጂ ሌላ ችሎታ አለኝ በማለት ሊያመለክት አይችልም ።

፲፩/ የሕክምና ሠራተኞች በገዛ ሥልጣናቸው አስታማሚዎች ፤ ተጠባባቂዎችንና ተማሪዎችን ሊያሠሩ ይችላሉ ። ዳሩ ግን እነዚህ ፈቃድ የሌላቸው ሰዎች መድኃኒት ለመስጠትና በሽተኛንም ለመቅደድ አይፈቀድላቸውም ።

፲፪/ ሚኒስትሩ ወይም እርሱ ሥልጣን የሰጣቸው ለምርመራ ሲሉ ምንጊዜም ቢሆን የሕክምና ሠራተኛውን አጥር ግቢ ይመረምራሉ ።

፲፫/ ሀ/ ፩/ ማንኛውም ሰው በውሸት በጥያቄው ወረቀት ውስጥ ያለችሎታው ችሎታዬ ነው ብሎ የሚያመለክት ሰው ፤

፪/ እንዲሁም በዚህ አዋጅ ውስጥ የተነገረውን ደንብ ሁሉ ያልፈጸመ ሰው ፤ በወንጀለኛነት ተቀጥሮ ሲመሰክርበት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በሚያዘው መሠረት ይቀጣል ።

ለ/ በዚሁ አንቀጽ መሠረት ወንጀሉን የመረመረው ፍርድ ቤት ወንጀለኛው የተወነጀለበትን መጣሪያ እንዲወረስ ትእዛዝ ይሰጣል ።

ሐ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ፍርድ ቤቱ ሐሳቡን ለሚኒስትሩ ያመለክታል ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በወ.መ.ሕ. ፲፯/በተ. ፻. ፩ (፲፱፻፵፱) አን. ፭፻፲፰ ፤ ፭፻፴፰ እና ፭፻፷፱ በግ. ኅ. ተሻሻለ ፤ (እነዚህ አንቀጾች የሕክምናንና የጤና አጠባበቅን ሥራ ያላገባብ ስለመሥራትና ስለሕክምና ጥበብ የወጡትን ደንቦች ስለመጣስ የወጡትን ቅጣት ይገልጻሉ ።)

፲፬/ የዚሁ አዋጅ ሥራ እንዲካሄድ ሚኒስትሩ ደንብ ያወጣል ። ይህም ደንብ የመድኃኒት ሺያጮችንም ይጨምራል ።

፲፭/ እንደሐኪም ፤ እንደቀዳጅ ፤ እንደጥርስ ሐኪም ፤ እንደዓይን ሐኪም ፤ ሆነው በ፲፱፻፴፩ ዓ.ም. ስለሕክምና ሥራ በተነገረው አዋጅ በመዝገብ ገብተው የፈቃድ ወረቀት የተቀበሉ ፤

www.chilot.me



ሰው በ፲፱፻፵ ዓ. ም. ስለሕክምና ሠራተኞች መመዝገብ በወጣው አዋጅ መሠረት በኢትዮጵያ አገር የሕክምና ሥራውን እንዲቀጥል ተፈቅዶለት ፤ የፈቃድ ወረቀት ተሰጥቶታል

አዲስ አበባ............ቀን ፲፱........ዓ.ም.

ማኅተም

ፊርማ
የሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስትር

የፈቃድ ወረቀት ያዥው
ፊርማ

የመዝገብ ቁጥር............

ግብር............የኢት/ብር..........

ጽሑፍ (ሐ)

ግብር

በ፲፱፻፵ ዓ.ም. በአምስተኛው አንቀጽ መሠረት ስለሕክምና ሠራተኞች መመዝገብ በወጣው አዋጅ መሠረት ፤

ለፈቃድ ወረቀት የሚከፈል ግብር

የኢት/ብር

ለሐኪም ፤ ለቀዳጅ ወይም ለጥርስ ሐኪም ፤ ለዓይን ሐኪም ፤ ........................ ፫፻
ለመድኃኒት ቀማሚ .................................................................. ፪፻
ለአዋላጅ ........................................................................... ፩፻
ለአስታማሚ ......................................................................... ፶

አዲስ አበባ መስከረም ፳ ቀን ፲፱፻፵፩ ዓ. ም.

፰ኛ/፲፰ (፲፱፻፵፪) ሕ. ፩፻፲፰*

ስለሐኪሞች አመዘጋገብ በ፲፱፻፵፩ ዓ.ም. በወጣው አዋጅ መሠረት የወጣ ደንብ ።

ምዕራፍ ፩

ጠቅላላ መግለጫ

አንቀጽ ፩

ሥልጣን

ይህ ደንብ የወጣው ስለሐኪሞች አመዘጋገብ በ፲፱፻፵፩ ዓ.ም. በቁጥር በወጣው አዋጅ (ከዚህ በታች አዋጅ እየተባለ በሚጠራው) በአንቀጽ ፲፩ ለሚኒስትሩ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው ።

* የመግቢያ የግርጌ ማስረጃ

በ፳፱/፲፭ (፲፱፻፷፪) ሕ. ፫፻፷፭ ተሻሻለ ።

www.chilot.me



ከእንስሳት የተቀመመ (ባዮሎጂካል ፕሮዳክት) ወይም በመርፌ የሚሰጥ (ፖሬንተራል ሜዲኬሽን) ወይም ይህንን ከመሳሰሉ ነገሮች ተቀላቅሎ የተሰናዳ መድኃኒት ነው ።

፲/ «የሕክምና ዕቃዎች» ማለት ሐኪሞች የሰዎችን ወይም የእንስሶችን ሕመም ለመመርመሪያ ፣ ለማከሚያና ለማዳኛ ወይም ሕመም ለመከላከያ የሚገለገሉባቸውና የሚጠቀሙባቸው ናቸው ። ይህም ከምግቦች በስተቀር የመድኃኒት ዝግጅቶችን ፣ መጣጭ ጥጥን ፣ ልዩ ልዩ ሻሾችን ፣ የቁስል ማጣበቂያ ሽቦችንና መስፊያ ክሮችን ፣ ልዩ ልዩ የሕክምና ጨርቆችን ፣ እንዲሁም ሐኪሞች ሙያቸው በሚመራቸው መንገድ ለመቅደጃና ለቁስል መጠገኛ የሚጠቀሙባቸው ይህንንም የመሳሰሉትን ሌላ መሣሪያ ሁሉ ጨምሮ ነው ።

፲፩/ «ሚኒስትር» ማለት የሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስትር ነው ።

፲፪/ «ሚኒስቴር» ማለት የሕዝብ ጤና ጥበቃ ዋና መሥሪያ ቤቱን ነው ።

፲፫/ «ናርኮቲክ» ማለት ኢትዮጵያ በተቀበለችው የናርኮቲክ ኮንቬንሽን መሠረት በናርኮቲክነት የተመደበ ማናቸውም ዓይነት መድኃኒት ነው ። ይህም ዋናው የኦፒየም ቦርድ (አንዳንድ ጊዜ የኢንተርናሲዮናል ናርኮቲክ መቆጣጠሪያ ቦርድ የሚባለው) በየጊዜው እየሻሻለ የሚያወጣውን በኢንተርናሽናል ቁጥጥር ሥር የሚገኙትን የናርኮቲክ መድኃኒቶች ዝርዝር ይጨምራል ።

፲፬/ «ፋርማሲስት» ማለት ከዚህ በታች በአንቀጽ ፯ የተመለከተውን በመከተል ለፋርማሲስትነት የሚያስፈልጉትን ግዳጆች አከናውኖ የሥራ ፈቃድ ያገኘና በዚህም ሞያ የተመዘገበ ማንኛውም ሰው ነው ።

፲፭/ «ፋርማሲ» ማለት የመድኃኒት ዝግጅቶች እየተዋሐዱ ወይም እየተዘጋጁ ለሕዝብ የሚሸጥበት ሱቅ ወይም ማናቸውም ሌላ ሥፍራ ነው ።

፲፮/ «ፋርማሲ ቴክኒሺያን» ማለት ከዚህ በታች በአንቀጽ ፱ በተመለከተው መሠረት ለፋርማሲስት ቴክኒሺያንነት የሚያስፈልጉትን ግዴታዎች አከናውኖ የሥራ ፈቃድ ያገኘና በዚሁም ሞያ የተመዘገበ ማንኛውም ሰው ነው ።

፲፯/ «የመድኃኒት» ማዘዣ (ፕሬስክሪፕሽን) ማለት የመድኃኒት ማዘዣዎች ለመስጠት በሕግ ተፈቅዶለት በ፳፩ኛው አንቀጽ መሠረት በጊዜያዊ ዝርዝር ውስጥ ስሙ የተላለፈለት ሰው መድኃኒት ወይም የመድኃኒት ዝግጅቶች እንዲሰናዱ ፈርሞ የሚሰጠው የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ነው ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፬/፲፩ (፲፱፻፶፯) ሕ. ፫፻፷ አን. ፫ ተሻሻለ ።

የተጠቀሰው ሕግ

የሕዝብ ጤና ጥበቃ አዋጅ ፤ ፮/፲፱ (፲፱፻፴፱) አ. ፺፩ ፤ ፴ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፫ ።

## አንቀጽ ፬

## የፋርማሲና የላቦራቶሪ ክፍል

በዋናው ፋርማሲስት መሪነት በዚህ ደንብ የተመለከቱትን ሥራዎችና ግዴታዎች ወይም በሚኒስቴሩ የውስጥ ደንብ መሠረት ሊወጡ የሚችሉትንና እነዚህንም የመሳሰሉትን ተግባሮች ሁሉ የሚያከናውንና የሚፈጽም የፋርማሲና ላቦራቶሪ ክፍል በሚኒስቴሩ ውስጥ ይቋቋማል ።

www.chilot.me



ምዕራፍ ፪

## አመዘጋገብና ፈቃድ አሰጣጥ

አንቀጽ ፫

### መዝገቦች

የፋርማሲና የላቦራቶሪ መምሪያው ክፍል ፡—

፩/ በዚህ ደንብ መሠረት ለፋርማሲስቶች ፣ ለድራጊስቶች ፣ ለፋርማሲ ቴክኒሺያኖች ፣ ለች ርቻርና ለሆስፒታል ፋርማሲስቶች ፣ ለድራግ ሱቆች ፣ ለመድኃኒት አዘጋጅ ላቦራቶሪ ዎች ራሳቸውን የቻሉ ልዩ ልዩ መዝገቦች ይዞ በተገቢው መዝገብ ውስጥ የያንዳንዱን ሰው ስም አድራሻና ሌሎችም መረጃዎችን ደንቡን ተከትሎ ይመዘግባል ፤

፪/ በዚህ ደንብ መሠረት የምዝገባ ምስክር ወረቀቶችና የሥራ ፈቃዶችን ያወጣል ፤

፫/ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መዛግብት በየጊዜው አስፈላጊው መረጃ እየተሞላባቸውና እየ ተከናወነባቸው እንዲጠበቁ ለማድረግ ፤

፫/ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መዛግብት በየጊዜው አስፈላጊው መረጃ እየተሞላባቸውና እየተከናወነባቸው እንዲጠበቁ ለማድረግ ፤

ሀ/ የተመዘገበ ሰው አድራሻውን ሲለውጥ አዲሱ አድራሻ በተገቢው መዝገብ እንዲ ሰፍር ያደርጋል ፤

ለ/ ከተመዘገቡት ሰዎች የአንዱ አድራሻው ሲያጠራጥር ለመላላክና ለመጠየቅ የሚ ያስችለውን መንገድና ዘዴ በተቻለ መጠን ያፈላልጋል ፤ እንደዚሁም በያንዳንዱ መዝገብ ውስጥ የተመለከተ ሰው በተመዘገበበት ሞያ መሥራቱን ያቆመ እንደሆን ጉዳዩን እያጣራ ለቦርዱ ያስታውቃል ።

አንቀጽ ፬

### የሥራ ፈቃዶችን በሚታዩበት ሥፍራ ስለማኖር

በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት የተመዘገበና ፈቃድ ያገኘ ማናቸውም ሰው ተግባሩን በሚያከናውንበት ቦታ በማናቸውም ጊዜ የሥራ ፈቃድ ወረቀቱን ሊታይ ከሚችልበት ሥፍራ ያኖራል ።

አንቀጽ ፭

### ፋርማሲስቶች

በፋርማሲስትነት ተግባር ለመሥራትና ለመመዝገቡ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው ፤

፩/ ቦርዱ በሚቀበለው የፋርማሲ ትምህርት ቤት ወይም ኮሌጅ ስለፋርማሲስትነት አስፈላ ላጊውን ትምህርት ላከናወነ ፤

፪/ በዕድሜው ከ፳፩ (ከሃያ አንድ) ዓመት በታች ያልሆነና በሌላም በኩል ያዋጁን ግዴታ ዎች ለፈጸመ ፤

፫/ በማናቸውም ጊዜና ሥፍራ ስለፋርማሲ የወጣውን ሕግ በመጣስ ላልተፈረደበት ፤

www.chilot.me



፬/ በሚኒስትሩ የሚወሰነውን የመመዝገቢያ አበል ክፍሎ በአዋጁ መሠረት የሥራ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻውን በማቅረብ ከቦርዱ አስፈላጊውን ድጋፍ ላገኘ ማንኛውም ሰው ነው ።

አንቀጽ ፰

ድራጊስቶች

በድራጊስትነት ተግባር ለመሥራትና ለመመዝገቡ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው ፡—

፩/ ቦርዱ ያስፈልጋል ብሎ የመደበውን ትምህርት ለፈጸመ ፤

፪/ በዕድሜው ከ፳፩ (ሃያ አንድ) ዓመት በታች ላልሆነ ፤

፫/ በማናቸውም ጊዜና ሥፍራ ስለፋርማሲ የወጣውን ሕግ በመጣስ ላልተፈረደበት ፤

፬/ በሚኒስትሩ የሚወሰነውን የመመዝገቢያ አበል ክፍሎ በአዋጁ መሠረት የሥራ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻውን በማቅረብ ከቦርዱ አስፈላጊውን ድጋፍ ላገኘ ማናቸውም ሰው ነው ።

አንቀጽ ፱

የፋርማሲ ቴክኒሺያን ።

በፋርማሲ ቴክኒሺያንነት ተግባር ለመሥራትና ለመመዝገብ ፈቃድ የሚሰጠው ፡—

፩/ በዕድሜው ከ፲፰ (ከአሥራ ስምንት) ዓመት በታች ላልሆነ ፤

፪/ በማናቸውም ጊዜና ሥፍራ ሕግን ተላልፎ ላልተፈረደበት ፤

፫/ ቦርዱ በወሰነው መሠረት የሚሰጠውን የፋርማሲስት ትምህርትና የሥራ ልምምድ ጊዜ ፈጽሞ በዚሁ ሞያ ለመሥራት ሚኒስቴሩ የሚያቀርበውን ፈተና ላለፈ ማናቸውም ሰው ነው ።

አንቀጽ ፲

የፋርማሲ ቴክኒሺያኖች መብትና ግዴታ

ማናቸውም የፋርማሲ ቴክኒሺያን በሆስፒታል ወይም ሚኒስቴሩ በሚፈቅድለት ድርጅት ውስጥ ይሠራል ። በማናቸውም ጊዜ የሥራ ግዴታዎቹን የሚፈጽመው ለድርጅቱ ሥራ ኃላፊ በሆነው ሐኪም ወይም በፋርማሲስት ተቆጣጣሪነት ሥልጣን ሥር ነው ። በዚህ አኳኋን ለአ ምስት ዓመት ከሠራ በድራጊስትነት ለመሥራት እንዲመዘገብ ፈቃድ ለመጠየቅ ይችላል ።

አንቀጽ ፲፩

መድኃኒት በገጠር የሚሸጡ

መድኃኒት በገጠር ለመሸጥ ሊመዘገብና የሥራ ፈቃድ ሊሰጠው የሚችለው ፡—

፩/ ዋናው ፋርማሲስት ይገባዋል ብሎ የመሰከረለት ፤

፪/ በዕድሜው ከ፳፩ (ከሃያ አንድ) ዓመት ያላነሰና ሕግን በመጣስ ያልተፈረደበት ፤

www.chilot.me



፫/ ከሚኒስቴሩ በየጊዜው በተጨማሪ የሚወጡትን ግዴታዎች የሚፈጽም ፤

፬/ በሚኒስትሩ የተቆረጠውን የመመዝገቢያ ገንዘብ የከፈለ ሲሆን ነው ።

## አንቀጽ ፲፪

### መድኃኒቶችን በገጠር የሚሸጡ ሰዎች ተግባር

በቂ ፋርማሲና የድራግ ሱቆች በማይገኙባቸው ሥፍራዎች ለሥራው አስፈላጊ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ለሕዝብ በገጠር መድኃኒት ለመሸጥ እንዲመዘገቡ ፈቃድ ሲጠይቁ ቦርዱ ሁኔታውን መርምሮ ከተስማማ ከሚኒስቴሩ በዝርዝር የተሰጡትን መድኃኒቶች ለመሸጥ ሊፈቅድላቸው ይችላል ።

## ምዕራፍ ፫

### የንግድ ሥራ ፈቃዶች

### ክፍል «ሀ» ፋርማሲዎች

## አንቀጽ ፲፫

### ስለፈቃድ አስፈላጊነት

ማናቸውም ሰው ቢሆን ደንብ በ፲፬ኛው አንቀጽ መሠረት ፈቃድ ሳያገኝ ፋርማሲ ለማቋቋም ወይም ለማካሄድ ወይም የመድኃኒት ዝግጅቶችን ፤ ናርኮቲኮችን ወይም መርዞችን ወይም በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፴፮ ቁጥር ፩ የተጠቀሱትን መድሃኒቶች በማናቸውም መንገድ ቢሆን ለማዘጋጀት ፤ ለመሸጥ ፤ ለመለወጥ ወይም ለሕዝብ ለማከፋፈል አይችልም ። ሆኖም በዚህ በ፲፫ኛ አንቀጽ የተመለከተው ለሕክምና ዕቃዎች በዚህ ደንብ በሌላ ክፍል የተፈቀደውን ሊሽር አይችልም ።

## አንቀጽ ፲፬

### የፈቃድ አወጣጥ ሁኔታ

ፋርማሲ ለማቋቋምና ሥራውን ለመምራት ሚኒስትሩ ፈቃድ የሚሰጠው ከዚህ በታች የተመለከቱትን መረጃዎች ሲያገኝ ነው ።

፩/ ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቀው ሰው ፋርማሲስት መሆን በሚያስፈልግበት ጊዜ ፋርማሲስት ሆኖ ስለ ፋርማሲው ቴክኒክ ሥራ ራሱ ኃላፊ መሪ መሆን አለበት ። ሆኖም በንግዱ ቤት ውስጥ ያሉት ፋርማሲስቶች ቁጥር ከአንድ በላይ የሆነ እንደሆነ የፋርማሲው ፈቃድ የሚሰጠው በፋርማሲው ውስጥ የበለጠ የባለቤትነት መብት ላያዘው ነው። ምናልባት መብቱ ለሁሉም እኩል ሆኖ የተገኘ እንደሆን ፈቃዱ የሚሰጠው በሚኒስቴሩ ዘንድ በከፍተኛነት ለታወቀው ነው ፡ ሆኖም ይህ የፈቃዱ አሰጣጥ ደረጃ የተቀሩትን ፋርማሲስቶች የኃላፊነት መብት ሊቀንስ አይችልም ።

፪/ ጠያቂው ሰው ፋርማሲውን ለማቋቋም ያቀደበት ሥፍራ በኢትዮጵያ ውስጥ በቂ የመድኃኒት ገበያ በምቹ ሁኔታ ተዘርግቶ ለሕዝቡ ጥቅም እንደሚያገለግል ሆኖ ሲገኝ ፤

፫/ በፋርማሲው ውስጥ የሚያስፈልጉት መሣሪያዎች በዚህ ደንብ ላይ በተመለከተው መሠረት ተዘጋጅተው ሲገኙ ፤

www.chilot.me



## ምዕራፍ ፬

## የፋርማሲዎች አመራር

### አንቀጽ ፳፫

### እንዳይሸጡ የተከለከሉ

ከፋርማሲ ዓይነተኛ የሥራ አመራር ጋር ተቃራኒ መስለው የሚታዩትን ማናቸውንም ዓይነት የተወሰኑ ወይም በያይነታቸው የተመደቡ ዕቃዎች በፋርማሲ እንዳይሸጡ ሚኒስቴሩ ለመከልከል ይችላል ።

### አንቀጽ ፳፬

### መቆጣጠር

የመድኃኒት ዝግጅት ወይም የሚቀመሙ መድኃኒቶች በሚዘጋጁበት ጊዜ ሥራው ከዚያው ሥፍራ በማይለይ ፋርማሲስት ቅርብ ተመልካችነት ይመራል ። ፋርማሲስት በማይገኝበት ጊዜ ግን ፋርማሲው በሚኒስቴሩ ፈቃድ ለተወሰነ ጊዜ በድራጊስትነት የቅርብ ተመልካችነት በድራግ ሱቅነት ብቻ እየሠራ ሊቆይ ይችላል ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፱/፲፩ (፲፱፻፶፬) ሕ. ፫፻፳ አን. ፫ ተሻሻለ ።

### አንቀጽ ፳፭

### የሥራ ሰዓቶች

እያንዳንዱ ፋርማሲ በሚገኝበት ሠፈር የሚኖረውን ሕዝብ ፍላጐት በማመዛዘን ፤ ማናቸውም ፋርማሲ ለሕዝብ አገልግሎት የሚከፈትባቸውንና የሚዘጋባቸውን ሰዓቶች ሚኒስትሩ ሊወስን ይችላል ።

### አንቀጽ ፳፮

### መለያ ምልክት

እያንዳንዱ ፋርማሲ በደጃፉ ላይ ከዋናው በር አጠገብ ሊነበብ በሚችል ጉልህ ፊደል የመድኃኒት ቤቱን ስም በአማርኛና በእንግሊዝኛ ጽፎ ማኖር ይገባዋል ።

### አንቀጽ ፳፯

### አመልካች ጽሑፍ

እያንዳንዱ ፋርማሲ በሚዘጋበት በማናቸውም ሰዓቶች ባቅራቢያው የሚገኘውን ፋርማሲዮች ስም አድራሻና የቴሌፎን ቁጥር ግልጽ በሆነ ጽሕፈት በሌሊት ሲሆንም በመብራት አድርጎ በሚታይ ሥፍራ እንዲኖር ያደርጋል ።

www.chilot.me



አንቀጽ ፴

አመዳደብ

፩/ አንድ ፋርማሲ በውስጡ የመገበያያ ሥፍራ ፣ የመድኃኒት ዝግጅት መድኃኒቶች መቀመሚያ ሥፍራ ፣ የዕቃ መደብር ሥፍራና እንደዚሁም ለንግድ ቤቱ ሥራ ተፈላጊ የሆኑ ሥፍራዎች ሊኖሩት ያስፈልጋል ።

፪/ በመድኃኒት ዝግጅት መሠረት እየተቀመሙ የሚወጡት መድኃኒቶች የሚሠሩበት ክፍል ከቀረው ክፍል የተነጠለ መሆን አለበት ።

፫/ ፋርማሲው በውስጡ ላቦራቶሪ ያለው እንደሆነ ፣ የዚህ ላቦራቶሪ ክፍል ወይም ክፍሎች ከንግዱ ቤት ክፍል ጋር የተለያየ መሆን አለበት ።

፬/ በፋርማሲው ውስጥ ማናቸውም ወገን ለመኖሪያ ወይም ለመኝታ ሥፍራ እንዲያገለግል አይደረግም ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፪/፲፩ (፲፱፻፶፯) ሕ. ፫፻፩ አን. ፫ ተሻሻለ ።

አንቀጽ ፴፩

ከቤቱ ጋር ስለተያያዙ ዕቃዎች

ለፋርማሲው የሚያስፈልገው ከቤት ጋር ተያያዥ ዕቃ ሚኒስቴሩ ለዚሁ ሥራ አስፈላጊ ነው ብሎ ከሚመድበው አነስተኛ የዕቃ ዝርዝር ያነሰ መሆን የለበትም ።

አንቀጽ ፴፪

መሣሪያ

እያንዳንዱ ፋርማሲ ሊኖረው የሚገባውን መሣሪያ ሚኒስትሩ ለዚሁ ሥራ አስፈላጊ ነው ብሎ ከሚያወጣውና የኢንተርናሲዮናል ፋርማኮፒያም እያተመ ከሚሰጠው መሣሪያ ዝርዝር ያነሰ መሆን የለበትም ።

አንቀጽ ፴፫

የመድኃኒት ማዘዣ

እያንዳንዱ የመድኃኒት ማዘዣዎች በቅደም ተከተልነታቸው ቀንና ዘመናቸው እየተመዘገበ ቢያንስ ከሁለት ዓመት ላላነሰ ጊዜ በማኅደር ውስጥ እንዲጠበቁ ያስፈልጋል ። የመድኃኒት ማዘዣው ተደጋጋሚ የሆነ እንደሆነ ግን አንደኛው ማዘዣ ብቻ ይያዛል ። ገዢው የጠየቀ እንደሆነ የመድኃኒት ማዘዣው ግልባጭ ይሰጠዋል ።

አንቀጽ ፴፬

ናርኮቲኮችን ስለማውጣት

፩/ ያለሐኪም ማዘዣ ማናቸውም ፋርማሲ ናርኮቲክነት ያለባቸውን የመድኃኒት ዝግጅትን ወጪ አያደርግም ።

www.chilot.me



፪/ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ግዳጆች ካልተፈጸሙ ማናቸውንም ዓይነት ናርኮቲክን የያዙ መድኃኒቶች የሚፈቅድ የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ለመቀበል አይቻልም ።

ሀ/ የመድኃኒት ማዘዣው እንደሚነበብ ሁኖ በግልጽ የተጻፈ መሆኑንና እንዲሁም የመድኃኒት ማዘዣዎችን ለመስጠት በሕግ ተፈቅዶለት በ፳፩ኛው አንቀጽ መሠረት በጊዜያዊ ዝርዝር ስሙ የተላለፈለት ሰው የፈረመበት ከመሆኑም በላይ ፣ ያዘዘው ሰው ስምና አድራሻ እንዶሚነበብ ሁኖ በመድኃኒት ማዘዣው ላይ የተጻፈበት እንዲሆን ያስፈልጋል ።

ለ/ የመድኃኒት ማዘዣው የታማሚውን ሰው ስም ፣ ዕድሜና አድራሻ የያዘ እንዲሆን ፣

ሐ/ የመድኃኒት ማዘዣው መድኃኒቱ የታዘዘበትን ቀንና ዓመት ምሕረት ፣ የመድኃኒቱን ጥንካሬና ዓይነት እንዲሁም ስለአደራረጉ በግልጽ የሚመራ እንዲሆን ።

፫/ ናርኮቲክ ያለበት የመድኃኒት ዝግጅት በሚጠየቅበት ጊዜ ራሱን የቻለ አዲስ የሐኪም ማዘዣ ወረቀት እንዲቀርብ ያስፈልጋል ።

፬/ ናርኮቲክ የተሸጠባቸው የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀቶች ሁሉ ቁጥርና ቀን እየተጻፈባቸው በልዩ ማኅደር እየሆኑ ከአምስት ዓመት ለማያንስ ጊዜ ይቀመጣሉ ። እንደዚህ ያሉት የመድኃኒት ማዘዣም ግልባጭ ሊሰጥ አይቻልም ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፷፬/፲፩ (፲፱፻፶፯) ሕ. ፫፻፭ አን. ፫ ተሻሻለ ።

## አንቀጽ ፴፭

## ስለናርኮቲክስ አገዛዝና አመዛጋገብ

፩/ ማናቸውም ፋርማሲ የዋናው መድኃኒት ቤት ኮርፖሬሽን ካልሆነ በስተቀር ከሌላ ቦታ ናርኮቲክስ እንዲወስድ አይፈቅድም ።

፪/ እያንዳንዱ ፋርማሲ በመደብር ያገባቸውን ናርኮቲኮች ሁሉ በማስታወሻ ይይዛል ። እንዲሁም የዋጋቸው መጠየቂያ ሠነዶቻቸውን በቅደም ተከተል አድርጐ በማኅደር ከአምስት ዓመት ለማያንስ ጊዜ ይጠብቃል ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፷፬/፲፩ (፲፱፻፶፯) ሕ. ፫፻፭ አን. ፫ ተሻሻለ ።

## አንቀጽ ፴፮

## የናርኮቲኮች አቀማመጥ

ማናቸውም ናርኮቲክ ቁልፉ በፋርማሲስቱ እጅ በሚገኝ የብረት ሣጥን ውስጥ ተቆልፎ መቀመጥ አለበት ።

## አንቀጽ ፴፯

## የናርኮቲኮች ዕቃ ዝርዝር

ፋርማሲስቶች ሁሉ በእጃቸው የሚገኙትን የናርኮቲኮች ሸቀጥ ሙሉ ዝርዝር ሚኒስትሩ በሚሰጣቸው ሠንጠረዥ ላይ በየጊዜው እየሞሉ በተወሰኑ ሰዓቶች ለሚኒስቴሩ ያቀርባሉ ።

www.chilot.me



### አንቀጽ ፴፰

### የንግድ ሥራን በሚያቋርጡበት ጊዜ ናርኮቲኮችን ስለማዘዋወር ።

የፋርማሲው ሥራ በሚቋረጥበት ጊዜ ስለናርኮቲክ የተያዙ መዛግብትና ማኅደሮች ፤ እንዲሁም ገና ያልተሸጡትን የናርኮቲክ ሽቀጦች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መምሪያ መሠረት ማስረከብ ያስፈልጋል ።

### አንቀጽ ፴፱

### መርዞችንና ሌላም አደገኛ የሆኑ መድኃኒቶች ስለማውጣትና ስለማስቀመጥ

፩/ ሚኒስትሩ በየጊዜው በሚያወጣው ደንብ መሠረት ካልሆነ በስተቀር ፤ ማናቸውም ፋርማሲ ሚኒስቴሩ በየጊዜው አዘጋጅቶ ለየፋርማሲዎች በሚያድለው ዝርዝር ውስጥ በስም ተለይተው የሚገኙትን መርዝነት ያላቸው ዝግጅቶች ወይም ሌላ አደገኛ ምጥኖች ወጪ ሊያደርግ አይችልም ።

፪/ ከዚህ በላይ በተመለከተው ፴፱ኛ አንቀጽ በቁጥር ፩ ከተጠቀሰው ዝርዝር ውስጥ በተለይ ስማቸው የሚጠሩ አንዳንድ መርዞች ወይም ሌላ ምጥኖች በተቆለፈ ሣጥን ውስጥ እንዲቀመጡ ያስፈልጋል ።

## ምዕራፍ ፭

### የድራግ ሱቆች አመራር

### አንቀጽ ፵

### እንዳይሸጡ የተከለከሉ

ከድራግ ሱቆች ዓይነተኛ የሥራ አመራር ጋር ተቃራኒ መስለው የሚታዩትን ማናቸውንም ዓይነት የተወሰኑ ወይም በየዓይነታቸው የተመደቡ ዕቃዎች በድራግ ሱቅ እንዳይሸጡ ሚኒስትሩ ለመከልከል ይችላል ።

### አንቀጽ ፵፩

### የሥራ አመራር

በድራግ ሱቅ ተቀጥሮ የሚሠራ ወይም የሚገኝ ማናቸውም ሰው ሐኪም በሚሰጠው የመድኃኒት ማዘዣ መሠረት የመድኃኒት ዝግጅት ደባልቆ ለመቀመም ፤ ወይም ማናቸውንም የመድኃኒት ዝግጅት ወይም መርዝ ለማሰናዳት ፤ ለመሥራት ፤ ወይም ጠቅልሎ ለማሸግ አይፈቀድለትም ። ሆኖም በመድኃኒት ማዘዣው ውስጥ የተጠየቁትን እሽጋቸው ያልተከፈተ መድኃኒቶችን ለመሸጥ የድራጉ ሱቅ ያለውን መብት ይህ ፵፩ኛው አንቀጽ ሊቀንስ አይችልም ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፷፱/፲፩ (፲፱፻፶፯) ሕ. ፫፻፩ አን. ፫ ተሻሻለ ።

www.chilot.me



## አንቀጽ ፺፪

## መቆጣጠር

የድራጉ ሱቅ ክፍት በሆነበት በማናቸውም ሰዓት ሥራው የሚካሄደው ከዚያው ሥፍራ በሚገኝ ድራጊስት ተመልካችነትና ሥራ መሪነት ነው ።

## አንቀጽ ፺፫

## የሥራ ሰዓቶች ፤ የመታወቂያ ምልክትና ተረኛን አመልካች

በዚሁ ደንብ በአንቀጽ ፹፮ እስከ ፹፱ ያለው በሙሉ ለድራግ ሱቅም ይሆናል ።

## አንቀጽ ፺፬

## ድርጅት

በድራግ ሱቅ ውስጥ ማናቸውም ሥፍራ ለመኖሪያ ወይም ለመኝታ እንዲያገለግል አይፈቀድም ።

## አንቀጽ ፺፭

## ናርኮቲኮች

ያለመድኃኒት ማዘዣ እንዲሸጡ ከተፈቀዱት ዝግጅቶች በስተቀር ማናቸውም ዓይነት ናርኮቲክ በድራግ ሱቅ ውስጥ መገኘት ፤ መቀመጥ መሸጥ አይችልም ።

### የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፱/፲፭ (፲፱፻፷፱) ሕ. ፪፻፳ አን. ፫ ተሻሻለ ።

## አንቀጽ ፺፮

## መርዞችና ሌላም አደገኛ የሆኑ መድኃኒቶች ስለማውጣትና ስለማስቀመጥ

ይህንን አንቀጽ (፺፮) ያሻሻለው የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር ፫፻፳፭/፺፯ ዓ.ም. አንቀጽ ፲፰ በአማርኛና በእንግሊዝኛው ጽሑፎች መካከል የሐሳብ ልዩነት ስላለ አስተውል ።

በአንቀጽ ፺፭ ከተሰጠው ውሳኔ በስተቀር ስለዚህ ጉዳይ በአንቀጽ ፹፬ የተመለከቱት ለድራግ ሱቅም ይውላሉ ። የመድኃኒት ማዘዣዎችም በዚሁ ደንብ በአንቀጽ ፹፫ በተመለከተው መሠረት ተይዘው ይቀመጣሉ ።

# ምዕራፍ ፲

# መድኃኒትን የሚቀምሙ መሥሪያ ቤቶች (ማኑፋክቸሪንግ ላቦራቶሪዎች) አመራር

## አንቀጽ ፺፯

## መቆጣጠር

መድኃኒቶችን የሚቀምም መሥሪያ ቤት (ማኑፋክቸሪንግ ላቦራቶሪ) መድኃኒት በሚሠራበት ወይም በሚጠቀልለበት ጊዜ ሥራው የሚካሄደው በአንቀጽ ፲፰ መሠረት የሥራ ፈቃድ

www.chilot.me



ባገኙ ሰዎች መሪነትና ተመልካችነት ሥር ነው ። መድኃኒቶች በሚሠሩበት ወይም በሚጠቀለሉበት ጊዜ ሁሉ ይህ ሰው በዚያው መገኘት አለበት ። ሆኖም እሱ በማይገኝበት ጊዜ ችሎታና የሥራ ፈቃድ ባለው ሰው ተመልካችነት ሥራው ሊመራ ይችላል ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፬/፲፩ (፲፱፻፶፯) ሕ. ፫፻፩ አን. ፫ ተሻሻለ ።

## አንቀጽ ፵፰

### ከዕፅዋትና ከእንስሳት የተቀመሙ (የባዮሎጂካል) ዝግጅቶች

ከእፀዋትና ከእንስሳት የተቀመሙ (የባዮሎጂካል) ዝግጅቶችን የሚሠሩ ማናቸውም ላቦራቶሪዎች ስለባዮሎጂካል ዝግጅቶች አሠራር ፣ አቀማመጥ ፣ አሰጣጥና አከፋፈል ሚኒስትሩ በሚያወጣቸው ልዩ ደንቦች ይመራሉ ።

## አንቀጽ ፵፱

### የተነጠሩ ዕቃዎች

በንጹሕ ተነጥረው የተቀመሙ የመድኃኒት ዝግጅቶች እየተሠሩ በትንንሽ ብልቃጦችና ጠርሙሶች ውስጥ የሚደፈኑት ለዚሁ ሥራ ተብሎ ለብቻው በተመደበ ክፍል ውስጥ ነው እንዲሁም በንጽሕና እንዲሠሩ የሚያስፈልጉት የሕክምና ዕቃዎች ማለት ለመቅደጃ ክፍል እንደሚያገለግሉት ዓይነት መጠቅለያዎች ተጋቢ ከሆኑ ነገሮች ነፃ እንዲሆኑ የሚሠሩትና የሚጠቀለሉት እንደዚሁ ንጽሕ በሆነ ክፍል ነው ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፬/፲፩ (፲፱፻፶፯) ሕ. ፫፻፩ አን. ፫ ተሻሻለ ።

## አንቀጽ ፶

### የናርኮቲኮች አሠራር

በአንቀጽ ፵፫—፵፰ ከተሰጠው ደንብ ጋር የሚስማማ ሁኖ ሲገኝ ፣ የተወሰነ ናርኮቲክ የያዙ የመድኃኒት ዓይነቶች እንዲሠሩ ሚኒስቴሩ ለአንድ ድርጅት ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል ።

የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፬/፲፩ (፲፱፻፶፯) ሕ. ፫፻፩ አን. ፫ ተሻሻለ ።

## አንቀጽ ፶፩

### ተሠርተው ስለወጡ አንዳንድ ዝግጅቶች አከላከል

አንዳንድ የመድኃኒት ዝግጅቶች የሚጐዱ ወይም ሊጐዱ የሚችሉ ሁነው ሲገኙ ፣ የፋርማሲና የላቦራቶሪ መምሪያ ክፍል በሚያቀርበው አሳብ መሠረት እንዳይሠሩ ፣ እንዳይሸጡ ወይም እንዳይሰጡ ሚኒስትሩ በየጊዜው ለመከልከል ይችላል ።

www.chilot.me



## ክፍል «መ» የመድኃኒት ምርመራና አከላከል

### አንቀጽ ፹፱

በማናቸውም አገር የተሠራውን የመድኃኒት ዝግጅት ለመመርመር ሚኒስቴሩ ሥልጣን አለው ፤ መድኃኒቱ በዕቃው ላይ ከተለጠፈው ጽሑፍ ጋር የማይመሳሰል ወይም በአንቀጽ ፶፪ መሠረት ሚኒስትሩ ከሚሰጠው ደረጃ በታች የሆነ እንደሆን ወይም መድኃኒቱ ነጋዴው ከሚሰጠው መግለጫ ጋር ያልተስማማ እንደሆን ፤ ወይም የተከለሰ እንደሆን ወይም የተሳሳተ ጽሑፍ ተለጥፎበት የተገኘ እንደሆነ ፤ መድኃኒቱ እንዳይሸጥና እንዳይከፋፈል ሚኒስቴሩ ሊከለክል ይችላል ።

## ክፍል «ሠ» በሙከራ ላይ ስላሉ አዲስ መድኃኒቶች

[በ፷፬/፲፩ (፲፱፻፶፯) ሕ. ፫፻፭ አን. ፫ ክፍል «መ» ፤ «ሠ» እና «ረ» ክፍል «ሐ» ፤ «መ» እና «ሠ» ተብለው ተሰይመዋል ። እንደዚሁም የክፍል «ሠ» አርእስት በሌሎች ቃላት ተተክቷል ።]

### አንቀጽ ፺፫

### ትርጉም

«አዲስ የመድኃኒት ዝግጅት» ማለት ይህ ደንብ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ከውጭ አገር ያልመጣ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ገና ያልተሠራ የመድኃኒት ዝግጅት ነው ።

#### የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፷፬/፲፩ (፲፱፻፶፯) ሕ. ፫፻፭ አን. ፫ ተሻሻለ ።

### አንቀጽ ፺፬

### እንዲሠራበት ስለመፍቀድ

የመድኃኒት ዝግጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ለገበያ ከመውጣታቸው ወይም ከመከፋፈላቸው በፊት ሚኒስትሩ ቦርዱ በሚያቀርብለት አሳብ መሠረት የመድኃኒት ዝግጅት አደጋ ሊያስከትል የማይችል መሆኑን አዋቂዎች እንዲመረምሩ ሥልጣን ይሰጣል ። እንደዚህ ያሉት የመድኃኒት ዝግጅቶች በአገልግሎት እንዲውሉ አዋቂው አሳብ በሚያቀርብበት ጊዜ በዚህ በ፰፻ኛው አንቀጽ የተመለከተው የሙያ ግዴታ መብቱን ሊቀንስበት አይችልም ።

#### የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፷፬/፲፩ (፲፱፻፶፯) ሕ. ፫፻፭ አን. ፫ ተሻሻለ ።

## ምዕራፍ ፯

## የሕክምና ዕቃዎች አቀማመጥ

### አንቀጽ ፺፭

### የተለዩ ምቹ ሥፍራዎች

በዚህ ደንብ መሠረት በማናቸውም ፋርማሲ ወይም ድራግ ስቶር የሚሸጡትን ማናቸውንም የመድኃኒት ዕቃዎች የተበላሹ ወይም ሊሸጡ የማይችሉ ሌላ ዕቃዎች ካሉበት መጋዘን ውስጥ አብሮ ለማስቀመጥ አይችልም ።

www.chilot.me



## አንቀጽ ፰፮

## የዕቃ ቤት ሁኔታ

የማናቸውም መድኃኒቶች አቀማመጥ ሁኔታ መጀመሪያ የሠራቸው መሥሪያ ቤት በሚያሳስበው መሠረት መሆን ይገባዋል ።

## አንቀጽ ፰፯

## የዕቃ ቤቶችን ስለመፈተሽ

ከዚህ በታች በአንቀጽ ፸ በተመለከተው መሠረት የሚሾመው ፈታሽ የመድኃኒትና ዕቃዎች የሚቀመጡባቸውን ማናቸውንም ሥፍራዎች በማናቸውም ጊዜ ፈትሾ የመድኃኒት ዕቃው አቀማመጥ ተለይቶ በተመደበለት ሁኔታ ያልተፈጸመ መሆኑን ሲረዳ ማለት በጊዜ ሁኔታ ፣ ከተባይ ወይም ያልተፈቀደለት ሰው እንዳይነካ በማድረግ በቂ መከላከያ ያልተደረገለት መሆኑን ከተረዳ ስለዚሁ ጉድለት ሐሳቡን ለሚኒስቴሩ ያቀርባል ። ሚኒስትሩም ሕግ በሚፈቅደው መሠረት እነዚህ ጉድለቶች ሊታገዱ የሚችሉበትን አስፈላጊ እርምጃ ያደርጋል ።

### የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፬/፲፩ (፲፱፻፶፯) ሕ. ፫፻፳ አን. ፫ ተሻሻለ ።

## ምዕራፍ ፱

## ልዩ ልዩ ነገር

## አንቀጽ ፰፰

## የሕክምና ዕቃ እንደገና ስለመጠቅለል

በዚህ ደንብ ውስጥ በተፈቀደው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ሰው ቢሆን ፋርማሲስት በሌለበት መድኃኒት የያዙ ዕቃዎች እንደገና በሌላ ዕቃ ለመጠቅለል በማሰብ ሊከፍት ወይም እንዲከፍቱ ለማድረግ አይችልም ። እንዲሁም እነዚህን የመሳሰሉ ዕቃዎች ፋርማሲስት በሌለበት በአዲስ ዕቃ አዛውሮ ማሸግ አይፈቀድም ።

## አንቀጽ ፰፱

## ለዓይነት የቀረቡ የሕክምና ዕቃዎች

ለዓይነት በነፃ እንዲታደሉ ከጉምሩክ ቀረጥ ወይም ግብር በነፃ ከውጭ አገር የሚገቡ የሕክምና ዕቃዎች ላይ በእንግሊዝኛና በአማርኛ «የማይሸጥ» የሚል አጭር መግለጫ ሊጻፍባቸው ይገባል ። እንደዚህ ያለ ጽሑፍ የሌለባቸውን ማናቸውንም ዓይነት ዕቃዎች ማንም ሰው ቢሆን ለሌላ ሰው ለመስጠት ወይም ለማስተላለፍ አይፈቀድለትም ።

## አንቀጽ ፺

## ስለመቆጣጠር

ይህን ደንብ ለማስከበር እንዲቻል ፋርማሲዮችን ፣ የድራግ ሱቆችን ፣ የመድኃኒት መቀመምያ መሥሪያ ቤት እንደዚሁም በጠቅላላ ሌሎችን የሕክምና ዕቃ የሚሸጡ ወይም የሚያከፋፍሉ ድርጅቶች ለመቆጣጠር ችሎታ ያላቸው ሰዎች ሚኒስትሩ ይሾማል ። የመቆጣጠሩ ተግ

www.chilot.me



<u>የተጠቃለሉ ሕጎች ማሰረጃ</u>

በ፷፬/፲፩ (፲፱፻፶፯) ሕ. ፫፻፭ አን. ፫ ይህ ቁጥር ተሰጠው ።

<u>የተጠቀሱ ሕጎች</u>

ስለሐኪሞች መመዝገብ የወጣ አዋጅ ፣ ፳/፩ (፲፱፻፵፩) አ. ፯ አን. ፲፫ ። እዚህ የተጠቀሱት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጾች በመጀመሪያ የወ.መ.ሕ. ፲፯/በተ. ዩ. ፩ (፲፱፻፵፱) አን. ፬፻፹፰ ፣ ፭፻፹ ፣ ፭፻፲፬ ፣ ፯፻፴፰ ፣ ፯፻፹፩—፯፻፹፯ እንደሆኑ ይገመታል ።

አንቀጽ ፳፮

ከዚህ በፊት በተሰጠ የሥራ ፈቃዶች ላይ

<u>የዚህ ደንብ አፈጻጸም</u>

ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት በዋናው አዋጅ መሠረት የተሰጠ ማናቸውም የሥራ ፈቃድ ወይም ልዩ ፈቃድ በሙሉ የጸና ሁኖ በዚህ ደንብ ይተዳደራል ።

<u>የተጠቃለሉ ሕጎች ማሰረጃ</u>

በ፷፬/፲፩ (፲፱፻፶፯) ሕ. ፫፻፭ አን. ፫ ይህ ቁጥር ተሰጠው ።

አንቀጽ ፳፯

<u>ደንቡ ስለሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ <u>በነጋሪት ጋዜጣ</u> ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል ፤ ሆኖም እስከ አሁን በሥራ ላይ ሁነው በዚህ ደንብ መሠረት ለመጀመሪያ ጊዜ የሥራ ፈቃድ ወይም ልዩ ፈቃድ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ይህ ደንብ ከወጣበት ጊዜ አንሥቶ የሥራ ፈቃድ ወይም ልዩ ፈቃድ ለማግኘት የዘጠና (፺) ቀኖች ጊዜ ይሰጣቸዋል ።

<u>የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ</u>

በ፷፬/፲፩ (፲፱፻፶፯) ሕ. ፫፻፭ አን. ፫ ይህ ቁጥር ተሰጠው ።

አዲስ አበባ ሰኔ ፲ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ.ም.

www.chilot.me



## ፲፰/፯ (፲፱፻፶፩) ት. ፳፪*

## ወባ ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት ውስጥ እንዲጠፋ ለማድረግ የወጣ ትእዛዝ

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እኛ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

ወባ በንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችን ውስጥ በብዙ ክፍል ሀገሮች አይሎ የሚገኝ በሽታ መሆኑንና በዚህም በሽታ ምክንያት ብዙው ሕዝባችን በጤንነቱ ረገድ ከባድ ጉዳት የሚደርስበት መሆኑን አይተን ፤

ስለዚህ በሽታ በሳይንስ ረገድ የተደረገው ምርመራና ጥናት ባስገኘው ውጤት መሠረት ሙሉና በቂ በሆኑ ዘመናዊ መሣሪያዎች እንዲሁም በሠለጠኑ ሠራተኞች ከተከላከልነው ወባን በጭራሽ ለማጥፋት የሚቻል መሆኑ ስለታወቀ ፤

እንዲሁም ወባን ማጥፋት ለአገር እጅግ ጠቃሚ መሆኑን ተመልክተን ፤ በተሻሻለው ሕገ መንግሥታችን በ፳፯ኛው አንቀጽ የተጻፈውንና የሚኒስትሮች ምክር ቤት የመከረበትን መሠረት አድርገን ቀጥሎ ያለውን ትእዛዝ ሰጥተናል ፡—

፩/ ይህ ትእዛዝ «ወባን ከንጉሠ ነገሥት ግዛታችን ስለማጥፋት የወጣ የ፲፱፻፶፩ ዓ.ም. ትእዛዝ» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ፤

፪/ በሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስትራችን ሥር የሚተዳደርና የሚመራ የወባ ማጥፊያ ድርጅት ተብሎ የሚጠራ አንድ መሥሪያ ቤት በዚህ ትእዛዝ ተቋቋሟል ። ይህም ድርጅት ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ይቋቋማል ፤

ሀ/ ከሚኒስትሩ በታች ሆኖ ሚኒስትሩ በዚህ ትእዛዝ መሠረት የሚያወጣቸውን ደንቦች ፤ ውሳኔዎችና ትእዛዞችን የሚያስከብርና የሚያስፈጽም አንድ ዋና ዲሬክተር በኛ ፈቃድ ይሾማል ፤

ለ/ ሚኒስትሩን ስለድርጅቱ አመራርና አስተዳደር በምክር የሚረዱት በኛ ፈቃድ የሚሾሙ ከአምስት አባሎች የማያንሱ ያሉበት አንድ የአማካሪዎች ቦርድ ይቋቋማል ለዚህም ቦርድ ወባን ለማጥፋት ከሚረዱን የኢንተርናሲዮናል ድርጅቶች አንዳንድ ወኪል የሆኑ ሰዎች አባል ይሆናሉ ፤

ሐ/ በዋናው ዲሬክተር መሪነትና በሚኒስትሩ ተቆጣጣሪነት ስለሥራው የሚወጣውን ደንብና ውሳኔ በሚገባ ለማከናወን ይቻል ዘንድ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይቀጠራሉ ። የነዚህም ሠራተኞች አቀጣጠር በውል ለተወሰነ ጊዜ ተቀጥረው የሚሠሩ ይሆናሉ ።

፫/ የወባ ማጥፊያ ድርጅት ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ተግባሮች ይፈጽማል ፡—

ሀ/ ወባን ከንጉሠ ነገሥት ግዛታችን ባጭር ጊዜ ውስጥ ለማጥፋት የሚያስችል ዓላማ ያለውን የወባ ማጥፊያ ፕሮግራም ያዘጋጃል ፤

* የመግቢያ የግርጌ ማስረጃ

፳፩/፫ (፲፱፻፶፱) ት. ፳፫ በግ. ሳ. ተሻሻለ ።

www.chilot.me



ለ/ ፕሮግራሙን ለማስፈጸሚያ አስፈላጊውን የወጪ በጀት በየመቱ ያዘጋጃል የበጀቱም መጠን በማናቸውም ረገድ የፕሮግራሙ አፈጻጸም እንዳይቋረጥና እንቅፋት እንዳያገኘው መሆን አለበት ፤

ሐ/ ፕሮግራሙን በሚገባ አኳኋን ለማስፈጸም በቂ የሠለጠኑ ሠራተኞች ለማግኘት የሚያስፈልገውን እርምጃ ሁሉ መውሰድ አለበት ፤

መ/ በወባ በሽታ በተመረዙት ክፍለ አገሮች የሚኖረው ሕዝባችን ፕሮግራሙን እታሰበው ግብ ለማድረስ እንዲተባበር አስፈላጊውን ምክር ይሰጣል ።

፬/ የጤና ጥበቃ ሚኒስትራችን ፡—

ሀ/ ለድርጅቱ አስፈላጊ የሆኑትን ሠራተኞች ለመቅጠርና ለማሰናበት ፣ እንዲሁም የደመወዛቸውን ልክና የሚቀጠሩበትን ሁኔታ ለመወሰን ይችላል ፤

ለ/ ፕሮግራሙን እግብ ለማድረስ ከማናቸውም ምንጭ ፣ ከውጭ አገር መንግሥታትም ሆነ ከኢንተርናሲዮናል ድርጅቶች በጥሬ ገንዘብ ወይም በሸቀጥ ወይም በሞያተኛ አገልግሎት የሚገኘውን እርዳታ ሁሉ ለመቀበልና ለዚሁም አስፈላጊውን ውልና ስምምነት ተነጋግሮ ለመዋዋል እንዲፈቀድለት ለማቅረብ ይችላል ፤

ሐ/ ለወባ ማጥፊያ ድርጅት አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎችና መሣሪያዎች መግዣ ለደመወዝና ለሥራ ማስኬጃ ከተፈቀደለት በጀት አስፈላጊውን ወጪ እያዘዘ ለማስከፈል ይችላል ፤

መ/ የዚህን ትእዛዝ ዓላማ ከግቡ ለማድረስ በዚህ ትእዛዝ የተሰጠውን ወይም የወባ ማጥፊያ ድርጅት ወይም መንግሥቱ ባደረጋቸው ስምምነቶች የተሰጠውን ሥልጣን በሙሉ ወይም በከፊል በውክልና ለማስተላለፍ ይችላል ።

## የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፹፭/፫ (፲፱፻፸፱) ት. ፳፫ እን. ፱ ፣ ፳፯ ፣ ፩ የተጠቃለለ የኢት. ሕጎች ፪—፱ ፣ ፳፯ ፣ (የሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በወባ ማጥፊያ ድርጅት ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞችን ለመቅጠርና ለማሰናበት የነበረው ሥልጣን የመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ጠቅላይ መሥሪያ ቤት ከተቋቋመ ወዲህ በግልጽ ሳይነገር ተሻሽሏል ። በትእዛዝ ቍጥር ፳፫ መሠረት የመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ጠቅላይ መሥሪያ ቤት ተስማምቶ ሳያጸድቀው በረዳት ሚኒስትር ደረጃ ወይም ከዚያ በታች ባለ ደረጃ ሹመት አይሰጥም ፣ አይቀጠርም ፤ የደረጃ እድገትም አይደረግም ። አንድ የመንግሥት ሠራተኛ የሥራ ችሎታው ደካማ ሆኖ ከተገኘ ደንበኛ በሆነ ሥርዓት መሠረት እንዲሰናበት ለማድረግ ይቻላል ።)

፭/ ወባን ከንጉሠ ነገሥት ግዛታችን ለማጥፋት የወባ ማጥፊያ ድርጅት ባልደረባ የሆኑ ሠራተኞች ከጤና ጥበቃ ሚኒስትራችን ወይም በርሱ ከተወከለ ባለሥልጣን ተገቢ የሆኑ ፈቃድ ሲሰጣቸው ፤ በንጉሠ ነገሥት ግዛታችን ውስጥ በማናቸውም ሥፍራ ቅጥር ግቢም ቢሆን ሳይከለከሉ ለመግባት ይችላሉ ።

፮/ በንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችን ውስጥ ነዋሪ የሆነ ማንኛውም ሰው ፈቃድ የተሰጣቸው የወባ ማጥፊያ ድርጅት ባልደረቦች ወባን ለመከላከል ለምርመራ ደም ለመቅዳትና ሕክምናም ለማድረግ ሲመጡ ፈቅዶ መቀበል አለበት ።

፯/ በንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችን ውስጥ ነዋሪ የሆነ ማንኛውም ሰው ወባ የያዘው ሰው መኖሩን ባወቀ ወይም በጠረጠረ ጊዜ ለወባ ማጥፊያ ድርጅት መሥሪያ ቤት ወይም ለፖሊስ ማስታወቅ አለበት ።

፰/ የጤና ጥበቃ ሚኒስትራችን በአማካሪው ቦርድ አሳሳቢነት እንዲሁም በወባ ማጥፊያ ድርጅት ባልደረቦች አማካይነት ወባን ለማጥፋት አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች ሁሉ

www.chilot.me



## የተጠቀሰው ሕግ

የሕዝብ ጤና ጥበቃ አዋጅ ፤ ፳/፲፱ (፲፱፻፴፱) አ. ፳፩ አን. ፱ እና ፲ ፤ ፴ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፫—፱ ፤ ፲ ።

፳/ በዚህ ትእዛዝ መሠረት የጤና አጠባበቅ ድርጅቶች የሚቋቋሙበትንና የሚካሄዱበትን መንገድና እንደዚሁም በጠቅላላው ይህ ትእዛዝ በተሻለ አኳኋን እንዲፈጸም ለማድረግ የሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስትራችን ደንቦችን ለማውጣት ይችላል ።

፳፩/ ይህ ትዕዛዝ በነጋሪት ጋዜጣ ከታተመበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፩ ቀን ፲፱፻፵፪ ዓ.ም.

www.chilot.me



፫ኛ አንቀጽ ።

**ለቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ስለተሰጣት ጉልት።**

በማናቸውም ምክንያት ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠና ከቤተ ክህነት የገባ መሬት በሁለተኛ አንቀጽ እንደተጻፈው ፤ ግብሩ ለቤተ ክርስቲያን ግምጃ ቤት ይገባል እንጂ ከቤተ ክርስቲያን አይወጣም ። ይህም ገንዘብ ለቤተ ክርስቲያን መስፋፋትና ለተማሪ ቤት ፤ ለበጐ ሥራ ነገር ሁሉ እንዲገባ ይደረጋል ።

፬ኛ አንቀጽ ።

**ስለገበዞች ጉልት ገቢ ገንዘብ ።**

ባለ ጉልት ገበዞች በዓመት ፩ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ የዋዜማውን ዝክር መዘከራቸውና ለጧፍ ፤ ለዕጣን ፤ ለመገበሪያና ይህን ለመሰለው የቤተ ክርስቲያን መባዕ ሁሉ ማስባቸው ቀርቶ፤ ጉልታቸው በእጃቸው ሆኖ መንግሥት ለባለ ጉልት በቆረጠው ግብር ልክ ለቤተ ክርስቲያን ይገብራሉ ። እንዲሁም የዝክር መዘከሪያ ጉልትና መልከኝነት ያላቸው ሰዎች ፤ ድግስ መደገሳቸው ቀርቶ መንግሥት ለባለ ጉልት በቆረጠው ግብር ልክ ለቤተ ክርስቲያን ይከፍላሉ ።

፭ኛ አንቀጽ ።

**ስለገበዞች ።**

ይህ ደንብ ከቆመበት ቀን ጀምሮ ወደፊት ባለ ጉልት ገበዞች በ፫ኛው አንቀጽ እንደተ ጻፈው መንግሥት ለባለ ጉልት በቆረጠው ልክ ለቤተ ክርስቲያን እየከፈሉ ጉልታቸውን ብቻ ይዘው ይቀመጣሉ እንጂ በታቦቱ የስእለት ገንዘብና በሙታን መገበሪያ ማስተንተንና ማዘዝ ፤ በዕቃ ቤቱም ቁልፍ አላፊ መሆን የለባቸውም ። በሹመትም ምክንያት ቤተ ክህነትን እንዳያ ዝዙ ይወሰናል ። ስለግብዝናውም ሹመት የደብሩ አለቃ ማኅበሩን አስመርጦ ፤ ከካህናቱ ውስጥ ሥልጣን ያለውን ካህን መርጦ ሊሾም ይፈቀድለታል ።

፮ኛ አንቀጽ ።

**ስለካህናት አስተዳደር ።**

ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ ካህናት መልካም ጠባይና ሙያ ያላቸው ተመርጠው ለያ ንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን እንደሚበቃው በልኩ ፤ በቁጥሩ ተወስነው በሚችሉት ሥራ ተተክለው በቀለብ ያድራሉ ። ከዚህ የሚከተለውንም ሕግ እንዲፈጽሙ ያስፈልጋል ።

ሀ/ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል የሚተከሉ ካህናት በዚያው ባሉበት ደብር ብቻ ያገለግላሉ ።

ለ/ ማናቸውንም ዓይነት የውጭ ሥራ ለመያዝ አይፈቀድላቸውም ።

ሐ/ በቤተ ክህነት ሹማምንት ፈቃድ ለሥራ በመዛወር ካልሆነ በተቀር በ፩ና በ፪ ደብር መተከል አይችሉም ።

፯ኛ አንቀጽ ።

**ስለቀለብ ውሣኔ ።**

እንዶሥራው ማዕርግ ይወሰናል ። አንደኛ ለሹማምንትና ለመምህራን ፤ ሁለተኛ ለካህናትና ለሠራተኞች እንደስፍራው አኳኋን ይወሰናል ። ለከተማና ለበረሃ ኑሮ ፤ ለባላገርና ለነፋሻ ስፍራ።

www.chilot.me



፫/፲፪ (፲፱፻፴፮) ድ. ፫

## ስለሚሲዮናች አቋቋም የወጣ ድንጋጌ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እኛ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

ሚሲዮኖች እንደሚቻል መጠን ከመንግሥት ጋራ ተባብረው እንዲሠሩ ለማድረግ ስለሚሲዮኖች አስተዳደር የታሰበውን በግልጽ ለይቶ ማስታወቅ አስፈላጊ ስለሆነ ፤

ሚሲዮኖች ሥራቸውን ከሕዝቡ መካከል የክርስቲያን ሃይማኖት በሌላቸው ሕዝቦች መካከል እንዲያስተምሩ እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀድሞ የክርስቲያን ሃይማኖት ሲጀመር ጀምሮ የያዘውን የክርስቲያን ሃይማኖት የሚለውጥ ትምህርት እንዳያስተምሩ ማገድ የመንግሥት አሳብ ስለሆነ ፤ ልዩ ልዩ እምነት ያላቸው ሚሲዮኖች ባንድ ወረዳ ውስጥ ያለመጠን እንዳይበዙና ከሚሲዮናውያን ሥራ መካከል መልካም ዕውቀት የሚያስገኝ የሆነው እንዲስፋፋ ለማድረግ የሚፈቀድ ስለሆነ በንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችን ውስጥ ስላሉት ሚሲዮናውያን ሥራዎች ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ደንግገናል ።

፩/ ይህ ድንጋጌ ካሁን በፊት በኢትዮጵያ ውስጥ ለተቋቋሙትና ወደፊትም ለሚቋቋሙት የውጭ አገር ሚሲዮኖች ሁሉ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ወደፊት የጸና ይሆናል ።

፪/ የትምህርትና የሥነ ጥበብ ሚኒስትር ያገር ግዛት ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ወይም እነርሱ የመረጧቸው ወኪሎች ያሉበት በትምህርትና በሥነ ጥበብ ሚኒስትር ፕሬዚዳንትነት ስለሚሲዮኖች አንድ ኮሚቴ እንዲቆም ተደርጓል ። የትምህርትና የሥነ ጥበብ ሚኒስትርም ይህን ድንጋጌ ሲያስፈጽም ከዚህ በላይ የተባለው ኮሚቴ በሚያቀርብለት አሳብ ይመራል ።

፫/ በኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ ሚሲዮን ለማቋቋም ፈቃድ ለማግኘት በሚሲዮናዊ ማኅበር ስም የሚደረገው ማናቸውም ጥያቄ ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሲላክ ይገባል ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም የቀረበለትን ጥያቄ ነገሩን እንዲቆርጥ ወደ ትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ያስተላልፋል ።

፬/ ሀ/ የትምህርትና የሥነ ጥበብ ሚኒስትር ማናቸውንም ይህን የመሳሰለውን ጥያቄ ከመረመረ በኋላ እንደመሰለው አይቶ ሊፈቅድ ወይም ሊከለክል ይችላል ። የትምህርትና የሥነ ጥበብ ሚኒስትር የቀረበለትን ጥያቄ ሲቀበል ጥያቄውን ያቀረበው የሚሲዮን ማኅበር ሥራውን ወስኖ የሚሠራባቸውን ወረዳዎች ወይም አውራጃዎች ለይቶ ይወስናል ።

ለ/ ጥያቄውን ለመቀበልም ቢሆን ፤ ወይም ለመከልከል ጥያቄ ያቀረበው ሚሲዮናዊ ማኅበር የታወቀ ፤ ወይም ከዚህ በፊት የተቋቋመ መሆኑንና አለመሆኑን የትምህርትና የሥነ ጥበብ ሚኒስቴር መመርመር አለበት ።

ሐ/ ስለነዚህ ደንቦች ሐሳብ የታወቀ ሚሲዮናዊ ማኅበር የሚባለው በልዩ ልዩ የዓለም ክፍሎች ውስጥ የሥራ ዕውቀትና መልካም ስም ያገኘ በቂ ገንዘብና ሠራተኞችም ያለው ማኅበር ነው ።

መ/ የተቋቋመ ሚሲዮናዊ ማኅበር ማለት ከ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. በፊት በኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ ፤ ወይም ከ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. ከሰኔ ወር ወዲህ የተቋቋመ ነው ። ስለሆነም ከ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. በፊት በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሠራ የተፈቀደለት ሚሲዮናዊ ማኅበርም ቢሆን ከመስከረም ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ሰኔ ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. ድረስ ቦታና ቤት ያገኘ ፤ አስቀድሞ እንደተቋቋመ ሚሲዮን ሆኖ አይቆጠርም ።

www.chilot.me



፬/ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሁን ቀደም የተቋቋመው ማናቸውም ሚሲዮናዊ ማኅበር ይህ ያሁኑ ድንጋጌ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ሠላሳ (፴) ቀን ድረስ የሚሲዮኖቹን ሁኔታ ፤ የሚሲዮናውያኑንም ስም ቁጥራቸውን ፣ ዕድሜያቸውንና ዜግነታቸውን ሚሲዮናቻቸው የሚሠሩባቸውን ወረዳዎች ወይም አውራጃዎች የሥራቸውንም ዓይነት ዘርዝር ለምትሀርትና ለሥነ ጥበብ ሚኒስትር ማቅረብ አለበት ።

፭/ ሚሲዮኖች ሥራቸውን የሚሠሩባቸውንና እንዳይሠሩ የሚከለከሉባቸውን ወረዳዎች ፣ ወይም አውራጃዎች ፣ የሚወስኑትን ደቦች ስለሚሲዮኖች የቆመው ኮሚቴ ያወጣዋል ። እነዚህም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ የሆኑ ወረዳዎችና ግልጽ ወረዳዎች ይባላሉ ።

፮/ ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ደንቦች ለማቋቋም ኮሚቴው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ነገሮች ይመራል ።

ሀ/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ የሆኑ ወረዳዎች የተባሉት ከሕዝቡ የሚበልጠው ወገን የኦርቶዶክሳዊትን ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት የሚከተል የሚገኝባቸው ወረዳዎች ናቸው ፤

ለ/ ግልጽ ወረዳዎች የተባሉት ደግሞ በኢትዮጵያ ከሚገኙት ያገር ክፍሎች ከሕዝቡ የሚበልጠው ወገን ክርስቲያን ያልሆነ ወረዳዎች ናቸው ፤

ሐ/ የሕዝቡ አኳኋን ባስፈለገበት ቦታ ኮሚቴው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ የሆኑት ወረዳዎች በግልጽ ወረዳዎች ውስጥ ግልጽ ወረዳዎችም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወረዳዎች ውስጥ እንዲገቡ ሊያደርግ ይችላል ።

፯/ ሚሲዮኖች የሕክምና ቤቶችና በሃይማኖት የወገን ልዩነት የሌላቸው ትምህርት ቤቶች እንዲያቆሙ ይፈቀድላቸዋል እንጂ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ በሆኑ ወረዳዎች ውስጥ ሃይማኖት የሚለውጥ ሚሲዮን ሊያቆሙ አይችሉም ።

፰/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ በሆኑ ወረዳዎች በሚገኝ የሚሲዮን ወይም የሕክምና ትምህርት ቤት የሚሰጠው የሃይማኖት ትምህርት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በአንድነት ባለመለያየት በተቀበሉት ክርስቲያን ሃይማኖት መሠረት ብቻ ይወሰና ል ። የትምህርትና የሥነ ጥበብ ሚኒስትር አስፈላጊ መስሎ ቢታየው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት መሠረት የክርስትና ሃይማኖት ዕውቀት ያላቸው መምህራን አስገብተው እርሱ በወሰነው ጊዜና ሰዓት እንዲያስተምሩ ይህን የመሰሉትን የሕክምና ቤቶችና የትምህርት ቤቶች ለመጠየቅ ይችላል ።

፱/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ በሆኑ ወረዳዎች ውስጥ የሚሲዮንን ሃይማኖት የተቀበሉ የተገኙ እንደሆነ ፤ ሚሲዮናውያን በእንደዚህ ያሉት ወረዳዎች ውስጥ ገብተው ራሳቸው የሚያምኑበትን ሃይማኖት ፣ ሃይማኖቱን ለተቀበሏቸው ሰዎች ሊሰብኩና ሊያስተምሩ ይችላሉ ። ግን ሃይማኖትን ለማስለወጥ ማስተማር አይችሉም ።

፲/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ባልሆኑት ወረዳዎች ውስጥ ወሰን ሳይደረግባቸው የክርስቲያንን ሃይማኖት ሚሲዮኖቹ ራሳቸው በሚያምኑበት መንገድ ሊያስተምሩና ሊሰብኩ ይችላሉ ።

፲፩/ አዲስ አበባ ግልጽ ወረዳ በመሆኑ በዚህ ወረዳ ውስጥ ሚሲዮናውያን ማኅበሮች የራሳቸቸውን ሃይማኖት የሚያስተምሩባቸው ትምህርት ቤቶች ሊከፍቱ ይችላሉ ።

፲፪/ በሙሉ ኢትዮጵያ የማስተማሪያ ቋንቋ አማርኛ ስለሆነ ይህን ቋንቋ ሚሲዮናውያን ሁሉ እንዲማሩት ይጠየቃሉ ።

፲፫/ በግልጽ ወረዳዎች ውስጥ ተማሪዎቹና ሚሲዮናውያኑ በአማርኛ መሥራት እስኪችሉ ድረስ በመጀመሪያ ጊዜ ሚሲዮናውያን በሀገሩ ቋንቋ ለመናገር ይችላሉ ።

www.chilot.me



፯/ የቤተ ክርስቲያኗን የገቢና ወጭ ገንዘብ ለመቆጣጠርና ግምጃ ቤቷን ለማስተያዳደር፤

፰/ በዚህ ትእዛዝ የተሰጠውን ሥልጣን በሙሉ ወይም በከፊል ከጊዜ ወደጊዜ ወይም በማናቸውም ጊዜ ለሚመረጠው ሰው ወይም ሰዎች ለመስጠት፤

፱/ በዚህ ትእዛዝ በዝርዝር በተሰጠው ወይም በሕግ በተፈቀደለት ሌላ ሥልጣን መሠረት ሥራውን በሚያካሂድበት ጊዜ አስፈላጊው ወይም ግዴታው ሆኖ ያገኘውን ማናቸውንም ሕጋዊ አድራጎት ለመፈጸም ።

፬/ ደንብ ስለማውጣት ፤

የቤተ ክህነት ጉባዔ በዚህ ትእዛዝ ስለተመለከተው የቤተ ክርስቲያን ሥጋዊ አስተዳደር ደንብ ለማውጣት ይችላል ።

፭/ ስለሚጸናበት ጊዜ ፤

ይህ ትእዛዝ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ.ም.

፳፫/፲፩ (፲፱፻፷፩) ሕ. ፫፻፷፱

ስለቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በ፲፱፻፶፱ ዓ.ም. በወጣው
ትእዛዝ መሠረት የወጣ ደንብ ።

፩/ ይህ ደንብ ስለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በቁጥር ፵፰/፲፱፻፶፱ ዓ.ም. በወጣው ትእዛዝ በአንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ ፪ በአንቀጽ ፫ በንዑስ አንቀጽ ፯ እና በአንቀጽ ፬ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የቤተ ክህነት ጉባዔ ያወጣው ደንብ ነው ።

፪/ ይህ ደንብ «የ፲፱፻፷፩ ዓ.ም. የዋናው ሥራ አስኪያጅ ሥልጣን ኃላፊነትና ተግባር ደንብ» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

፫/ በቤተ ክህነት ጉባዔ በፓትሪያርኩ መሪነትና ቁጥጥር ሥር ሆኖ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ዋና ኃላፊ የሚሆን አንድ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ይኖራል ።

፬/ ከዚህ በላይ በተመለከተው ጠቅላላ ሥልጣን ሳይወሰን ዋናው ሥራ አስኪያጅ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ተግባሮች ይፈጽማል ።

፩/ የጠቅላይ ጽ/ቤቱን የልዩ ልዩ ክፍሎችንና ዘርፎች መሥሪያ ቤቶችን አስተዳደር ይመራል ።

፪/ ከቤተ ክህነት ጉባዔ የሚወሰኑት ውሳኔዎችና መምሪያዎች ፍጻሚ እንዲያገኙ ያደርጋል ።

፫/ የቤተ ክርስቲያንን ገቢ ይሰበስባል መሰብሰቡንም ያረጋግጣል ።

፬/ የቤተ ክህነትን ጉባዔ እያስፈቀደ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ ወይም ለመለወጥ፤

www.chilot.me



፭/ ከ፩፻ሺህ የኢትዮጵያ ብር የማይበልጥ ገንዘብ ለመበደርና ዋጋው ከዚህ ገንዘብ የማይበልጠውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለማስያዝ ፤

፮/ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ከአምስት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ ለመከራየት ወይም ለማከራየት ፤

፯/ የቤተ ክርስቲያንን ጥንታውያን ንብረቶችን መሸጥ መለወጥ ወይም ማስያዝ ካል ሆነ በቀር ማንኛውንም ውል ለመዋዋል ይችላል ።

፰/ ከቤተ ክርስቲያን አቋም ጋር የሚስማሙ ሥራዎችን በማካሄድና ለቤተ ክርስቲያን ትምህርት የስብከትና የአገልግሎት ዓላማ የገንዘብ ምንጭ ለማስገኘት የቤተ ክርስ ቲያን ንብረት የሚለማበትንና ጥቅም የሚያስገኝበትን ዘዴ እያጠና በሥራ ላይ ያውላል ።

፱/ የዕለት ሥራ አመራርን ስለሚመለከቱ ጉዳዮች በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ስም አስፈላጊውን ይፈጽማል ።

፲/ ስለቤተ ክህነት የአስተዳደር ሠራተኞች በሚወጣው የሠራተኞች ማስተዳደሪያ ደንብ መሠረት ይሠራል ።

፲፩/ የቤተ ክርስቲያን የሂሣብና የንብረት መዛግብትና ማኅደረ ጉዳዮች በሚገባ እንዲጠ በቁ ያደርጋል ።

፲፪/ የቤተ ክርስቲያንን መሥሪያ ቤቶች የሥራ አመራርና የገንዘብ አስተዳደር ይቆጣ ጠራል ።

፲፫/ በየዓመቱ ከጥቅምት ወር መጨረሻ በፊት ባለፈው ዓመት ውስጥ በእርሱና በቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽ/ቤት የተፈጸሙትን ሥራዎች በዝርዝር የሚያስረዳ ዓመታዊ መግለጫ (ራፖር) ለቤተ ክህነት ጉባዔ ያቀርባል ።

፲፬/ የቤተ ክህነትን ጠቅላላ የዓመት በጀት አዘጋጅቶ በየዓመቱ ከሐምሌ ፴ ቀን በፊት ለቤተ ክህነት ጉባዔ አቅርቦ ያስፈቅዳል ።

፲፭/ በተፈቀደው በጀት መሠረት ማንኛውም ወጪ የሚደረገው በዋናው ሥራ አስኪያጅ እርሱም በሌለ ጊዜ እርሱ በደንቡ መሠረት በሚወክለው ባለሥልጣን ፊርማ መሆ ኑን ያረጋግጣል ።

፲፮/ ለቤተ ክህነት መልካም አመራርና ለቤተ ክርስቲያን ዓላማዎች ተግባሮችና አገልግ ሎቶች ዕድገትና ፍጻሜ ማግኘት አስፈላጊ የሆኑትን ሐሳቦች እያጠናና እያስጠና በየጊዜው ለቤተ ክህነት ጉባዔ ሐሳብ ያቀርባል ።

፲፯/ ስለቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽ/ቤትና ዘርፎች መሥሪያ ቤቶች አቋም ዝርዝር ተግባርና ግንኙነት አጥንቶ የውስጥ ደንብ እንደዚሁም የቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር ክፍል ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ደንብ አጥንቶ ለቤተ ክህነት ጉባዔ አቅርቦ ያስፈቅዳል ።

፲፰/ በማንኛውም የክስ ጉዳይ ስለቤተ ክህነት በመወከል ይቀርባል ወይም ሌላ ወኪል ያደርጋል ።

፲፱/ ከዚህም ሌላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የሚወስንለትን ተግባር ሁሉ ይፈጽማል ።

፮/ ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ መጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ. ም.

www.chilot.me



## ክፍል ፴፪

# የመተዳደሪያ ደንብ ያላቸው ልዩ ልዩ የግል ድርጅቶች ።

፯/፰ (፲፱፻፴፱) መ. ፯

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እኛ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

በንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችን ውስጥ የንግድ ሥራ እንዲስፋፋና ነጋዴዎችንም ለመርዳት አስበን ፤

የአዲስ አበባ የነጋዴዎች ምክር ቤት መተዳደሪያ ደንብ በንጉሠ ነገሥቱ እንዲጸድቅ የሚገባ መሆኑን ተመልክተን ፤ በልዩ ችሮታችንና በሙሉ ፈቃዳችን የአዲስ አበባ ነጋዴዎች ምክር ቤት አንድ አካል ፥ አንድ መንፈስ ሆኖ የዲሬክተሮቹ ጉባዔ እየተስማማበት በሚለው ጠው እንድ ማኅበራዊ ማኅተም ፤ ዛሬና በሚመጣውም ዘመን እየተወራረሰ እንዲሠራ ፤ ከዚህም በላይ በዚህ በንጉሠ ነገሥቱ በተሰጠው መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የተጻፈውን በመከተል በተፈቀደለት ሥልጣን መሠረት ሥራውን እንዲያካሄድ ፈቅደን አዘናል ።

፩/ በዚህ መሠረት የቆመው ማኅበር "የአዲስ አበባ የነጋዴዎች ምክር ቤት" ተብሎ ይጠቀሳል ። ከዚህም በታች «የምክር ቤቱ» እየተባለ ይጠራል ።

፪/ በነጋዴዎች ምክር ቤት አባል ለመሆን የሚችሉ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትራችን መዝገብ የገቡ ወይም ወደፊት መዝገብ የሚገቡ ፤ መዝገብም ከገቡ በኋላ በትንሹ አንድ ዓመት የሆናቸው የኢትዮጵያና ወይም የውጭ አገር ዜጎች ባለፋብሪካዎች ፥ ባለባንኮች ፥ ነጋዴዎች ወይም ልዩ ልዩ ሥራ ዐዋቂዎች ፥ የእርሻ ሥራ አዋቂዎችና እንደዚሁም የንግድ ማኅበሮች ፥ የኩባንያዎችና የኮርፖሬሽን ወኪሎችና ሌሎችም ሕጋዊ ሥያሜ ያላቸው ማኅበሮች ናቸው ።

፫/ በነጋዴዎች ምክር ቤት ደንብ (ዕለታቱ) ወይም በዚሁ ደንብ ላይ በሚደረገው በማናቸ ውም ማሻሻያ የንግድና የኢንዱስትሪ ሚኒስትራችን እንዲስማማበት ያስፈልጋል ። የመጀመ ሪያው ደንብና በዚሁ ደንብ ላይ ወደፊት የሚደረገው ማናቸውም ማሻሻያ ግልባጭ በንግድና በኢንዱስትሪ ሚኒስትራችን ይቀመጣል ። ሕዝብ እንዲያውቀውም <u>በነጋሪት ጋዜጣ</u> ይወጣል ።

### <u>የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ</u>

የዚህ አንቀጽ የእንግሊዝኛው ቅጂ <u>በነጋሪት ጋዜጣ</u> ይወጣል አይደለም ።

፬/ የነጋዴዎች ምክር ቤት ሥራ እንደሚከተለው ይወሰናል ፡—

ሀ/ ሕግ በሚፈቅደው አኳኋን በንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችን ንግድና እንዱስት ሪን ማስፋፋት ፤

ለ/ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛትና በውጭ አገር ባሉት አባሎች መኻ ከል የንግድና የኢንዱስትሪን ማስታወቂያ አስፋፍቶ መንገር ፤

ሐ/ በሌሎች አገሮች ካሉት የነጋዴዎች ምክር ቤቶች ጋራ የወዳጅነት ግንኙነት ማቋ ቋምና በመካከላቸው ስላለው የጋራ ጥቅም ማስታወቂያ መለዋወጥ ፤

www.chilot.me



መ/ የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችንን ንግድ ወይም እንዱስትሪ የሚነካውን ማናቸውንም ነገር ለመንግሥታችን ለባለክፍሉ ሚኒስቴር ወይም መሥሪያ ቤት ማቅረብ ፤

ሠ/ ስለንግድ ወይም ስለእንዱስትሪ ጉዳይ በአባሎቹ መካከል የሚነሣውን ማናቸውንም ክርክር በሽምግልና ማየትና መገላገል ።

፭/ የነጋዴዎች ምክር ቤት ባንድነት የሚሠራ ፤ ባንድ ስም የሚጠራ ፤ አላፊነት ያለው ነው ። ስለዚህ እያንዳንዳቸው ለነጋዴዎች ምክር ቤት ሊሰጡት ከሚገባቸው ፋንታ (ድርሻ) በላይ እነዚህ ሰዎች በሚያደርጉት ስሕተትና ጥፋት አባሎቹ መጠየቅ የለባቸውም ።

፮/ የነጋዴዎች ምክር ቤት አባሎች ሊከፍሉት የሚገባቸውን ድርሻ ወይም ፋንታ ሊገምትና ሊወስን መብት አለው ።

፯/ የነጋዴዎች ምክር ቤት እንደሚከተለው በሚመረጡ በአሥር (፲) ዲሬክተሮች ጉባዔ ይካሄዳል ፡—

ሀ/ የመጀመሪያው የነጋዴዎች ምክር ቤት ፕሬዚዳንት በንግድና በእንዱስትሪ ሚኒስትራችን ይመረጣል ፤ እሱም የዲሬክተሮች ጉባዔ ፕሬዚዳን ይሆናል ፤

ለ/ ፕሬዚዳኑ በዚህ በአሁኑ አንቀጽ የተጻፈውን ቃል ወደፍጻሜ ለማድረስ እንዲችል የንግድና የእንዱስትሪ ሚኒስትራችን በአገር ውስጥ በሚያስፈልገው ጉዳይ በገንዘብ ፤ በጽሕፈት ዕቃና በሌላም አኳኋን ርዳታ ያደርግለታል ፤

ሐ/ የነጋዴዎች ጉባዔ ፕሬዚዳን ከንግድና እንዱስትሪ ሚኒስትራችን ጋራ እየተማከረ በንግድና በእንዱስትሪ ሚኒስትራችን መዝገብ የገቡትንና በነጋዴዎች ምክር ቤት አባሎች ለመሆን ለንግድና ለእንዱስትሪ ሚኒስትራችን ጥያቄ ያቀረቡትን የታወቁ ነጋዴዎች ፤ ባለፋብሪካዎች ፤ ልዩ ልዩ ሥራ አዋቂዎች ፤ ኩባንያዎችና ኮርፖሬሽኖች መዝገብ እያገባ ለአባልነት ይቀበላቸዋል ፤

መ/ ከዚህ በኋላ ፕሬዚዳኑ የነጋዴዎች ምክር ቤት የዲሬክተሮች ጉባዔ አባሎች የሚመረጡበትን ጊዜና ስፍራ ለአባሎች ሁሉ ያስታውቃል ፤

ሠ/ የሚመረጡትም የድምፅ ብልጫ ያገኙ ዐሥር (፲) ሰዎች ናቸው ፤

ረ/ ከዚህ በኋላ ፕሬዚዳኑ አዲስ የተመረጠውን የዲሬክተሮች ጉባዔ ይሰበስባል ፤

ሰ/ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፕሬዚዳኑና የዲሬክተሮች ጉባዔ አባሎች ሁሉ ከዚህ በላይ በንዑስ ክፍል (ሠ) በተመለከተው መሠረት በያመቱ ይመረጣሉ ። የዲሬክተሮች ጉባኤ ፕሬዚዳን የነጋዴዎች ምክር ቤት ፕሬዚዳን ሆኖ ይሠራል ።

፰/ በዲሬክተሮች ጉባዔ ስብሰባ ሰባት (፯) ዲሬክተሮች ከተቀመጡ ፤ ነገር ለመቁረጥ ይችላሉ ።

፱/ የዲሬክተሮች ጉባዔ የሚያደርገው ውሳኔ ሁሉ በድምፅ ብልጫ ይወሰናል ፤ ድምፁ እኩል እንደሆነ ግን የፕሬዚዳኑ ድምፅ ባለበት ወገን ይወሰናል ።

፲/ የዲሬክተሮች ጉባዔ አስፈላጊ መስሎ እንደታየው አንድ ሥራ በከፊል ወይም በሙሉ እንዲያካሂድ ለፕሬዚዳኑ ሥልጣን ሊሰጠው ይችላል ።

፲፩/ የዲሬክተሮች ጉባዔ ስብሰባ የሚደረገው በፕሬዚዳኑ ጥሪ ወይም ከአባሎቹ ሦስት (፫) ሰዎች የፈረሙበት የጥሪ ወረቀት ሲጻፍላቸው ነው ።

፲፪/ ይህ የአሁኑ መተዳደሪያ ደንብ ሊሻሻል የሚቻለው አባሎቹ ሁሉ እንዲሰበሰቡ የዲሬክተሮች ጉባዔ በጽሕፈት አስታውቋቸው ማስታወቂያው ከተላከ በኋላ ቢያንስ አሥር (፲) ቢበዛ ሃያ (፳) ቀን ቆይቶ በያመቱ በሚደረገው በነጋዴዎች ምክር ቤት ጉባዔ በድምፅ ብልጫ ነው ።

፲፫/ የነጋዴዎች ምክር ቤት አስፈላጊ የሆነውን ኮንትራትና ስምምነት ለማድረግና ከዚህ በላይ በ፫ኛው አንቀጽ የተመለከተውን ወደ ፍጻሜ ለማድረስ አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ

www.chilot.me



ሥልጣን አለው ። ይኸውም ከዚህ በላይ የተመለከተውን ለማስፋፋት የነጋዴዎች ምክር ቤትና ንብረቱን እንደዋስትና አድርጐ ኮንትራት ለማድረግና ከዚህ በላይ የተመለከተውን ሀሳብ ለማስፋፋት የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለመበደር ያለው ሥልጣን ጭምር ነው ። ይህም ስለተባለ የንግድና የእንዱስትሪ ሚኒስትራችን የንጉሠ ነገሥት መንግሥታችንን ሃሳብ (ፖሊሲ) የሚነካውን ሥራ ሁሉ ለመከልከል ሥልጣን አለው ።

፲፬/ ከዚህም ሌላ የነጋዴዎች ምክር ቤት ስለሚከተሉት ጉዳዮች ለንግድና ለእንዱስትሪ ሚኒስትራችን ሃሳቡን ፣ አስተያየቱን ለማቅረብ ተፈቅዶለታል ፡—

ሀ/ በጠቅላላው ስለሚሠሩባቸው ደንቦች ፤

ለ/ አስፈላጊ በሆነው አገር ሌላ የነጋዴዎች ምክር ቤት ስለማቆምና ደግሞ ማናቸውም የንግድ ሥራ ስለሚስፋፋበት ሃሳብ ከንግድና ከኢንዱስትሪ ሚኒስትራችን ምክር ለማግኘት ፤ ነገር ግን በጠቅላላው በሚሠራባቸውና ቀዋሚ በሚሆኑት ደንቦች ካልሆነ በቀር በሌላ ጉዳይ የነጋዴዎች ምክር ቤት በሚያቀርብለት ምክር ለመስማማት በዚህ በአሁኑ መተዳደሪያ ደንብ የንግድና የእንዱስትሪ ሚኒስትራችንን የሚያስገድደው ነገር የለም ።

፲፭/ የነጋዴዎች ምክር ቤት በጠቅላላው ስለ ታሪፍ የንግድ ሥራ ለመሥራት የተሰጡትን ፈቃድ መልሶ ስለመውሰድና ስለነጋዴዎችም የጋራና ጠቅላላ ጥቅም ሐሳቡን ለንግድና ለእንዱስትሪ ሚኒስትራችን ለማቅረብ መብት አለው ።

፲፮/ የንግድ ሥራ ለመሥራት ፈቃድ ሲሰጥ ለንግድና እንዱስትሪ ሚኒስቴር ከሚከፈለው ታክስ ከመቶ ሃያ አምስት (25%) ለነጋዴዎች ምክር ቤት ተወስኖ ፤ ይህን ገንዘብ በያመቱ የገንዘብ ሚኒስትራችን ይከፍለዋል ።

፲፯/ የነጋዴዎች ምክር ቤት በጀት ሁሉ እንዲስማማበት የንግድና የእንዱስትሪ ሚኒስትራችን እንዲቀርብለት ያደርጋል ።

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳፩ ቀን ፲፱፻፵፱ ዓ.ም.

፯/፪ (፲፱፻፵) መ. ፺፬

ከዚህ ቀጥሎ ያለው የመተዳደሪያ ደንብ በጠቅላላ ማስታወቂያ ስም ታትሞ እንዲወጣ ተደርጐአል ።

## መተዳደሪያ ደንብ

በንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችን ውስጥ የቀይ መስቀል ሥራ እንዲስፋፋና ሕዝባችንንም ለመርዳት አስበን ፤ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ በንጉሠ ነገሥቱ እንዲቋቋም የሚገባ መሆኑን ተመልክተን ፤ በልዩ ችሮታችንና በሙሉ ፈቃዳችን የኢትዮጵያ የቀይ መስቀል ማኅበር አንድ አካል ፣ አንድ መንፈስ ሆኖ የመናብርት ጉባዔ በሥራው ሁሉ እየተስማማበት ይህን ማኅበራዊ መተዳደሪያ ደንብ ዛሬና በሚመጣው ዘመን እየተወራረሰ

* የመግቢያ የግርጌ ማስረጃ

በ፯/፯ (፲፱፻፵) ት. ፬ ፣ ፲፫/፫ (፲፱፻፵፮) ት. ፲፩ በግ. ሰ. ተሻሻለ ።

www.chilot.me



እንዲሠራ ከዚህ በላይ በዚህ በንጉሥ ነገሥቱ በተሰጠው መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የተጻፈውን በመከተል በተፈቀደለት ሥልጣን መሠረት ሥራውን እንዲያካሄድ ፈቅደን አዘናል ።

፩/ ማኅበሩ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ተብሎ ተሠይሞአል ፤ የማኅበሩም ዓላማ በነጭ ሰሌዳ መኸከል ቀይ መስቀል አለበት ።

፪/ ይኸውም የተመሠረተው እንደ ኤውሮፓ ቁጥር በ፲፰፻፷፬ ዓ.ም. በገኔብ ጉባዔ ተወስኖ በዚህ ቦታ እንደ ኤውሮፓ ቁጥር ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፳ ዓ.ም. እና ሐምሌ ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. ጠቅላላ ስምምነት አግኝቶ ኢትዮጵያ በ፲፱፻፴፮ ዓ.ም. በተቀበለችው መሠረት ነው ።

፫/ ይኸውም ማኅበር ከመንግሥታት ቀይ መስቀል ማኅበሮች ሁሉ የተባበረና በገኔብ ከሚገኘው የዓለም መንግሥታት ኮሚቴ ጋር የመግባባት አባልነት ይኖረዋል ።

## የማኅበሩ ዓላማዎች (ሥራዎች)

፬/ የኢትዮጵያ የቀይ መስቀል ዓላማዎች እነዚህ ናቸው ።

### በጦርነት ጊዜያት

ሀ/ የታመሙትን ፤ የቆሰሉትን የጦር ሠራዊትና ሰላማዊ ሕዝብ ሲያስታምም ዜግነትን ሳይለዩ መርዳት ፤

ለ/ ጦርነት የሚያመጣውን ጉዳት ማሳነስና ሕዝቡ ከጉዳት እንዲድን ማገዝ ፤

ሐ/ በጦርነት ምክንያት በተበታተኑት ሰዎች መኻከል የቤተ ሰብ መገናኛ አቁሞ መርዳት ።

### በሰላም ጊዜያት

ሀ/ በጦርነት ጊዜያትና በድንገተኛ ችግር የተቸገሩትን ሁሉ ችግራቸውን ለማስወገድ መዘጋጀት ፤

ለ/ በጠቅላላው የሕዝብን ጤና በማሳደግ ፤ እናትና ልጅን በጤንነት በመጠበቅ ፤ ጽዳት ፤ ምግብንና የሕክምናን አመዳደብ በማሻሻል ፤ ተላላፊዎችንና ጠንቀኞች ሕመሞችን በማስቀረት መርዳት ፤

ሐ/ ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ሥራዎች ሥራዬ ብለው የያዙትንና በፈቃዳቸው የሚያሠለጥኑትን ሰዎች ፤ እንዲሁም በሽተኞችን በቤት የማስታመም ዘዴ በማስተማር መርዳት ።

### ማኅበረተኛነት

፭/ በዚህ ደንብ ውስጥ ከ፯ እስከ ፲፩ ቁጥር የተመለከተውን ለመፈጸም ከቻለ ማናቸውም የኢትዮጵያ ወይም የውጭ አገር ተወላጅ ማኅበርተኛ ሊሆን ይችላል ።

፮/ የመናብርት ጉባዔ ቀጥሎ እንደተመለከተው ማኅበረተኛ ለመሆን ይፈቅዳል ፦

ሀ/ የክብር ማኅበረተኞች ፤

ለ/ ያንድ ጊዜ ገንዘብ ሰጭ ማኅበረተኞች ፤

ሐ/ በየጊዜው ገንዘብ ሰጭ ማኅበረተኞች ፤

መ/ በያመቱ ገንዘብ ሰጭ ማኅበረተኞች ፤

www.chilot.me



ሠ/ ተባባሪ ማኅበረተኞች ፤

ረ/ ወጣት ማኅበረተኞዎች ።

፯/ የክብር ማኅበረተኞች ለማኅበሩ ያደረጉት ልዩ አገልግሎት ሲታወቅ በመናብርት ጉባዔ ይህ የክብር ስም የተሰጣቸው ሰዎች ናቸው ።

፰/ ያንድ ጊዜ ገንዘብ ሰጭ ማኅበረተኞች የሚባሉት ቢያንስ ቢያንስ በአንድ ጊዜ አምስት መቶ ብር (የኢ.ት/፭፻) ወይም በዚሁ ልክ የሆነ ሀብት የሚሰጡ ሰዎች ናቸው ። ይኸውም ስጦታ ለገንዘብ ሰጭዎቹ እስከ ዕድሜ ልካቸው ማኅበረተኛነታቸውን ያጸናላቸዋል ።

፱/ በየጊዜው ገንዘብ ሰጭ ማኅበረተኞች በዓመት ሃያ ብር (የኢ.ት ፳) የሚከፍሉ ሰዎች ናቸው። በየጊዜው ገንዘብ ሰጭ ማኅበረተኞችም ቢያንስ ቢያንስ በአንድ ጊዜ ሁለት መቶ ብር (የኢ.ት ፪፻) ከከፈሉ ዕድሜ ልካቸው ማኅበረተኛነታቸውን ያጸናላቸዋል ።

፲/ በያመቱ ገንዘብ ሰጭ ማኅበረተኞች የተባሉ ቢያንስ ቢያንስ ለማኅበረተኛነት አሥር ብር (የኢ.ት ፲) የሚከፍሉ ሰዎች ናቸው ።

፲፩/ ተባባሪ ማኅበረተኞች የተባሉ በዓመት ከ፪ ብር (የኢ.ት ፪) የማያንስ የሚከፍሉ ናቸው ።

፲፪/ ወጣት ማኅበረተኞች ቢያንር ቢያንስ ለማኅበረተኛነት ባመት አምሳ የብር ሳንቲም (የኢ.ት ፶) የሚከፍሉ ዕድሜአቸው ከ፲፰ ዓመት ያነሰ ወጣቶች ናቸው ።

## ማኅበረተኛነት የሚቀርባቸው መንገዶች

፲፫/ ሀ/ ማንም ማኅበረተኛ በፈቃዱ በጽሑፍ ከማኅበረተኛነት ልውጣ ብሎ ሲያስታውቅ ፤

ለ/ አቅም በሚያሳጣ በብርቱ ሕመም ፤

ሐ/ በሞት ፤

መ/ ሁለት ዓመት አከታትሎ የሚገባውን ባለመክፈል ከማኅበረተኛነት መዝገብ ይፋቃል ።

፲፬/ በትንሹ ከመናብርቱ ጉባዔ አባሎች ከአራቱ ሦስቱ እጅ በፈቀደው ውሳኔ አንዱን ማኅበረተኛ ከማኅበሩ ለማስወገድ ይችላል ።

## የመናብርት ጉባዔ

፲፭/ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ባንድ ሊቀ መናብርት በዐሥራ ስድስት (፲፮) አባሎች ከዚህም ውስጥ ስድስት (፮) የተሾሙ ፤ አሥር (፲) የተመረጡ መናብርት ጉባዔ ይተዳደራል ።

፲፮/ የማኅበሩ ሊቀ መናብርት በመንግሥት ማስታወቂያ ይሾማል ፤ እርሱም የመናብርት ጉባዔ መሪ ነው ። ሊቀ መናብርቱ ከወንበሩ አባሎች ለአንድ ዓመት (፩) አንዱን ምክትል ሊቀ መንበር አድርጎ ሊሾም ይችላል ሹመቱም ለመታደስ ይቻላል ።

## የተሾሙ አባሎች

ሀ/ ያገር ግዛት ሚኒስትር ወኪል

ለ/ የአገር መከላከያ ሚኒስትር ወኪል

ሐ/ የትምህርት ና የሥነ ጥበብ ሚኒስትር ወኪል

መ/ የገንዘብ ሚኒስትር ወኪል

www.chilot.me



ሠ/ የጽሕፈት ሚኒስትር ወኪል

ረ/ የሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስትር ወኪል ናቸው ። የቀሩት አባሎች በዋናው ስብሰባ በምሥጢር ምርጫ ለአራት (፬) ዓመት ይመረጣሉ ። ከነዚህም ከተመረጡት አባሎች ውስጥ በጥቂቱ ሁለት (፪) ሐኪሞችና አንዲት (፩) ለዚሁ ሥራ ማዕረግ የተሰጣት አስታማሚ መሆን አለባቸው ። በሁለተኛው ዓመት መጨረሻ በዕጣ አምስት (፭) የመናብርት አባሎች ሲለወጡ ከዚያ በኋላ በየሁለት ዓመት (፪) የመናብርት አባሎች እኩሌቶች ይመረጣሉ ።

## የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳/፯ (፲፱፻፶፱) ት. ፪ ፡ ፫ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፩ በግ. ባ. ተሻሻለ ። (በዚህ ትእዛዝ ቀድሞ የጤና ጥበቃ መሥሪያ ቤት ይባል የነበረው አሁን የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እንዲባል ተደረገ) ፲፫/፫ (፲፱፻፵፮) ት. ፲፩ ፡ ፫ የተጠቃለሉ የኢት. ሕጎች ፩ («የጦር ሚኒስቴር» የነበረውን» የአገር መከላከያ ሚኒስቴር» ያደርገዋል ።)

፲፯/ የመናብርት አባል የሆነ በሚበቃ ምክንያት ካልሆነ ከጉባዔው ስብሰባ ሦስት (፫) ጊዜ አከታትሎ ሲቀር ጉባዔው ከጉባዔው አባልነት ሽሮ ተራ አባል ያደርገዋል ።

፲፰/ አንድ የተመረጠ የመናብርት ጉባዔ አባል አባልነቱን ሲተው ፤ ሲወገድ ወይም የማይገኝ ሲሆን ጉባዔው የተመረጠበትን የሥራ ጊዜ ካልጨረሱት ተለዋዋጭ አባሎች ላንዱ ማስታወቅ አለበት ።

፲፱/ የተመረጡትን የሥራ ጊዜ የጨረሱ አባሎች እንደገና ሊመረጡ ወይም ሊሾሙ ይችላሉ።

፳/ በሊቀ መናብርቱ አማካይነት የመናብርት ጉባዔ በወር አንድ (፩) ጊዜ ስብሰባ ያደርጋል ። ቢያንስ ቢያንስ ስብሰባ ከሚያደርግበት ከስምንት (፰) ቀን በፊት ለያንዳንዱ አባል ማስታወሻ ይልካል ፤ ወይም ለድንገተኛ አስቸኳይ ነገር ሲሆን ከስብሰባው ጊዜ በፊት ከሐያ አራት (፳፬) ሰዓት አስቀድሞ ለአባሎቹ ጥሪው እንዲደርሳቸው ያደርጋል ።

፳፩/ ሊቀ መናብርቱ ስድስቱ (፮) የጉባዔው አባሎች አነስተኛ ስብሰባ ያደርጋሉ ። በዚህ ረገድ የመጀመሪያ ስብሰባ ውሳኔ ለማድረግ ያልተቻለ ሲሆን በሁለተኛ ስብሰባ ጥሪ ተደርጐ አምስት (፭) አባሎች ሊቀ መናብርቱ ጭምር ውሳኔ ያደርጋሉ ።

የእነዚህም ቁጥራቸው አነስተኛ ጉባዔ ይሞላል ። እንደዚሁም በድምፅ ብልጫ ከሁለት (፪) የተከፈለው ነገር በሊቀ መናብርቱ ምርጫ ሊወሰን ይቻላል ።

## የመናብርት ጉባዔ የማስተዳደር ሥራዎች

፳፪/ አንደኛና ሁለተኛ ምክትል ሊቀ መናብርት ፤ የግምጃ ቤት ሹም ከጉባዔ አባሎች መኻከል መምረጥ ።

፳፫/ ለማኅበሩ ዋና ጸሐፊ መምረጥ ።

፳፬/ ሊቀ መናብርቱ በሚያቀርበው አሳብ መሠረት የማኅበሩን ሠራተኞች መሾም ፤ ማስወገድ ፤ እንደዚሁም ኃላፊነታቸውንና ደመወዛቸውን መወሰን ።

፳፭/ ከዚህ በላይ እንደተመለከተው የማኅበሩን ሥራ አኳኋን የሚቆጣጠሩ መርማሪዎችና ወኪሎች መሾም ፤ እነዚህም ሰዎች የሚመረጡት ከሹማምንት ወይም ከቀሩት የማኅበሩ አባሎች መካከል ሲሆን ደመወዝ ይከፈላቸዋል ።

፳፮/ ከማኅበሩ አባሎች መካከል ነዋሪና ለጊዜው የሚሆን ደርግ ማቆም ።

www.chilot.me



፳፯/ የዓመቱን ሂሳብ ግምት አደላድሎ ማሰናዳትና እንደገና አጥንቶ ፈቅዶ መወሰን ።

፳፰/ የማኅበሩ ሀብት ከፍ የሚልበትንና የሚካሄድበትን ዘዴ እንደዚሁም የንብረትን አቀማመጥና የተቀማጩን ገንዘብ ዝርዝር መወሰን ።

፳፱/ በየወሩ የማኅበሩን ገንዘብ ሂሳብ አጣርቶ በያመቱ የገንዘቡን ዝርዝር ማመልከቻ ለጠቅላላው ጉባዔ ማቅረብ ።

፴/ የማኅበሩን ዓላማ ለመፈጸም ስለታቀደው ፕሮግራም ዓይነት በየዓመቱ መወሰን ።

፴፩/ በማኅበሩ ዓላማ መሠረት በመናብርት ጉባዔ ምርጫ ልሻንና ይህንን የመሰለውን የምስክር ወረቀት መሸለም ።

፴፪/ የማኅበሩን የውስጥ ደንቦች ማቆም ።

፴፫/ የያንዳንዱን የጉባዔ ስብሰባ ቃለ ጉባዔ ማኖር ፤ እነዚህም ቃላተ ጉባዔ በዋናው ጸሐፊ በልዩ መዝገብ ላይ ተጽፈው ሊቀ መናብርቱና ዋናው ጸሐፊ ይፈርሙባቸዋል ።

፴፬/ ሊቀ መናብርቱና ሁለቱ ምክትል ሊቀ መናብርት በሌሉ ጊዜ በሥራ ላይ ካሉት አባሎች በሹመት ከፍ ያለው አባል በሊቀ መናብርቱ ወንበር ላይ ይቀመጣል ።

፴፭/ የጉባዔውን ሥራ ለማካሄድ አንድ ሊቀ መናብርት በዋናው ጸሐፊ፤በግምጃ ቤቱ ሹም፤ በአንድ የሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወኪልና ከተመረጡት የጉባዔ አባሎች በአንዱ አባል ስብሰባ የሚቆም አንድ አከናዋኝ ደርግ ለመወከል ይችላል ።

## የሊቀ መናብርቱና የምክትል ሊቀ መናብርት ሥራ

፴፮/ ሊቀ መናብርቱ ዋና የማኅበሩ አስተዳዳሪ ወኪል ነው ።

፴፯/ የማኅበሩን መብት የሚነካ ነገር በፍርድ ቤት ወይም በሌላ ቦታ ሲነግ እርሱ ራሱ ይቆማል ወይም በማኅበሩ ስም ሆኖ የሚነጋገር አንድ (፩) ነገረ ፈጅ በሥልጣኑ ይሾማል ።

፴፰/ ለተለመደው ደንበኛና ድንገተኛ ለሆነው ስብሰባ የመናብርትን ጉባዔና ጠቅላላውን ስብሰባ ይጠራል ። እንደዚሁም በነዋሪና ለጊዜው በቆመው ደርግ ስብሰባ ውስጥ ሊገኝ ይችላል ።

፴፱/ ስለሚቀጠሩት ፤ ስለሚሾሙትና ስለሚወገዱት ሠራተኞች ለመናብርት ጉባዔ ሐሳቡን ያቀርባል ። ስለሠራተኞች ሥነ ሥርዓት የመጨረሻውን ውሳኔ ያደርጋል ።

፵/ ለተለመደው ለዘወትር ሥራ አካሄድ ወኪል ለማድረግ ሲችል ገቢ ደብዳቤዎችን ሁሉ ይቀበላል ። ወደ ውጭም በሚሄዱት ደብዳቤዎች ላይ ይፈርማል ። በቼኩችና የገንዘብ ጉዳይ ባለባቸው ሠነዶች ላይ ከግምጃ ቤቱ ሹም ጋር ይፈርምበታል ።

፵፩/ ጉባዔውና ስብሰባው ግንኙነት እንዲያደርግ የታቀደውን የማመልከቻ ሥሌዳ እያጸናና በማስታወሻዎች ላይ እየተፈራረመ የተወሰነው ሥራ በትክክል መከናወኑን ይቆጣጠራል ።

፵፪/ ሊቀ መናብርቱ በሌለ ጊዜ መጀመሪያው ምክትል ሊቀ መናብርት ወይም ወኪሉ ምትክ ይሆናል ።

፵፫/ ሁለተኛው ምክትል ሊቀ መናብርት በኃላፊነት ይከተላል ።

## የዋናው ጸሐፊ ሥራዎች ።

፵፬/ ዋናው ጸሐፊ በጠቅላላው አስተያየት ኃላፊነታቸውን ለመፈጸም እንዲችሉ ሊቀ መናብርቱንና የመናብርቱን ጉባዔ ይረዳል ።

www.chilot.me



፹፭/ የዋናውን ጽሕፈት ቤት ሥራዎች እየመራ ይቆጣጠራል ።

፹፮/ የጉባዔውንና የስብሰባውን ረቂቆች ማስታወሻ እየጻፈ ለስብሰባዎቹ አባሎች ማሳሰቢያዎች እያዘጋጀ የአባልነትን መዝገብ ይይዛል ።

፹፯/ ከሊቀ መናብርቱ እንደታዘዘው ወጭና ገቢ ደብዳቤዎች እያሰናዳና እየተቀበለ ይፈርማል ።

## የግምጃ ቤቱ ሹም ሥራዎች ።

፹፰/ የግምጃ ቤቱ ሹም በመናብርቱ ጉባዔ በተወሰነው መሠረት የማኅበሩን ገንዘብ አካሄድ ይቆጣጠራል ።

፹፱/ ለማኅበሩ ገንዘብ አስተዳደርና ለመዝገቡም አያያዝ ኃላፊ ነው ።

፺/ የማኅበሩን ሀብትና ገንዘብ የመናብርቱ ጉባዔ በመረጣቸው ባንኮች ውስጥ በአደራ ያስቀምጣል ።

፺፩/ የወር ፣ የዓመትና ሌላም የሒሣብ ዝርዝር የሆነውን ማመልከቻ ሒሣብ በየወሩ ለመናብርቱ ጉባዔ ያቀርባል ።

## የገንዘብ ድርጅቶች ።

፺፪/ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት በግናቸውም ምክንያት የማይወጣ አምስ ሺህ ብር (፭ ሺህ) ይሰጣል ። ከዚህ ገንዘብ የተገኘው ወለድ ከማኅበሩ ሌሎች ገቢዎች ጋር ተደምሮ ለማኅበሩ ወጭ እየተከፈለና ወጭ ገንዘብ እየሆነ ይሠራበታል ።

፺፫/ የዓመቱ የገንዘብ ገቢ መወሰኛ ከመስከረም ፩ ቀን እስከ ጳጉሜ መጨረሻ ነው ። የግምጃ ቤቱም ሹም በያመቱ ገቢውን ዘግቶ ሂሳቡን ያሰናዳል ።

፺፬/ የማኅበሩ ገንዘብ ሒሣብ በዋናው እዲተር ይመረመራል ።

### የተጠቃለሉ ሕጎች ማስረጃ

በ፳፩/፫ (፲፱፻፶፬) አ. ፪፻፹፱ አን. ፰ ተሻሻለ ።

፺፭/ የገንዘብ ጉዳይ ያለባቸው ደብዳቤዎችና ቼኮች ሁሉ በሊቀ መናብርቱና በግምጃ ቤቱ ሹም ይፈረማሉ ።

## ጠቅላላው ስብሰባ ።

፺፮/ ጠቅላላው ስብሰባ በተለመደውም ሆነ በድንገተኛ ስብሰባ የሚገናኙ የክብር ፣ ያንድ ጊዜ ፣ በየጊዜው ፣ በያመቱ ገንዘብ ሰጭ ማኅበርተኞች ፣ ተባባሪ ማኅበረተኞች አሉት ።

፺፯/ ከስብሰባው የቀረ አባል በጽሑፍ አንድ ወይም አንዲት አባል ሊወክል ይችላል ። ግን አንድ (፩) አባል ከአምስት (፭) ለበለጡ አባሎች ሊወክል አይችልም ። የማኅበሩ ክፍል ዘርፍ ወኪሎች እስከ መቶ ለሚቆጠሩ አባሎች ወኪሎች ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ ።

፺፰/ በደንበኛው ስብሰባ በየዓመቱ በጥቅምት ወር ውስጥ በሊቀ መናብርቱ ሰብሳቢነት ጠቅላላው ስብሰባ ግንኙነት ያደርጋል ። ከስብሰባው ቀን በፊት በጥቂቱ አሥራ አምስት (፲፭) ቀን አስቀድሞ በሁለት ጋዜጦች ማስታወቂያ ይወጣል ።

፺፱/ ጠቅላላው ስብሰባ በመናብርት ጉባዔ መሠረት የዓመቱን የገንዘብ ማመልከቻዎችና ከሂሳብ ተቆጣጣሪዎች የቀረቡትን ማመልከቻዎች ጭምር ተመልክቶ ውሳኔ ያደርጋል ።

www.chilot.me



ይህ የስፖርት ኰንፌዴሬሽን እኛ የምንመርጣቸውን የክብር አባሎች ረዳትነትና ድጋፊነት የሚያገኝ ይሆናል ። ሥራውንም የሚያከናውነው በዚህ ከንጉሠ ነገሥቱ በተሰጠው መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የተጻፈውን በመከተል በተፈቀደለት ሥልጣን በሚሠራ በመናብርት ጉባዔ በኩል ነው ።

## የኰንፌዴሬሺኑ ስምና የመለዮ ቀለም ።

፩/ የኰንፌዴሬሽኑ ስም የኢትዮጵያ ሕዝብ የስፖስት ኮንፌዴሬሺን (ኢ.ሕ.ስ.ኰ.) ተብሎ ተሰይሚል ። ከዚህም ቀጥሎ ኰንፌዴሬሽኑ እየተባለ ይጠራል ። ደግሞም ኰንፌዴሬሽኑ የመናብርቱን ጉባዔ ውሳኔ ተከትሎ የተፈቀደላቸው ተጨዋቾችና ሹማምንት ፤ ከሌሎች መንግሥታት ሕዝቦች ጋር በሚደረገው የስፖርት ግጥሚያ ስለኢትዮጵያ ሲወከሉ የኢት ዮጵያን ሕዝብ ሰንደቅ ዓላማ ቀለሞች እንዲለብሱ ሲፈቅድላቸው ይችላል ።

## የኰንፌዴሬሽኑ ዓላማ ።

፪/ የኰንፌዴሬሺኑ ዓላማ በንጉሠ ነገሥት ግዛታችን ውስጥ በጠቅላላው የስፖርትን ጨዋ ታና የሰውነትን ማጠንከር ሁኔታ ትምህርት ማስፋፋት ፡ ማዘጋጀት ፡ መስበክና ተወዳጅ ማድረግ ። ደግሞም የሕዝባችንን የስፖርት መንፈስ ማነቃቃት ነው ።

## የመናብርት ጉባዔ

፫/ ማኅበሩ የሚተዳደረው እኛ የምንሾማቸው አንድ ፕሬዚዳን አንድ ምክትል ፕሬዚዳን ፤ አንድ ዋና ጸሐፊ ፤ አንድ ገንዘብ ያዥና በየጊዜው አስፈላጊ መስሎ እንደታየን የምንሾ ማቸው ተጨማሪ አባሎች ፤ ደግሞም የያንዳንዱ የኢትዮጵያ የስፖርት ፌዴሬሺን (ኢ.ስ.ፌ.) ፕሬዚዳኖች በሚገኙበት የመናብርት ጉባዔ ነው ። የመናብርቱ ጉባዔ የዚህን አዋጅ ጽሑፍ ሳይተላለፍ የኢትዮጵያ ልዩ ልዩ የስፖርት ፌዴሬሽን ደረጃ ለመወሰን ሙሉ ሥልጣን አለው ።

፬/ የመናብርት ጉባዔ የውስጥ ደንቡን ራሱ ይሠራል ።

## የጉባዔው ሥራዎች

፩/ በ፪ኛው አንቀጽ የተጻፈውን ዓላማውን ይፈጽም ዘንድ የጉባዔው ሥልጣንና ሥራ እንደ ሚከተለው ይሆናል ።

፪/ በንጉሠ ነገሥት ግዛታችን በሚገባ የተቋቋመውን የስፖርት ጨዋታ በጠቅላላው ማስተ ዳደርና የኢትዮጵያን የስፖርት ፌዴሬሽንና ክበቦች በቴክኒክና በገንዘብ ረገድ መቆጣጠር ።

፫/ እንደዚህ ያሉትን ፌዴሬሺን ሥራ መርዳት ማስማማትና እንዲስፋፉ ማድረግ ።

፬/ የኢትዮጵያ የስፖርት ፌዴሬሽን የተቋቋመበትን ደንብ ፤ ተጨማሪ ደንብ ፤ ሌሎችንም ደንቦችና ሥርዓቶች ማዋሐድና መፍቀድ ፤ አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ ማፍረስና መሰረዝ ። ደግሞም የኢትዮጵያንና የሌሎችንም አገሮች የስፖርት ፌዴሬሽን ግንኙነት መፍቀድና የግንኙነታቸውንም ጽሑፍ በኢትዮጵያ የስፖርት ፌዴሬሽን ማቋቋሚያ ደንብ ተጨማሪ ደንብና ሥርዓቶችም ውስጥ ገብቶ እንዲጻፍ ማድረግ ።

፭/ ሀ/ ከውድድር በሚነሱ ክርክሮች ፤

ለ/ ከኰንፌዴሬሺን ወይም ከክበቦቹ ግንኙነት በሚነሱ ክርክሮች ፌዴሬሺኑ ወይም የፌዴሬሺኑ አባል የሆኑት ክበቦች ሊፈጽሙት ባልቻሉት ሁሉ ላይ ውሳኔ ማድረግ ።

www.chilot.me



ደግሞም የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችን ልማት በመገናኛና በማመላለሻ ምቾት ብርታት በተቻለ ፍጥነት እርምጃውን ወደፊት እየቀጠለ እንዲሄድ ምኞታችን ስለሆነ ፤

በሕዝባችን መካከል ታላቅ የሆነ የአይሮፕላን ፍቅር እንዳደረ ስለተረዳነው ፤ የዚህም ፍቅር እድገት ለሕዝቡ ዋጋና ጥቅም ያለው መሆኑን ስላወቅን ፤

ወደፊት ክለብ ተብሎ የሚጠራውን በፈቃዳችንና በአሳባችን በዚህ የመንግሥታችን ቻርተር በእኛና በእኛ ወራሾች በንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት የቆመ ያየር ክለብ በስሙም በሥራውም አንድ ሆኖ ተባብሮ እንዲሠራ ፈቅደን አዘናል ።

፩/ ክለቡ በአይሮፕላን ረገድ መሠረታዊ እውቀትንና ስለመብረርም መደበኛ ልምድ ማስተማር ነው ።

፪/ ክለቡ ለአትራፊነት የተቋቋመ አይደለም ። ግናቸውም አባሉም የገንዘብ ትርፍ ማግኛ ሥራ አይሠራም ።

፫/ ክለቡ ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ ፕሬዚዳን ፤ አንድ ምክትል ፕሬዚዳን ፤ አንድ ዋና ጸሐፊ ፤ አንድ ግምጃ ቤትና ስድስት (፮) አባሎች በሚገኙበት የዲሬክተሮች ኮሚቴ ይተዳደራል ። ያስተዳዳሪው መሥሪያ ቤት ተግባርና ሥልጣን ደግሞም ጠቅላላው ደንብና ሥርዓት እኛ ፈቅደን በክለቡ መቋቋሚያ ደንብ ውስጥ ይወጣል ።

፬/ ይህን ቻርተር ከፈቀድንበት ቀን አንስቶ ከዚህ በላይ እንደተጻፈው አኳኋን የመጀመሪያው የዲሬክተሮች ኮሚቴ የክለቡን አቋቋም አዘጋጅቶ አቅርቦልን እስክንፈቅድ ድረስ የሚከተሉት ደንቦች ጸንተው እነዚህም በክለቡ አቋቋም ደንብ ውስጥ ይጻፋሉ ፡—

ሀ/ የመጀመሪያው አስተዳዳሪ ጉባዔ አባሎች የሚመረጡት የአደራጁው ኮሚቴ አባሎች ጭምር በሚገኙበት በቻርተሩ አባሎች ነው ፤ እነርሱም ፕሬዚዳንን ፤ ምክትል ፕሬዚዳኑን ፤ ዋና ጸሐፊውን ፤ ግምጃ ቤቱንና ደግሞ እስከ ነሐሴ ወር መጨረሻ ድረስ በሹመታቸው የሚቆዩትን ስድስት (፮) አባሎች ከመሐከላቸው ይመርጣሉ ፤ በዚያን ጊዜም ከዚህ በላይ በተጻፈው አኳኋን አዲስ ፕሬዚዳን ፤ ምክትል ፕሬዚዳን ፤ ዋና ጸሐፊ ፤ ግምጃ ቤትና የኮሚቴ አባሎች ይመረጣሉ ፤

ለ/ የክለቡ ደንበኛ ማኅበረተኞች በየዓመቱ በመስከረም ወር የዲሬክተሮች ኮሚቴ የሚያቀርበውን ያመት ራፖር ለመቀበልና ፕሬዚዳን ፤ ምክትል ፕሬዚዳን ፤ ዋና ጸሐፊ ፤ ግምጃ ቤትና የኮሚቴ አባሎች ለመምረጥ የዓመት ስብሰባ ያደርጋሉ ። የነዚህም ሹማምንቶች ምርጫ የሚፈጸመው በዓመቱ ስብሰባ ውስጥ ባሉት ማኅበረተኞች የድምፅ ብልጫ ነው ፤

ሐ/ የገንዘብ ኃላፊነቶች የሚከናወኑት በክለቡ ማኅበረተኞችና በሥራው ላይ ካሉ አባሎች ከሚገኘው ግብርና አባሎች ከሚከፍሉት የትምህርት ዋጋ ፤ ደግሞም በአየር በተበረረበት በየአንዳንዱ ሰዓት ልክ የኢትዮጵያ መንግሥት ከሚከፈለው የእርዳታ ገንዘብና እንዲሁም በልዩ እርዳታ ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ከሚሰጠው ችሮታዎች በሚገኘው ገንዘብ ነው ፤

መ/ የክለቡ ግምጃ ቤት በያመቱ በመስከረም ፩ ቀን ስለክለቡ ገቢና ወጭ ሙሉ የሒሳብ ራፖርና ስለክለቡ የመብረር ሁኔታዎች አንድ ራፖር አዘጋጅቶ ለዲሬክተሮች ኮሚቴና ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ሲቪል አቪያሲዮን ያቀርባል ፤

ሠ/ ክለቡና ማኅበረተኞቹ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ሲቪል አቪያሲዮን በዓየር ስለመብረር ለሚያወጣቸው ሲጸኑበት ለሚችሉት ድንጋጌዎች ሁሉ ይታዘዛሉ ፤ ይተባበራሉም ፤ እንዲሁም ደግሞ የዲሬክተሮች ኮሚቴ ጠቃሚ መስሎ እንደታየው በቶሎ ከኢንተርናሲዮናል ያየር ማኅበር ክለቦች ጋር የሚዛመድበትን መንገድ ይፈልጋል ።

